

# ባይራ

ባያሬ ጸሺታፊ ፀፀጸሔት

## ቅጽ ፩ ቁጥር ፩

ባይራ ዲጂታል መጽሔት
ቅጽ 2 ቁጥር 1

---

**ዋና አዘጋጅ**

ውብአረገ አድምጥ

**ምክትል አዘጋጅ**

ሩት ሃብተማርያም

**ግራፊክስ ዲዛይን**

ብርሃን ደርበው

**አርታኢ**

ልዑልሠገድ አስማማው





**ዋና አዘጋጅ**

ውብአረገ አድምጥ

**ምክትል አዘጋጅ**



ሩት ሃብተማርያም



**ግራፊክስ ዲዛይን**

ብርሃን ደርበው

**አርታኢ**



ልዑልሠገድ አስማማው



ጂቡቲም የኛ ናት....................05
ዓለማየሁ ታዬ

ሰፈድ.........................19
ሐና አበበ

አዕዋፋት እና ካፊቾዎች..................20
ዙፋን ክፍሌ

እኔና ቤቴ ግን ውበትን እናመልካለን........28
ሮሐ ናትናኤል

ጥበቃ (Expectation)............42
ደምስ ሠይፉ

ባይራታ.........................45
ሩት ሃብተማርያም


ስሜትን ፍለጋ-አንድ.................52
ወ/ሚካኤል አደሙ (ዕዝራ-ዘዓብ)

ባይራ ውይይት.......................58
ባይራ

"ተዓምሩ" ጫሌ፤ የወረ-ባቦው ንጋት......62
ነቢል አዱኛ

"የጎፋ ተረቶች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችና
እንቆቅልሾች" መጽሐፍ ዳሰሳ..............69
በመ/ር ይርዳው ግዌ ዶምባ (በዌክሎር MA)

አዲስ ልብስ ወዳለሁ....................78
ሳምራዊት ንጉሤ



# ጂቡቲም የኛ ናት

ዓለማየሁ ታዬ



ከሚሆን ይልቅ ”ፈረንሳይ ጀምራ ያልጨረሰቻት ሃገር” ቢሆንም ኖሮ የዚህ ወግ ርእስ ያስኬድ ነበር።
ጂቡቲ እንደምን የኛ ሆነች? ፈረንሳይስ ምን ቆርጧት ኮረዳዪቱን ጂቡቲ እንደ ልግመኛ አፍቃሪ ነካክታ ሳትጨርሳት/ሳታስጨርሳት ኮበለለች? ተከተለኝና አሃዱ ብዬ ልጀምርልህ።

## አሃዱ

ያቺም አገር የኛ ናት የሚል ጠነን ያለ ባለቤትነትን አመልካች ሃሳብ የተሰነዘረው አዲሁ በዘፈቀደ ወሬ ለማጣፈጥ ወይም ጦርነት ለማወጅ ታቅዶ አይደለም። የፖለቲካ ሳይንስ እንደሚያስረዳው አንድ አካባቢ በውስጡ ተመሳሳይ ቋንቋ ሲነገርበት፣ ተመሳሳይ ኃይማኖት ሲመለክበት፣ ተመሳሳይ ዝርያ ያላቸው ሰዎች ሲኖሩበት፣ ተመሳሳይ መልክአ ምድር ውስጥ ሰዎቻቸው ሲወለዱና ሲዋለዱበት እንዲሁም ነዋሪዎቹ ተመሳሳይ ባህል ወግ ትውፊት ህልምና ራእይ ሲኖራቸው እነዚህ ሰዎች አንድ አገር አንድ ኅዝብ ይሰኛሉ።

ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች በመፈቃቀር በመተሳሰብ አብሮ በማደግ ምኞት ላይ ተቀንብበው ሲሸመኑ ደግሞ ኅብረ ብኄራዊነታቸው ያብባል፣ ይጎመራል። የፅድቅና የሰላም ፍሬም ያፈራል። ወዲያውም “ጠላትን ያሳፍራል፤ ወዳጅንም ያኮራል” እንዲሉ ያዲሳባ ፀሃፊ ወጎች።

እኔን ጂቡቲም የኛ ናት ያሰኙኝ እንደዚህ ጠነን ያሉ ጠጣር ሶሺዮ ፖሊቲካል እውነታዎች ብቻ አይደሉም። ስፍር ቁጥር የሌላቸው በርካታ ገራገር ትዝብቶች እንጂ። ስለሁለቱ ህዝቦች ኅብረ ኑባሬ ለማሰስ ወደዚያው ለማምራት ሳስብ...

"ጂቡቲ ዋእይ ናት። ሙቀቷ እንኳን ትንፋሽን ወኔንም ሳይቀር ይሰልባል፤ አገሪቱ ለደገኛ/ highlander የምትሆን ደገኛ አገር አይደለችም" የሚል ሃሳብ ጠብሰቅ አደረገኝና ደርሰው የተመለሱ/አንዳንዶቹም በዚያው የሚኖሩ ወዳጆቼን የትኛው ወቅት ሻል ያለ የአየር ንብረት ይኖረዋል ብዬ ጠየኩ። ኅዳር እና ታኅሳስ ተመርጦልኝ ጓዜን ቀረቀብኩ።


ጉግል አድርጌ ያገኘሁት የሆቴል ባለቤት የሚያምር ባላንድ ክፍል አልጋ ከነሙሉ የኪችን እቃና መታጠቢያ ቤት ፎቶግራፍ ለጥፎ ቢያስተዋውቅም እስፍራው ሲደረስ ግን ጉዳዩ ሌላ ነው። አንድ ቀን አድሬ ወደሌላ ማረፊያ አመራሁ። እንዲያውም የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ የተመሰረተበት መንደር አቅራቢያ በሚገኘው ራያን ሼዳ ሆቴል መሰንበቻዬን አደላደልኩ።

ሆቴሉ ክፍያውን በጂቡቲ ፍራንክ ቢከፍሉም፤ በአሜሪካን ዶላር ቢከፍሉም ግድ አይሰጠውም። ሪሴፕሽን ላይ ያስተናገደችኝ ገፅታዬን ተመልክታ ሃበሻ መሆኔን አልሳተችውም። ብር መመንዘሬን በአማርኛ ቋንቋ ጠየቀችኝ። "ተጠንቀቅ እንዳይበሉህ" ብላ አስጠነቀቀችኝ። ልሳኗ እንደ ልጅ አንደበት ይጣፍጣል። የሰሞኑን የዶላር የምንዛሪ ዋጋ ነገረችኝና ሻንጣዬን ለማገዝ እየታተረች ወደ ተከራየሁት ሩም መራችኝ። ሆቴሉ ጥድት ያሉ ክፍሎች አሉት።

የመግቢያ ቁልፉ እንደ ኤቲኤም ካርድ ያለ ነገር ነው። ከውስጥ እንደገቡ ለካርዱ ማኖሪያ ሚጢጢ ሰንዱቅ ግድግዳው ላይ ተሰቅላለች። ካርዱን እዚያ ሲያስቀምጡ የክፍሉ መብራት ወከክ ይላል ኤሲውም ይለኮሳል። ካርዱን ሲያወጡት ደግሞ ሁሉ ድርግምግም ይላል።

ትንሽ እረፍት አድርጌ ወደ ኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ሆቴል አመራሁ። ከኢትዮጵያ ኮሙኒቲ በስተግራ በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ያሸበረቀ ቤተክርስቲያን በክብር ተሹሟል። ታኅሳስ ገብርኤል ነገ መሆኑ ታወሰኝ። የቤተክርስቲያኑ የውጪ በር ወለል ብሎ ተከፍቷል ነጣላ የለበሱም ያልለበሱም ሃበሾች ግቢ ውስጥ ውር ውር ይላሉ። የጠመጠሙ ቀሳውስትም ለነገው ክብረበዓል ዝግጅቱን ለማሳለጥ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ይታያሉ። ደጀ ሰላሙን ተሳልሜ ወደ ኮሙኒቲው አመራሁ።

የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ማኅበር ግቢ መግባት ሰፋ ወዳለ የቀበሌ ክበብ እንደመግባት ነው። ወደ ውስጥ ስትዘልቅ በሃበሻ ልብስ የደመቀች ሴት ቡን ታፈላለች። በርካታ ኢትዮጵያውያን በተለይ ሸምገል ያሉ ረከቦቷን ከበው ባገርኛ ቋንቋ ያወጋሉ።




እንግዳ መሆኔን የለዩቱ

“እንግዳ ነህ? ኖር! አረፍ በልና ቡና ጠጣ”

ቢሉኝም ትንሽ አረፍዳለሁ ብዬ ወደ ውስጥ ዘለኩ። የኮሙኒቲው የምግብ አዳራሽ ሰፊ ነው። አንዱ ጥግ ላይ ተቀመጥኩና ሜኑውን ቃኘሁት። ሜኑው ባበሻ ምግቦች ስም ዝርዝር ተሞልቷል። ክትፎ፣ ዶሮወጥ፣ የበግ ጥብስ፣ የፍየል ጥብስ፣ ቅቅል፣ ፉል... ወዘተ በመደዳ ተሰድረው ገበያ ወጥተዋል። እነ ሽሮ፣ ፍትፍትና፣ የፆም ቡፌ ሳይቀሩ ባማርኛ ቋንቋ በተዘጋጀው ሜኑ ላይ መካተታቸው የጂቡቲ ወገኖቻችን ባበሻ ምግብ አምሮት አይጎማጁም የሚል የመፅናኛ ቃል ሹክ አለኝ።

ወደ ውጭ ተመልሼ ቡን የሚፈላበት በረንዳ ላይ ያለውን ጉባኤ ታደምኩ። ሃበሾቹ የባጥ የቆጡን እያነሱ ይጫወታሉ። አጠቃላይ ድባቡ አገር ቤት እንጂ ጎረቤት አገር አይምስልም። የተደናቀፈ “እኔን” ይባላል፣ ያስነጠሰ “ይማርክ” ይባላል፣ በቡና አፍዪዋ ላይም “ ሙድ “ ይያዛል።

“አዲስ ባል መቶልሻል ቆንጂት” አሏት።

አንድ ሳቅ ሳቅ የሚሉ አዛውንት እኔን ጠቀስ እያረጉ።

“በደስታ አለች!” ኮረዳዪቱ ባይኗ ጥግ እየገረመመችኝ። ጠይም ናት። ጠያይማን ደግሞ ክፍሌ ናቸው። (ይናፍቅሃል! አትለኝም) ለሼባው ሞቅ ያለ ፈገግታ መገብኳቸው።

“ታዲያ ምን ትላለህ?” አሉኝ

“ጠሎት አድርጊ!” አልኳት ልጅቱን ጎርነን ባለ ድምፅ። ሳቁም ጨዋታውም ደራ። ግን seriously I am so handsome. ያለ ጦም ያለጠሎት የምቀመስ አይነት ነገር አይደለሁም (ወይዛዝርት ካላመናችሁኝ ጉግል አድርጉኝ)። ለግብዣው ሻይ ብመርጥም ቡና ብቻ ነው ያለውና ቡኑንም ወጉንም ተቀላቀልኩ።

ጂቡቲ በርካታ ኢትዮጵያውያንን በጉያዋ አቅፋ ትኖራለች ታኖራለች። ኮምቦልቻና ድሬ ዳዋ ቅርብ ስለሆኑ ወፈሰማይ የነዚያ አካባቢ ፈላሲያን እዚህ ከትመዋል - ከጥንት ጀምሮ። ሴቶቹ በቤት ስራ ወንዶቹ ደግሞ በጥበቃ። በቅርቡ ደግሞ ከፍቼ ሰላሌና ከደራ የመጡ ቆነጃጅትና ጎረምሶች ጂቡቲን እየወረሩ መሆኑን ሽማግሌዎቹ አወጉኝ።

"እንጀራ አለ ብለው አይነግሩም ለደሃ
አቋርጦ ይመጣል አርባራቱን ውሃ"
እንዲል ያገራችን ስንኝ። ከደራ እና ከ ፍቼ ሰላሌ ሰሞናዊ የፖለቲካ ግርግር የሸሹ ዘመዶቻችን ጂቡቲን የቡና ሱሰኛ አድርገዋታል። ሴቶቹ ያን የሚያምር ወዘናቸውን በፈገግታ አጅበው ቡና በፔርሙዝ ሞልተው ከተማዋን ሲያካልሏት ይውላሉ። ወገኖቻችን ሲፈልሱ ሰርተው እንጂ ሰርቀው አይበሉም። ባልተገባ ተግባር ለመሳተፍ መንገድ ላይም አይቆሙም።

ተርበውም አይሞቱም፤ ወይ ለምፅዋት እጃቸውን አይዘረጉም። እንዲህ ናት የኔ ኢትዮጵያ!!!! (በገራገር ዓይን ስታዘባት)
በቡና ወጎቻችን መሃል ውይይቱ አዲሳባ ውስጥ ስለፈረሱት ቤቶችና ስለቀጣይ የልማት ተነሺዎችስለ፤ ኮሪደር ልማት፤ ስለ ልግመኛ ፖለቲከኞች፤ ስለ ተራማጅ ባለስልጣናት፤ ስለ ዱርቤቴ ተዋጊዎች... ወዘተ ብቻ እንዲሆን ስላልፈለኩ የውይይቱን አቅጣጫ ሆን ብዬ ጠመዘዝኩት።

ስለ ጂቡቲ አጠቃላይ ቀጠናዊ፣ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ እና ስነልቦናዊ ስሪት ርእስ አድርጌ ለማውጋት እንዲመቸኝ የውይይቱን አቅጣጫ ወደዛው ጠመዘዝኩት። በንባብ ያገኘሁትን ከነዋሪዎቹ አንደበት ለመስማት።

አባቱ! ያገሪቱ ሰዎች ተብለው የተበየኑት ሁለት ጎሳ አላቸው። አፋርና ኢሳ። በደወሌ መስመር አውራ ጎዳናውንም ይሁን ጉራንጉሩን ይዘህ ከድሬዳዋ ወደ ጂቡቲ ብታቀና እንዳለ ኢሳ ነው። በጋላፊ መስመር ደግሞ ከአዋሽ እስከ ጂቡቲ አፋር ነው። same race ምን ያመልካሉ? አላህን። Same religion ምን ይነጋገራሉ? አፋርኛን/ሶማሊኛን። Same language መልከአምድራቸው ከማን ጋር መሳ ለመሳ ነው? ከኛው ጋር። Same geographical location ባህላቸው የተጨለፈው ከየትኛው ውሃ ነው። ከፈለቁበት ከአዋሽ ወ ከደወሌ። Same culture ደማቸውስ የማን ነው? የአፋርና የኢሳ። Same blood ወዘተርፈ ወዘተራርፈ።




## ታዲያ ጂቡቲም የኛ ናት አትለኝም?

ምኒሊክ በዚች አገር ንጉስ ናቸው። በአገሪቱ ታሪካዊና ማራኪ መንደር የሚሰኘው የሳቸው ግዛት ነው። ልጥቀስልህና “Place Menelik is the central square, a shady and historic area known as the center of the town, home to the tourist office and other buildings, and also known for its vibrant nightlife with bars and nightclubs”

የከተማዪቱ ድረገፅ ውስጥ ገብተህ best place to visit in Djibouti ምናምን ብለህ ብትፅፍም። ከሌሎቹ መሃል የምኒልክ ግዛት “Place Menelik” ከች ይልልሃል። በጃንሆይ (እምዬ ምኒልክ) ስም የተሰየመ ገዘፍ ያለ ሆቴልም ከተማዋ እምብርት ላይ በግርማ ሞገስ ተጎብሯል። በጓሮ በኩል ዞር ስትል ደግሞ ባር ምኒልክ የሚል ታፔላ ታያለህ ወደዚያው ስታመራም በሩ ላይ ጎራ በል እስኪ ብለው ገዘፍዘፍ ያሉ ጋርዶች ይጋብዙሃል። የምኒልክ ሆቴል ባለቤት ሃበሻ መሆኑ ተነግሮኛል። እዚያው ምኒሊክ አደባባይ ላይ በርካታ በሃበሻ ባለቤትነት የተያዙ ሌሎችም ናይት ክለቦች አሉ።



ጎልደን እና ለማሬስ ሁለቱም የኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ሰምቻለሁ። አመሻሽ ላይ ባር ላማሬስ ጎራ ብዬ ቢራ አዘዝኩ የታዘዘችኝ ኢትዮጵያዊት ናት። የድሬ ልጅ። እንግዳ መሆኔ ገብቷታል።

“መርከበኛ ነህ?”
“አይደለሁም ጎብኚ ነኝ” (ለምን ሹፌር ነህ ብላ አልጠየቀችኝም?) ጂን ብጤ ተጋበዘችልኝ። ብዙ ቢራ የመጠጣት ፍቅር ቢኖረኝም ፊያቶ ግን ስለሌለኝ ጊዜ መግደያ መወያያም ይሆናል በሚል ሰበብ፤ “ፑል እንጫወ” አልኳት። እሷ ስትሬት (Straight) መረጠች እኔ ደግሞ ኤይት ቦል(Eight ball) መረጥኩና በኔ ምርጫ ፀናን። ቀጣጣኋት አልልህም። ለኤይት ቦል የሰለጠነ ስኪል አለኝ (ካላመንከኝ ወዳጆቼን ጠይቅ)። እየተጫወትን ስናወጋ የጂቡቲ መኖሪያ ፈቃድ እንደሌላትና በራሷ አንደበት “ላይፍ ትንሽ ቦሪንግ” እንደሆነባት አወጋችኝ።

“ይሄውልህ እዚች ቤት ውስጥ ተዘግቼ ሶስት አመቴ።”
“ለምን ወደ ድሬ አትመለሺም?”
“ምን ይዤ?” ይሄ ቃልና ሃሳብ የብዙ ስደተኛ ሃበሻ የፍርሃት መንስኤና አታካቹን የስደት ኑሮ የማያስተው የግር ብረት መሆኑን አቃለሁ። ምክር ዝክር ልሞካክር ፈለኩና ምንም ላትፈይድ ብዙ መዘብዘብ እንዳትጀምር የሚል ሃሳብ ኮረኮመኝ ። ስለጂቡቱ የኑሮ ውድነት አወጋችኝ። “ከአፍሪካ ለኑሮ ውድ ከሆኑ አገሮች በቁጥር አንደኛዋ ጂቡቲ ናት” አለችኝ።

ስለኑሮ ውድነቱ ሌላም ሰው ያለምንም ያረፍተ ነገር መዛባትና የቃላት ለውጥ እንዲሁ አምርሮ ሲናገር ሰምቻለሁና ጉዳዩን ጉግል ላይ ቼክ ለማድረግ ለራሴ የቤት ስራ አዘጋጀሁ። ሰዐቱ ከምሽቱ ወደ አራት ሰአት እያቀና ስለሆነ ልጅቱን ተሰናብቼ ወደ ሆቴሌ በእግሬ አመራሁ(ምን አመራሁ እልሃለሁ ተንከራተትኩ እንጂ)። ናዝሬት አለ የሚባለው አዙሪት እዚህም ጠለፈኝ። ብዙ ሞክሬ ሳይሆንልኝ ሲቀር በፈረሳይ ቋንቋ የሚነጋገሩ ሁለት ያበሻ ወዘና ያላቸው ኮረዶች ቀስ እያሉ ዋክ ሲያደርጉ አገኘሁዋቸውና ሰላምታ አቀረብኩላቸው። በትህትና አናገሩኝ።

“ራያን ሼዳ ሆቴልን እኮ አለፍከው ና እኛ እናሳይሃለን።”

ስለቤተሰቦቻቸው እየጠየኳቸው ወደ ሆቴሌ ሸኙኝ። ከኮምቦልቻና ከራያ ከፈለሱ ቤተሰቦች ቢወለዱም አማርኛዋን ያለምንም አክሰንት ሰልጥነውባታል። አለባበሳቸው በጣም የተብረቀረቀ አይደለም። ኩልና ሊፒስቲክም የለም። በዚህ ምሽት የወጡት ምንም ፍለጋ ሳይሆን አየር ለመቀበል መሆኑን ነገሩኝ። የውስጤን ጥያቄ እዚያው በዚያው መመለሳቸው ነው። እውነትም ጂቡቲ ቀዝቃዛ በሚባለው ወርሃ ታህሳስ እንኳን በቀን ወበቋ እረፍት ይነሳል። የማታ ሽርሽርም ተለምዷዊ ተግባር ነው።

በነገራችን ላይ I have a very bad sense of direction ቅድምም እንዲሁ መንገዱ ግራ አጋብቶኝ ትልቅ ቪላ ቤት በር ላይ ተቀምጠው የሚያወጉ ሁለት ጎልማሳ ሃበሾች በባላገር ያማርኛ ዘዬ ሰላምታ አቅርበውልኝ መንገድ አመላክተውኛል።

“በይህ በኩል ዝልእና ኸጥ ብለህ ስትሄድ ኸዚያው ትደርሳለህ።”

ጂቡቲ ሰፋ ያለች ድሬዳዋ ማለት ናት። ወይም ባለወደብ ሐረርጌ ናት ልትላት ትችላለህ። ሐረርጌን ሐረርጌን የሚሸት ቃና አላት። የሚገርምህ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ እንቁ የሚታየውና የገንዘቦች ሁሉ ቁንጮ ተደርጎ የሚታሰበው የአሜሪካ ዶላር እዚህ በየመንገዱ እንደ ጉሊት እቃ መቸርቸሩ(መመንዘሩ) ነው። ሐረር ውስጥ ከገጠር የጫት እርሻቸው ቆርጠው ሸዋ በር ላይ ጫት የሚሸጡ ድሪያ የለበሱ እናቶቻችን(እህቶቻችንን) ታስታውሳለህ? ከነሱ ቁመናና አልባሳት ወ ገፅታ ጋር በእጅጉ የሚመሳሰሉ እናቶች ባራሴራምቦ (ያውቶቢስ መናኸሪያ) ላይ በአነስተኛ ከረጢት ብጤ ጫት ነው ብለህ ልትገምተው የምትችለውን ነገር ይዘው መንገድ ላይ ቁጭ ብለው ታያለህ።

እነሱ (ሸርፍሌ) ነው የሚባሉ በከረጢታቸው የያዙት ግን ጫት አይደለም። የአሜሪካ ዶላር የጂቡቲ ፍራንክ እና የኢትዮጵያ ብር ነው። ሸርፍሌዎቹ ወሮበላ ይዘርፈናል ፖሊስ ይነጥቀናል የሚል ስጋት አይታይባቸውም። ዶላሩንም መግዛት ወይም መሸጥ፤ ብሩንም ፍራንኩንም እንዲሁ ያለስጋትና ወደጎን ወደኋላ የመገለማመጥ ድራማ ታከናውናለህ። ከትናንት ወዲያ ያገራችን ባንኮች በዶላር እጥረት ሲጨናነቁ ከሚከርሙ ለምን በድሬ በኩል ወደጂቡቲ ዘልቀው ከመንገድ ላይ ሸርፍለውት(አፍሰውት) አልመጡም?

የምንዛሪውን ጣጣ ለሚመለከታቸው ጀለሶች ተወት አድርጌ ቀይ ባህራችንን ሳላይ አላድርም ብዬ ወደዚያው የሚያመራኝ ታክሲ መያዣ ስፍራ የት እንደማገኝ ያገሪቱን ፖሊሶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስጠይቅ አይነውሃዬን በማየት ብቻ የተረዱት ፋቲግ ለባሾች ከመንገዱ ማዶ ጫት የምትሸጥ ሃበሻ ጠቁመው በማቀው የኢትዮጵያ ቋንቋ እሷን እንድጠይቃት አመላክተውኛል።

## ጂቡቲ ታዲያ የኛ ካልተባለች ማን የኛ ሊባል ነው?

በአገሪቱ ጎዳና ስትዘዋወር "መዲ ሽሮ" የሚል ቃል አይንህን ይጠልፈዋል። ቡና ሃውስ የሚል ሬስቶራንትም አታጣም። እነ መዲና ምግብ ቤትና ላፎንቴ ምግብ ቤት ሁሉ በኛ ሰዎች ባለቤትነት ነው የሚተዳደሩ። ጂቡቲ ውስጥ በተለይ ኤሮንና ቤካ ዱስ የተሰኙ አካባቢዎች ያበሻ መናኸሪያዎች ናቸው። ኤሮንን ተወውና ቤካዱስ ልውሰድህ። ወደዚያ ያመራሁት ጂቡቲ ከመጣሁ አይቀር አዲሲቱን ደጀ ሰላም ማርያምን ልሳለም በሚል ሰበብም ጭምር ነው።

ከንቲባ የሚለውን ቃል ከንተበ የሚል የግእዝ ግስ ብትሰጠውና ብታረባው። ከንተበ፣ ይከንትብ፣ ይክንትብ፣ ይክንትብ፣ ከንቲቦ፣ ከንታቢ፣ ክንትብ፣ ክንታቤ እያለ ያታክትሃል። እኛ ካዲሳባ ጎዳኖች ከንትበን ከንትበን ያሸሸናቸው የደሃ እልፍኞች የኪሰ ኮሳሳ ምርጥ ሽሮ ቤቶች እዚህ ተዘርግፈውልሃል። በኬንዳ እና በቆርቆሮ የተሰሩ በርካታ ያበሻ ሽሮ ቤቶች አግዳሚ ወንበራቸውን ዘርግተው ሽሮ በእንጀራ ውሃ በኒኬል ኩባያ ያቀርቡልሃል። እነ ምስርና እነ ጎመንም አሉ።

ወቅቱ የገና ፆም ስለሆነ ይመስለኛል የዚህ መንደር አጠቃላይ ድባብ ሽሮና ምስር ነው። እጅግ በጣም ብዙ ሹፌሮች ቤካዱስ ውስጥ ሲያውደለድሉ ይስተዋላሉ። ነገሩ ጭነት እስኪመቻች የመጠበቅ ጉዳይ ይመስላል። የቤካዱስ ሽሮ ቤቶች ሆደ ቀጭን ግን ሾጣጣ ናቸው። ዝም ብለህ ወደውስጥ ከዘለክ የውስጠኛ ክፍሎች ውስጥ ሰሌን ተዘርግቶ የደከማቸው ሃበሻ ሹፌሮች ተጋድመው ታያለህ። እኔ ጎራ ያልኩበት የዘቢደር ቤት የፍቅር ቤት ይመስለኛል።

"እንግዳ ነህ ምሳ በኔ ነው!" ብላ ዘቢደር የምሳ አላስከፈለችኝም። ወደ ማርያም ሳቀናም የባጃጅ ከፍላ የላከችኝ እሷው ናት። የጂቡቲ እንጀራ የጠራት የባህር ዳር ልጅ ናት። "የቅዱስ ዮሃንስ/እንቁጣጣሽ አገሬ መጣለሁ" አለችኝ ሁለት ሶስት አመት ሰርታ ጠቅልላ እንደምትገባም ነግራኛለች። የስደት ቋት እንደማይሞላ ስለማውቅ "Good luck!" አልኳት በውስጤ።

ይልቅዬ ስለቤካዱስ ልጨምርልህ በዚህ አብዛኛው ያበሻ ምግብ አለ። ድፎ ዳቦ ሳይቀር እዚህ ይደፋል። የደነቀኝ ደግሞ ድፎ ዳቦው የሚጋገረው ሰፋ ባለ በገ ፊጅ ብጤ ድስት ነው እንጂ በሸክላ ምጣድ አይደለም። ድፎ ዳቦው መጣፈጡ!

የቤካዱስ ማኅበረሰብ ኢትዮጵያዊ የተለያየ ብሄር ቢኖረውም እዚህ ሰፈር ውስጥ ባማርኛ ቋንቋ ለመነጋገር የተስማማ ይመስላል። ምሳ በልተህ ብትፈልግ በኢትዮጵያ ብር ብትፈልግ በጂቡቲ ፍራንክ ትከፍላለህ። በቤካዱስ ብራችን ከፍራንክ ጋር እየተጋፋ አገልግሎት ላይ ይውላል። በቤካዱስ ድብርትም የለም። ቡና ይፈላል። ካርታ እየተጫወትክ ጊዜ ትገላለህ።

እርስ በርስ እየተተራረብክ ሙድ ትያያዛለህ። እነጠላና አረቂም ከዘቢደር ጓዳ ውስጥ የሚጠፉ አይመስለኝም። ጫት የለም ወይ እንዳትለኝ። እንዴት ነው ቤካዱስ ጫት የሚጠፋው? ተትረፍልፎልሃል። ከጫት ሌላ ድንች የጂቡቲ የክት እራት እየሆነ ነው። የደራ ቆነጃጅት ጂቡቲን የቡና ሱስ አስይዘዋታል አላልኩህም? የድሬ ልጆች ደግሞ ከተማዪቱን የድንች ቅቅል ፍቅር ላይ ጥለውታል። አመሻሽ ላይ ድንቻቸውን/እርጥብ የሚሸጡ የድሬ ቆነጃጅት በጂቡቲ ሰዎች የእራት ገበታ ላይ አዲስና ጣፋጭ ሜኑ አስተዋውቀዋል (አስለምደዋል)።

ቤካዱስ አካባቢ የሚኖሩ ወዳጆቼን አንድ ሁለት ቤቶች አስጎብኘዪ ተሼ አሳይቶኛል። ካዲሳባው ባላንድ ክፍል የትናንትና ጨረቃ ቤቶች የማይተናነሱ በርካታ ኪራይ ቤቶች አሉ። እዚህ ግን በብሎኬት እንጂ በ ጭቃ/አፈር የተገነቡ አይደሉም። የቤቶቹ የውስጥ ክፍል እና የተከራዮቹ የኑሮ ዘይቤ ግን ተመሳሳይ ነው። አልጋዋ እዚያው በ መጋረጃ ተጋርዳለች። ጥጋጥጉ ላይ ማብሰያ ሚጢጢ ስቶቭ፣ ኮሞዲኖ፣ ቁምሳጥን፣ የውሃ ባልዲ፣ የልብስ ማጠቢያ ሳፋ፣ የቡና ረከቦት ከነጓዙ፣ ድንች፣ ቲማቲም፣ ቃሪያ… በቃ ምን አለፋህ ባንድ ትንፋሽ ያገርህን(የመሰሎችህን) ኑሮ እዚህ ታገኛለህ። ሻይ ቡና ይፈላልሃል። መስተንግዶው ልብህን ያሞቀዋል።

ተሼ የሎጂስቲክ ባለሙያ ነው። ትህትናና እንግዳ ተቀባይነቱ አንጀት ያርሳል። አንድ ዐይና ብዬ ሙድ በያዝኩባት ዶቅዶቁው(Scooter) ከተማውን ሲያዞርህ የጂቡቲን መግቢያ መውጫ አብጠርጥሮ እንደሚያውቀው ትረዳለህ።

የግራ ፍሬቻዋ በረገፈው ዶቅዶቄው አፈናጦ የቀድሞ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያሁኑ ሺፒንግ ላይንን ህንፃ ይዘን ወደ ምኒልክ አደባባይ ስናመራ ይሄ ራስ መኮንን ጎዳና ይባላል አለኝ። የኢትዮጵያ ጎዳና ደግሞ ከነ ጎልደን ባር ፊት ለፊት ያለው መንገድ ነው።

በየት ዞረን ሼመንደፈሩ፣ ታሪካዊው ባቡር ጣቢያ ጋር እንደደረስን አላቅምም። የአፄ ምኒሊክና የፈረንሳይ ደማቅ አሻራ የታተመበት ሼመንደፈሩ ኢትዮ-ጂቡቲን ያስመለከቱ በርካታ ፖለቲካዊ ማኅበራዊና ስነ-ልቦናዊ ምስጢራትን ተሸክሟል። የባቡር ሃዲዱን ይዘህ ስትጓዝ ባንድ አቅጣጫ ወደ ወደቡ በተቃራኒው ደግሞ ወደድሬ ትጓዛለህ።

ስለጂቡቲ ያያቶቻችን ርስትነት የሚያመለክቱ ግን አንጀት የሚያሳርሩ ጠጣርና ተጨባጭ እውነታዎች አሉ። ጂቡቲ ካስራ ሁለተኛው እስከ አስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን በኛው ሱልጣኖች ነበር የምትተዳደረው። “ይህቺን ውብ አገራችንን ምን ልክፍት ምን ክፉ ቀን ከመዳፋችን አወጣት?

አፄ ምኒልክ ለምን ለ99 (100) ዓመት ጂቡቲን በኪራይ (lease) ለፈረንሳይ ሰጡ። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴስ በዚያ ደማቅ ክብርና ተሰሚነታቸው ተጠቅመው ጂቡቲንም ወደ እናት አገሯ ለምን አልጠቀለሉም?

የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዚደንት ጓድ መንግስቱ ኃይለማርያምስ የጂቡቲ ሪፈረንደም ከመካሄዱ ከሁለት ዓመታት በፊት በ1975 ዓም (በፈረንጆቹ አቆጣጠር) ላይ ለምን ኢትዮጵያ በጂቡቲ ላይ የይገባኛል ጥያቄ የላትም ሲሉ ወደ ጓዳችን ሊመለስ ይችል የነበረውን ሲሳይ ቸለል አሉት? ጥቅስ አበዛህ ካላልከኝ "Ethiopia had historical claims over Djibouti, but in 1975, the new military government of Ethiopia officially declared that it had no claims over the territory."

እነዚህን እንቅልፍ የሚያሳጡ ጥያቄዎች ላንተው ልተውልህና ክልኤቱ ልበልህ።

ቆይማ አንዴ ታገሰኝ። ዓመት አላወራ! እንቅልፍ ከነሳሁህ አይቀር አንድ የጭን ቁስል ላክልልህ የጂቡቲን ታሪክ ቅደም ተከተላዊ አካሄድ ስትመረምር የሚከተለውን ታገኛለህ። "1892 - Djibouti becomes capital of French Somaliland. 1897- Ethiopia acquires parts of Djibouti after signing a treaty with France." እንግዲህ ጥንት ብቻ ሳይሆን ከረፈደም ወዲህ የ ፈረንሳይን የሊዝ ኮንትራት ተከትሎ የጂቡቲ የተወሰነ አካል በኢትዮጵያ ይዞታ ስር ሰንብቷል ማለት ነው።

እንዲያውም የሆነ ንባብ ላይ አገራችን በምስጢር ከፈረንሳይ ጋር ያደረገችው ስምምነት እንደነበር አስታውሳለሁ። ስምምነቱም ፈረንሳይ ኮንትራቷን ጨርሳ ስትሄድ ጂቡቲን ሙሉ ለሙሉ ለኢትዮጵያ እንደምታስረክብ የሚያረጋግጥ ምስጢራዊ ሰነድ ነበር። እንግዲህ ይህን ምስጢራዊ ሰነድ የት ወይም እንዴት ልታገኘው እንደምትችል ያንተው የቤት ስራ ይሁንልኝ።

## ክልኤቱ

ፈረንሳይ ጀምራ ያልጨረሰቻት አገር ስልህ የከተማዪቱን ውበት ፅዳትና አጠቃላይ የኢንፍራስትራክቸር ይዞታ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። የባራሴራንቦን ቅራንቅንቦ የቤካዱስን የደካከሙ ቤቶችና አቧራማ ቆሻሻ ጎዳኖች መመልከቱ ብቻ ጂቡቲ ከፍተኛ የከተማ ልማት የሚያሻት አገር መሆኗን ትረዳለህ።

ዱባይን ዓለም አቀፍ ዘመናዊ መዲና ያደረጓትን ዓይነቶቹን ቱጃር አልሚዎችና መሃንዲሶችን ተወት አድርገህ ምነው የኢትዮጵያ የሪል እስቴት ሰዎች ጂቡቲን በቃኟት ብለህ ትመኛለህ። ያውራ ጎዳና ባለሙያዎቻችን ወደጂቡቲ ቢዘልቁ ያቺን አገር ከመንገድ ድህነት ተርታ ነፃ ያወጧት ነበር ብለህ ታስባለህ።

በመዲናዪቱ እምብርት ላይ ከሾላ ገበያ ያነሰ ግን አጠቃላይ ድባቡ እጅግ ኋላቀር መገበያያ መንደር አለ። ፍየሉና ሰዉ እኩል ይጋፋል። ጭቃ ባይኖርም አቧራና ቆሻሻ አይን ያታክታል።

የገበያው አጠቃላይ ድባብ የሐረሩን ሸዋበር ይመስላል (የድሮውን ማለቴ ነው) ። እነ ጀለቢያ፣ ሸበጥ፣ ሽቶ፣ እርድ፣ ጫት፣ የእቃ ቤት ቁሳቁሶች ደመቅ ብለው ዓይንህ ይገባሉ። እንደ ሽቶና፣ የእጅ ስልክ፣ ሬዲዮ፣ ፎጣ፣ ሳሙና፣ ሲጃራ፣ ብርድልብስ ወዘተ... ያሉ ከጠረፍ የሚመጡ የኮንትሮባንድ እቃዎችም የሐረር(ሸዋ በር) ትውስታህን ይቀሰቅሰዋል።

ገበያውን ካነሳሁ አይቀር እዚሁ ገበያ ለመሸመት የመጣ ጎራ ሳይል የማይመለስባትን አሳ ቤት ሳላነሳ ማለፍ ተገቢ አይሆንም። ባንድ ጎኑ በቢላ ተቆርጦና ልክ እንደመፅሐፍ ተዘርግቶ እንደበቆሎ የከሰል ምድጃ ላይ የሚበስለው ጥብስ አይን ያጓጓል ሆድ ያጮሃል።

የአሳው አጠባበስ ለየት ስላለብኝ  ወደ ጓዳ ጎራ ብዬ ነበር። ረጅም የብረት ዘንግ የያዘው ሼፍ
“አሰላም አሌኩም አለኝ” አለኝ የቅንድቦቼ አበዛዝ
“ወአሌኩም አሰላም” ብዬ ባህላዊውን የአሳ አጠባበስ ለማየት ያለኝን ጉጉት ሳላሳብቅ ወደ ውስጥ ዘለኩ። ምድጃው እኛ አገር እንደምናየው ከላይ ጉብ ያለ አይደለም።  መሬት ውስጥ ከሁለት ሜትር ተኩል እስከ ሶስት ሜትር በሚደርስ ጥልቀት ላይ የተሰራ ነው።

ጥሬው አሳ ወደ ምድጃው የሚጨመረውም ሆነ ሲበስል ከማንደጃው የሚወጣው በረጅም የብረት ዘንግ ላይ ተሰክቶ ነው። አሳው የከሰል ምድጃ ላይ ስለሚበስል ለተስተናጋጅ ሲቀርብ  ትናንሽ የከሰል ፍሞች ሊኖሩት ይችላል። እፍ እፍ እያልክ ትበላለህ። ጀርም ያለው ጀርመን አገር ነው አትለኝም? የማድቤቱ ሰራተኞች በሙሉ ወንዶች ናቸው። አስተናጋጆቹ ደግሞ ሴቶች።

አሳ ቤቷ በራሷ ሚጢጢ ገበያ ትመስላለች። ባለ ቁምጣ፣ ባለ ጀለቢያ፣ ባለ ሂጃብ፣ ባለ ሸሚዝ... ጠባቧ ምግብ ቤት በላቦት፣ በሙቀትና በጨኸት ትጨናነቃለች። የደራ ገበያ አላት።

ጂቡቲን ዓለምአቀፉ የገንዘብ ድርጅት ከድህነት በታች ከሚማቅቁ አስር የአፍሪካ አገራት ተርታ ከዘንድሮው ምደባው ቢያወጣትም አገሪቱ በኑሮ ውድነት ከሚታመሱ ያፍሪካ ሃገሮች የመጀመሪያዋ ናት የሚል ተደጋጋሚ ሃሜት ሰምቼ ስለነበር ይህንኑ ለማረጋገጥ ጉግሌን ብጎለጉል በፌታውራሪነት ለኑሮ ውድ ተብላ የመጣችልኝን አገር አትጠይቀኝ። በሹክሹክታ ልንገርህና የኛው ሙሽሪት ናት - አቢሲኒያ ።

ወደ ጂቡቲ ስመልስህ ከአልጄሪያ በስተቀር ፈረንሳይ የገዛቻቸው ያፍሪካ አገሮች በሙሉ በድህነት እንደሚማቅቁ በዚያው አገር የተዋወኩት አንድ ወዳጄ አወጋኝ። ፈረንሳይ ወዳም ሆነ ተገዳ ጓዟን ቀርቅባ ካፍሪካ ስትወጣ ምናልባት ቋንቋዋ እንዲስፋፋ የየትምህርት ቤቱን ካሪኩሉም የፈረንሳይ አፍ ቅኝት እንዲኖረው ስትራቴጂ ቀይሳ ይህንኑ በገንዘብም በሰው ኃይልም ትደግፋለች እንጂ ይሄ ነው የሚባል ሌላ እርዳታ አታበረክትም።

እንደሌሎቹ ፈረንሳይ ገዛ አገሮች ጂቡቲንም ዞረህ ብታያት ወደ እድገት ጎዳና ለማምራት ዘመናትን የምትፈልግ አገር መሆኗን ትረዳለህ። ባጠቃላይ በርካታ የኢፍራስትራክቸር ችግሮች አሉባት ብልህ ምንም ማጋነን የለውም።

ቻይና። አ ቻይና! በሌሎቹ ያፍሪካ አገሮች ላይ ያየሺውን ፀጋ በጂቡቲ ላይ እንዳትመለከቺ አይንሽን ምን ጋረደው? የሚል ሃሳብ ሊመጣብህ ይችላል ግን እማሆይ ቻይና በጠባብ ዓይኖቿ የጂቡትን ወደብ አስተካክላ የተመለከተችው መሆኗን የምትረዳባቸው ጥሬ እውነታዎች አሉ። ምሳሌ ጥቀስ ካልከኝ የጦር ቀጠናዋን (Military base) ተወውና በቻይና ፊታውራሪነት በከፍተኛ ምስጢር የሚገነባውን አዲሱን የዱራሌ ወደብ ልጥቀስልህ።

ለረጅም ጊዜ ለኢትዮጵያ ግልጋሎት ይሰጥ የነበረውና እስከ ዳርቻው ድረስ ባቡራችን የሚዘልቅበት አሮጌውና ታሪካዊው ግዙፍ ወደብ ታሪክ ወደመሆን ግርጌ እየተንሸራተተ ያለ ይመስላል።

የሚገርመው ነገር ፈረንሳይ እና ቻይናን ጨምሮ  እነ ዩናይትድ ስቴትስ፣ እነ ጀርመን፣ እነ ሳውዲአረቢያ፣ እነ ስፔን፣ እነ ጥልያን፣ እነ ጃፓን በሙሉ በጂቡቲ የጦር ቀጠና ገንብተው ጡንቻቸውን መወጣጠር መያዛቸው ነው። ይህ የመንደር ጎረምሶች ጉልበት የመፈታተሽ አባዜ በኑሮ ውድነትና በኋላ ቀርነት  የምትማቅቀውን ጂቡቲና አጠቃላይ ያፍሪካ ቀንድ አገሮች ወደ እድገት ጎዳና እንዲያቀኑ ይረዳል ወይስ የግጭት መጠንሰሻ የስጋት ወረዳ ያደርጋቸዋል? ይህንንም ላንተ ልተውልህና  እንቅልፍህን አጥተህ ተጨነቅበት።

ይልቅዬ በተርታ ሰው እይታዬ ስላገሪቱ ከታዘብኳቸው ገራገር ምልከታዎች ትንሽ ልጨምርልህ። ጂቡቲ ፈረንሳይ ጀምራ ያልጨረሰቻት አገር ስልህ እንዲሁ የቆሻሻ ክምር ውስጥ እየተፍገመገመች ያለች ተስፋ ቢስ ቀጠና ናት እያልኩህ አይደለም። ጂቡቲ የተሻሉና ትላልቅ የገበያ አዳራሾችም አሏት በተለይ ባዋዲ ሞል (Bawadi Mall) እጅግ ዘመናዊ ና ሰፊ ህንፃ ውስጥ ይገኛል። ሞሉ መግቢያ ላይ ከሺ በላይ ተሽከርካሪዎችን የሚይዝ የመኪና ማቆሚያ (ፓርኪንግ) አለው። ወደ ውስጥ ሲዘልቁም ዓለማችን የያዘቻቸው ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ የቤት ቁሳቁስ፣ የቢሮ እቃዎች፣ ሞባይል ስልኮች፣ ላፕታፖች፣ አልባሳት ወዘተ... ተትረፍርፈው ይገኛሉ። ጂብ ሳርዲንም (Djib Sardin) ከባዋዲ ባይስተካከልም ጥድት ያለና ዘመናዊ የገበያ አዳራሽ ተብሎ የሚመደብ ነው።

ሌላው የመዲናዪቱ ትልቁና ደረጃውን የጠበቀው ባለአምስት ኮከብ ሆቴል የቀይባህርን ግርጌ ተስታኮ የተሰራው ፓላስ ኬምፒንስኪ ነው። የሆቴሉ አጠቃላይ ድባብ ከነ ቅንጡ መስተናገጃው ምድራዊ ገነት የሚመስል ነው። ተስተናጋጆቹም ያገሪቱ ዜጎች ሳይሆኑ ያሜሪካ፣ ያውሮፓና የእስያ ወዘተ... ሰዎች መሆናቸውን ዓይንን ጨፍኖ ሳይቀር ማየት ይቻላል። እንደ ሼራተን ጂቡቲ፣ አይላ ግራንድ ሆቴል፣ ራስ ዲካ ያሉ ባላምስት ኮከብ ሆቴሎችም ጂቡቲን ምድራዊ ገነት አስመስለዋታል።

እየረፈደ ነው። እንዴ! አረ እንዲያውም ወዳገሬ መሳፈሪያዬ ሰዓት አልደረሰልህም? ሽማግሌዎቹን ልሰናበት በሚል ሰበብ ያቺን ጠይም ቆንጆ ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ ኮሙኒቲ አቀናሁ። ልጅቱ የለችም። ጉባኤው ግን እንደተሰየመ ነው።


“ይቅናህ!
“ሰላም ግባ!
“እመ ብርሃን ትከተልህ!”
ጠይሚቱ ግን የለችም። ምናልባት ያኔ እዚያ የተከሰተችው ሌላ ሰው ተክታ ልትሰራ ነበር? ወይም ከስራ ተባራለች? ወይም አገር ቀይራለች? ወይም አዲስአበባ፣ ድሬዳዋ፣ ወሎ ዘመድ ጥየቃ ዘልቃለች?
ወይም ሮቢላኑ ሳያመልጠኝ ታክሲ ተሳፍሬ ወደ አውሮፕላን ጣቢያው አመራሁ።

ምርትና
አግልግልዎትዎን
ያስተዋውቁ!




bayradigital@gmail.com

# ሰፈድ



(ሐና አበበ)

ማመን
መፍራት
መድፈር
ማፈር
ማ-አፈር?
ማን ይሙት
ማን ይሁን አፈር
(ሺ አመት አይኖር)
???

መልሶ መጀገን
ትንፋሽ መዝገን
መሣቅ
መስጠም
መሄድ
መኩራት
ደሞ የነሎጥ ፍርሃት
(ትናንትስ?)
???

ማለም
ምናብ ማቅለም
መክነፍ
በአላዷን ምንጣፍ
ድንገት
አንዳች ሲዶፍ
ደሞ
ቁልቁል መክነፍ
እርፍ
እተነሱበት ደጃፍ
(ነገስ?)
???

መግለጥ
መጥበርበር
የጨረር አቅም ሲከር
መንቃት
እስኪዋሃዱ መብቃት
መውረድ
እስኪያካፍሉ መናድ
መፍረስ
ከነፍስ ጥጋት መድረስ
(አሁንስ?)
ማመን
(አሁን?)
እመን።

# አዕዋፋት እና ካፈቾዎች



(ዙፋን ክፍሌ)

*"ገመና ከታቹ የሳር ቤት ያማረሽ*
*ምሥጢረ መለኮት ማነው ያስተማረሽ*
*የሳር ኪዳን ጎጆ መሬቱን ፈልፍሎ*
*ከሰማይ ቤት ዕጣሽ ማን በሰጠኝ ከፍሎ"*

ከፋ (ካፋ፥ ካፈቾ) ከጥንታውያን የጎንጋ ቤተሰብ (Gonga Families) ከሚባሉት ሕዝቦች (ከፋ፣ ሸካ-እናርያ፣ ሽናሻና የም) መካከል አንዱ ነው። ጎንጋ ባሁኑ ጊዜ በአገራችን የተለያዩ ክፍሎችና አቅጣጫዎች ተበታትኖ ይገኛል። ከፋና ሸካ ባገራችን ደቡብ ምዕራብ ክፍል ይገኛሉ። ዛሬ ስለ ከፋዎች ነው ልነግራችሁ ያሰብኩት።

## ስለ ከፋዎች እና ስለ አዕዋፎቻቸው

ከፋዎች እና ተፈጥሮ ያንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ከዛፉ፣ ከወፉ፣ ከወንዙ፣ ከላሙና ከበሬው ይግባባሉ። ቋንቋ አላቸው። በሬዎቻቸውና ላሞቻቸው ስም አላቸው። ስም አወጣጡም ብዙውን ጊዜ የከብቱ የቆዳ ቀለም ላይ በመመስረት(ቦቃ፣መጋላ...ወዘተ አይነት) ነው።

በስም ጠርተው "ሃእ፥ሃእ - እንካ፥እንካ (እንች፥እንች)" ብለው መዳፍ ሲዘረጉ ስሙ የተጠራው ከብት ሰተት ብሎ ሲመጣ ማየት አጀብ ያሰኛል። አንዳዴ ከብቱ ጌታውን ሲያይ ብቻ ስሙ ሳይጠራ ይመጣል። የመጣውን ከብት(ላም/በሬ) አሞሌ ያስልሱታል።

አሞሌ ቢያጡ ግራዋ ቀጥፈው ያበሏቸዋል(ግራዋ ከብቶችን የማይማረረው ለምንድነው? ምሬቱን ይሆን ሚወዱት? ተፈጥሮ ወጥ የሆነ ምላስ የላትም? ይኸው ይመስለኛል የስሙርነቷና የመቀጠሏ ምስጢር) ግራዋም ከታጣ ከብቱ ትናንት የበላበት እጅ ነውና ባዶ መዳፍ ይልሳል። ባለቤትየው ቁጭ ያለ እንደሆነም የጌታውን ራስ ይልሳል(በላብ መልክ የወጣውን ጨው ይሆናል...?)። አለ ጌታው የማይጠመድ በሬ፣ የማይለጎም ፈረስ፣ አለእመቤቷ የማትታለብ ላም አሉ።

ከፉ ተወልደው ያደጉ በሬዎች ቋንቋ ያውቃሉ። "ዬሻሻ..አማህን ታዶኖ - ቁምማ ጌታው፣ አትሂድ ጎበዜ..." ሲሏቸው ቀጥ ይላሉ። በሬው እያረሰ ያዳለጠው፥የወደቀ እንደሆነ ገበሬው እንደሰው "ታድህቦን ታዶኖ - እኔ ልውደቅ ጌታው" ይለዋል ። በሬውም ይሰማል ይኼን። ያውቃል ይኼን።

ከተራራው፥ከጋራው - ከወጠጤው፥ከአውራው፣ ከዛፉና ከሐረጉ - ከጎባጣው፥ከዝርጉ፣ ከ አድባርና ከደብሩ - ከአዝመራው፥ከመኸሩ፣ ከክረምትና ከበጋው...ከዝናብና ፀሐዩ፣ ከበልግና ከጸደዩ፣ ከሰኔና ከነሐሴ ከመስከረምና አደዩ... ወዘተረፈ ያላቸውን ቁርኝትና ቋንቋ ካነሳሁ ''...ብዙ ቢያወጉ ይዘነጉ '' እንዳያስብልብኝ ቶሎ ወደ ተነሳሁበት ልመለስ። ከፉና አዕዋፍ።

# ፫. ካፌ (ካፎ - ወፊት) ወፍ - ያፍ

"እህህህ ወፊቱ..እህህህ ወፍዬ
  እህህህ ወፊቱ..እህህህ ወፍዬ"

ከፉዎች ወፊት ከፉ እንደሆነች ያምናሉ። በፍጹም ያምናሉ። በአፈታሪኮቻቸውም ሆነ ዛሬ ባሉት ከፉዎች ዘንድም ወፊት ቋንቋዋ ከፍኛ እንደሆነ ያምናሉ። ቢያንስ ከፉ ውስጥ ያለች ወፊት ከፉ ናት።

በወፍ ያስተነብያሉ። ያስተነትናሉ። ይተነትናሉ። ወፊትን ያምናሉ። መንገድ ሲወጡ፣ ከዳኛ ዘንድ ነገር ሲኖራቸው፣ የያዙትን እኩይ መክያ(በትር፣ጦር፣አንካሴ) ክረምት እንደሆን መሬቱ እንዳያዳልጣቸው እየተመረኮዙ፣ በጋ እንደሆን እትከሻቸው አጋድመው በሃሳብ ተውጠው ጭልጥ ብለው ዱሩን እየጣሱ ድንገት የዱር ወፍ ከሃሳባቸው ታናጥባቸዋለች...

"ዴተ ገት ፥ ወድተ ገት፣ ሻታህን! - በጀልኝ በል ፥ አማረ በል ፥ ሰመረ በል -አትፍራ!"

ይኸንን ያለችው እንደሆነ ጮቤ ይረግጣል። ወፊት ከፈጣሪ ዘንድ የተላከች መላክተኛ እንደሆነች ያምናል። ወፊትን ሰምቶ ዝም አይልም። የሱ መልስ አለ :-

*"ነ ኩቾ ጠባያ፣*
*ነ ቡሾ ቅታያ፣*
*ሻትያነ ዬርን ግበነሆ -*
*ጎጆ ይስፉሽ*
*ሜጬት አይሙትብሽ*
*አዎን አልፈራም እግዚአብሔርን እታመናለሁ " ይላታል ።*

*“ሻት፥ሻት፥ሻት፥ሻት - ፍራ፥ፍራ፥ፍራ፥ፍራ”*

ይኽን ያለችው እንደሆነ ከወጣበት መንገድ ይመለሳል። ይፈራል። ያሰበው እንደማይሳካ እንደማይቀና ያምናል። ወፊት ይኽን ያለችው እሱ ምንም ሳያስብ ከሆነም ምን ሊመጣብኝ ይሆን እያለ ይሰጋል።

ከላይ ያልነውን ብስራትም ሆነ መርዶ ወፏ እየደጋገመች ሰውዬው እየተራመደ ከሆነና እየተከተለች የምትለው ከሆነ ሰውዬው ነገሩ(መልዕክቱ)ትንቢቱ ለርሱ መሆኑንና ቁርጥ ወይም ዕሙን መሆኑን ያምናል።

# ፪. መቸኮ

በከፍኛ “መቸኮ” የሚባለውን ወፍ ድምፅ እንጂ መልኩን አይቼ ስለማላውቅ የወፉን መልክና ስም ለይቼ አልነግራችሁም። እንድትገምቱት ግን ድምጹና ዝማሬውን በአማርኛ ሲያደምጡት “መሸኮ” የሚል ቃናና ድምጸት አለው።

ስለዚህ ወፍ የሚነገር የከፋዎች አፈታሪክ አለ። ፈጣሪ ለሁሉም ፍጡራን ሚስት ያድል ነበር አሉ። (በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ትውፊት ውስጥ ሔዋን ገና ሳትፈጠር አዕዋፍ ለእያንዳንዳቸው ከተሰጧቸው ከእንስታቸው ጋር ሲጫወቱ አዳም አይቶ እንደቀና የሚነገረውን ልብ ይሏል።) እና ለሁሉም ተባዕት ሚስት ስትታደል መቸኮ ለሚባለው ወፍ የደረሰችው ሚስት ፋንጋ ነበረች ይላል የካፊቾ ሚት (myth)። መቸኮ ተበሳጨ። “እምቢ አልፈልጋትም” አለ።

“ተወዋ!” አለና እግዜር ሚስቱን ንስት፣ ክልክል! ይኸው እስከዛሬ “መቸኔ፥መቸኮ - አወየው ሚስቴ-ሚስትዋ…” እያለ እየጮኸ እየተጸጸተ ይኖራል ይላሉ። ከእግዚአብሔርና ከተፈጥሮ የሆነ ሥጦታ ልክ ነው። ፍጹም (Absolute) ነው ለማለት ማጀቢያ የሚያደርጉት ተረክ ነው። ተረትም እውነትም።

በቅንፍ፡-
(ያው ተረት አናቆርፍድ ብለን እንጂ “ሚስት ከሌለችው ማንን ተኝቶ ከማን ወልዶ ዘሩን ተክቶ ኖረ?” ብለን እንጠይቃለን። በዛውም ላይ መቸኮ በሚለው ቃል ውስጥ መቸ (ቼ) ማለት ሚስት ቢሆንም ኮ (ኮ - Koo) የሚለው የኔነት (Possession) አመልካች ተቀጥላ ጥቅም ላይ የሚውለው በኦሮሚኛ እንጂ ከፍኛ ውስጥ መኖሩን አላውቅም።)

# ፫. ኡጌ - እርግብ - ርግብ!

ከአዕዋፋት ገራገርና የዋህ ብንባል እርግብን ቀድሞ የሚመጣልን ያለ አይመስለኝም። በወንጌልም "እንደ እርግብ የዋሖች ሁኑ ፤ እንደ እባብ ልባሞች ሁኑ" ተብሏል። እባብ ብል ትዝ ያለኝን "የከፋ - የእባብና - የወፍ" ነገር ነግሬአችሁ ወዳነሳነው የ "እርግብና ከፋ" ወግ እንመለሳለን። እንደ እርግብ ገራገርና የዋሕ የሆኑ ከፋዎች እንዴት እንደ እባብ ልባሞች እንደሆኑ እዩ። ተመልከቱ።

ወፍ ጎጆ ትቀልሳለች። ጠላቷ እባብ ነው። ስለዚህም ከጥቃት ራሷንና እንቁላሏን ለመከላከል ስትል ዘዴ ትዘይዳለች። ይኸውም ማሳሳቻ ሐሳዊ ጎጆ (pseudo nest) መቀለስና እንቁላሏን ግን በድብቁና እውነተኛው ጎጆ ውስጥ መጣል ነው። በዚህም ከጠላት (በተለይ እባብ) ታመልጣለች።

ከፋዎች በርሷና በእባብ መካከል ያለውን ጥላቻ ስለሚያውቁ አረንጓዴነቱ ያልጠፋ ልጥ በብዙ መንገድ ከገላው አንስቶ እስከሌላው ነገር እባብ እንዲመስል አድርገው የወፏን ጎጆ ይጠመጥማሉ። ወፏ ወደ ጎጇዋ ስትመጣ እባብ (ልጥ ወይም ሌላ ከእባብ የተገናኘ ምልክት ዳና...) ስታይ ዕጽ እየበጠሰች ታመጣለች። እሱን ዕጽ (ለምሳሌ ዕጸ ዜዌ ቢሆን...) ዘሩን ዓይነቱን ለይተው መርምረው ያጠኑታል። ታዲያስ እንዲህ አይደል እንደ እባብ ልባም መሆን!

ንግባዕከ ሀበ ጥንተ ነገር.. ወደ እርግብ እንመለስ። እርግብን በከፍኛ ኡጌ (Ugge) ይሏታል። ይህች ገራገር ወፍ የምትዘምረው ዝማሬ (የሌሎች ወፎች ዝማሬ እንደ ክራር - የእርግብ ዝማሬ እንደ በገና ነው) በከፋዎች ዘንድ ተቀድቶ ተተርጉሞ ግጥም ተገጥሞ ይዜማል። ይዘመራል።

"እቴሜቴ...የሎሚ ሽታ" ስትሉ ኢትዮጵያውያን ሕጻናት ባንድነት እንደሚቀበሏችሁ ሁሉ የከፋ ገጠሮች ኼዳችሁ "ጉድች እንዴ ታንዴ..." ብትሏቸው በፍጹም ሃሴት ሆነው "ቡሼ ከኖ ዋቴ...ገሜ እከ ሸቄን ኡሽ ገደ ባጬ..." እያሉ ይቀበሏችኋል።

ዜማው የሚወርደው እርግቧ ራሷ በምታዜምበት ስልት ነው። ራሱን። ግጥሙ ደሞ እሷ በድፍን ያለችው ተፈትቶ፤ ተገስሶና እሷን አብነት አድርጎ በሰው አፍ ተገጥሞ ነው።

የከፋ እርግብ የሕጻናት ዝማሬና ዜማ ናት። አሳዳጊያቸው ነች። የመንፈስ ሞግዚት። በተቀዳ ሲዲ ሳይሆን በተፈጥሮ አፍ። በርግብ እምምታ ነው የከፋ ማቲዎች የሚያድጉት።



# ፬. ዩዬ (ዶዮ)፣ ኑቶ -ጉጉት

ጉጉቶች ብርሃን ሲቀንስ በደምብ ያያሉ። ስለዚህ የሌሊቱን ክፍለ ጊዜ ይጓጓዙበታል። ታዳኛቸውን በድምጽ ለይተው ደርሰው ለቀም የሚያደርጉ እነዚህ ሥጋ በል ወፎች ሲማታና ሲክነፈነፍ ድምጽ የማያወጣው ክንፋቸው በረጭታ እንዲበሩ ያደርጋቸዋል።

ከ ስያሜዋ ስንነሳ ከፋዎች ለወፏ የሰጡት ስም ድምጸ ቀድ ይመስላል። “ፏ.. “ የሚለውን ውኃ ፏፏቴ እንደሚሉት ሁሉ “ዩ (ዪ? ፤ ው? ፤ ኡ?) “ የሚል መነሻ ድምጽ የሚወጣትንና በከፋዎች ዘንድ በደግ የማትነሳውን ጉጉት “ ዩዬ “ ያስባላት ይመስላል። “ ዶዮ ፤ ኑቶ “ የሚሉት አጠራሮች ጉጉት ወፍን በወንድ አንቀጽ ሲጠሩት ከሙት መንፈስነት እና በካፋዎች ዘንድ ካለው የጉጉት የሞት ጠሪነት ተረክ ጋር ይያያዛል።

ጉጉት በጥንታዊያን ሚቶሎጂዎች ውስጥም ጎልታ ትነሳለች። በጥንት ግሪክ የ ጉጉት ወፍ በቅርብ መኖር የአቴናን ጥበቃና መልካም ዕድልን ያሳያል። ከሞትና ሙታን ጋር ጉጉትን በማያያዝ ለካፋዎቹ ተረክ ቀረብ ብሎ ጉጉትን በደግ (Positively) በማንሳት ከካፋዎቹ ተረክ ፈቀቅ የሚለው የግብጾች Myth፣ ድኅረ ሞት ባለው ሕላዌ ውስጥ የሙታንን ነፍሳት እንደሚጠብቁ ይወሳል።

የጥንት ሮም ስነ ተረት ግን ከዛሬዎቹ ካፋዎች ተረክ ጋር አብሮ ይኼዳል። ይጫፈራል። በሁለቱም እምነት ጉጉቶች የሙት መናፍስት እና የክፋት መልእክተኞች ናቸው። ካፋዎች ለጉጉቶች የሰጡት “ ዶዮ ፤ ኑቶ “ የሚሉት ስሞች በቀጥታ የሚገናኙት ከዚህ ተረክ ጋር ነው።

እናም ወፎችን ካፍኛ የሚያናግሩት ካፌቾዎች ጉጉት በካፍኛ ምን ብትላቸው ነው የጠሏት? “ ዩ፣ ኮቾን ትቀቦት? ~ ዩ ፤ የማንን ልቀፍ ? “ እያለችን ይሏችኋል። “ዩ...” የዚህች የሞት መላክተኛ ወፍ ዜማ ማንሻ ስትሆን “ የማንን ልቀፍ? ‹› ማለቷም እንደ ዉሻ ማላዘን ያለ የመጥፎ ገድ ምልክት (bad omen) እና የሞት ጥሪና ሟርት ነው።

የጉጉት ዜማ (hooting) የምሽት ዜማ መሆኑ ላይ ወፈር፣ ደርበብ፣ ጫን ማለቱ እውነትም ያሸብራል።
ጉጉት “ የማንን ልቀፍ? ‹› ስትል ካፋዎች “ጉልቻ አቀፊ! “ እያሉ በመራገምና የአምላካቸውን ስም እየጠሩ በመጸለይ የዚህችን የሞት መላክተኛ ወፍ ሟርት ያከሽፋሉ። የዶሮና የከፋዎችን ነገር እናውጋና በቃን።

# ፫.ባኮ- ዶሮ - ዶርሖ

አዕዋፍ ሁለት ምድብ ናቸው። አዕዋፍ ዘቤት(የቤት ወፎች ፣ እነዚህም ዶሮዎች ናቸው) እና አዕዋፍ ዘአፍዓ(የውጭ ፥ የዱር ወፎች ፣ እነዚህም ከሚበሉት ወገን ቆቅና ጂግራ... እና ሌሎች እማይበሉ አሉበት...) ተብለው ይከፈላሉ በግዕዙ የሥነ-ፍጥረት ትምህርት።

## ፫.፩ ቆቅ

"እህህ.. ፈጣሪዋን አምና እህህ.. ያፏን ጥሬ ዘርታ፣
ለጭሮ አዳር ውሎን በዝማሬ ወጥታ፣
አዳኝ እንዴት ያጥቃት ፍርድና ዳኛ አጥታ..? "

የከፋ ኮበሌዎች ጀብድ (adventure) የሚጀምሩት ቆቅ በማጥመድ ነው። ከዚያም በላይ ቆቅን ከማደሪያዋ አስነስቶ ስትበር እየተከተሉ አዳክሞ መያዝ ደሞ የጀብዶች ጀብድ ተደርጎ ይቆጠራል። ይኼ ግን ቆቋ በበረራ፣ አጥማጅ በሩጫ ስለሆነ ፉክክሩ ለቆቅ ይቀናታል። በባሕርይዋ አየር ላይ እየበረረች መቆየት አትችልምና ሲደክማት እምናምኑ ገብታ ኮሽ ሳትል ትደበቃለች። ይኼ ነው እንግዲህ ቆቅ ማጥመድን ብርቅና አስደሳች የሚያደርገው። አደይ ግውው ብሎ ሲያብብ ያን ጊዜ ቆቅ ትፎክራለች። ታሽካካለች። ታዜማለች።

የከፋ ገጠር ጠዋት ጠዋት ከሚጤሰው የደመና ተራራ፣ ካበበው አበባ፣ ከቡና ወቀጣ ድምጽ ጋር...የቆቅ ማሽካካት ሲጨመርበት እግዚኦ ማሕሌት!!!
ለአቅመ ማጥመድ ያልበቁቱ የቆቅ እንቁላል ፍለጋ ጢቱን ይሰማራሉ። ዕድለኛው ማቲ(አዋቂም ቢሆን) ደስታው የቆቅ ግማሽ ያህላል።

## ፫.፪ ከማጀዋ ቆቅ - ነገረ ዶሮ

በከፋዎች የኖረ ስርዓት ሴቶች ዶሮ አይበሉም ነበር። (ዛሬም ቢሆን በዕድሜያቸው ያለፈው ትውልድ አካል የሆኑትና በወግ አጥባቂው የከፋ ገጠራማ ክፍል ያሉ ሴቶች የዶሮ ስጋ አይበሉም። በቁጥር ግን ጥቂት ቀርተዋል።)

ታዲያላችሁ.. በኋላ ሴቶቹ ዶሮ መብላት ጀመሩ። ወንዶቹ በዘፈናቸው፣ በዝርውና በግጥማቸው ሴቶችን ሸነቆጡ - ተቆጡ። አወሩ። አሸሞሩ።

**ወንዶቹ ዘፈን መሃል እንዲህ ብለው ከሰሱ፡-**
**(በተቀራራቢ አማርኛ ስመልስላችሁ..)**

*"እረ ሴቶች ተበላሹ*
*ወይዛዝርት ተበላሹ*
*ዶሮ በሉ ቅቤ እያሹ።"*

**ወግ ጥሰው ዶሮ መብላት ያመጡት አፈንጋጭ ሴቶችም እንዲህ መለሱላቸው፡-**

*"ማን አባክ ሸንኩርት ልጦ?*
*ማን አባክ ቅቤ አቅልጦ?*
*እኛ እንጂ ብልት የበለትን-*
*እኛ እንጂ ላባ የነጩን*
*እኛ እንጂ ቆላነው ፈጩን፥*
*አዝሙድ አብሹን ቅመሙን*
*'በሉብን' ብላችሁ ታሙን?*

*እኛን እንጅ እሳት የፈጀን*
*እሰየው እንኳን አበጀን*
*እሰይ እንኳን ተበላሸን*
*ዶሮ በላን ቅቤ እያሸን"*



**የሴቶቹ አብዮት ጸንቶ የዛሬዎቹ የከፋ ሴቶች(ከላይ ካልናቸው ጥቂቶች በቀር) ብልት ተቀራማች ሆነዋል። እውነትም እሰይ አበጁ!**
**በዚህ ይብቃን።**

**በአያ ሙሌ የነፍስ አድርስ ብዕርና በአበበ ተካ ጉሮሮ ልሰናበታችሁ ፡-**

*"...ኸህህ..ምነው ባደረገኝ ኸህህ.. የሷ ጋሻ ጃግሬ*
*እንደምንም ብዬን እኔም ጥሬ ግሬ*
*ያገዳ ጎጆዬን ባቆምኳት ማግሬ...፤*
*---*
*ገመና ከታቹ የሳር ቤት ያማረሽ*
*ምሥጢረ መለኮት ማነው ያስተማረሽ*
*የሳር ኪዳን ጎጆ መሬቱን ፈልፍሎ*
*ከሰማይ ቤት ዕጣሽ ማን በሰጠኝ ከፍሎ...*
*--------*
*ኸህህ.. ፈጣሪዋን አምና ኸህህ.. ያፏን ጥሬ ዘርታ፣*
*ለጭሮ አዳር ውሎን በዝማሬ ወጥታ፣*
*አዳኝ እንዴት ያጥቃት ፍርድና ዳኛ አጥታ..*
*-------*
*ታማ ትንፋሽ አጥታ ደክማ ስታጣጥር*
*ማን ያቃናት ይሆን ውለታ ሳይቆጥር..!?*
*ኸህህህ ወፊቱ..ኸህህህ ወፍዬ*
*ኸህህህ ወፊቱ..ኸህህህ ወፍዬ"*

**ድጎ ቱነባ- ሠናይ ለክሙ!!**

# እኔና ቤቴ ግን ውበትን እናመልካለን



(ሮሐ ናትናኤል)

*“ማምለክ የማያስፈልግ መስሎ ከታያችሁ ግን፣ የቀድሞ አባቶቻችሁ ከወንዙ ማዶ ካመለኳቸው አማልክት ወይም በምድራቸው የምትኖሩባቸው ያፌታዊያን ከሚያመልኳቸው አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን ውበትን እናመልካለን።”* **መፅሐፈ ቁንጅና** 25÷15

**አንድ ቀን እኔ ለሁለት ተሰንጥቄ ነበር....አንዱ እኔ ጠያቂ አንዱ እኔ መላሽ**

**እኔ 1:- ጥበብ ጥበብ ማለትህ (*መቼ ነው እንደ ሰው ኮንኮላታ ገዝቼ ከዚህ ጠሃይ የምገላገለው*) ስለምን?!....ጥበብ ምንድን?!**

**እኔ 2:- ጥበብ ጥበብ ማለቴ ለአምልኮተ ውበት (*ደንደሷ እንዴት ያምራል? ይች ጥንቅሽ ነገር*)፤ ለአፍቅሮተ ውበት**

**እኔ 1:- ው ው (*ምን አንቀለቀለው*) ው ውበት፣ ውበትስ ምንድን? ጥበብ፣ ውበት ምን እና ምን?**

**እኔ 2:- ነቃ ደንገጥ ብለህ ስማ (*ኡሁሁሁ አሁ ይሄ ጉንፋን አሁንስ ሊደፋኝ ነው*) ምንባቡን እንዲህ ነው....**



The Birth of Venus by Sandro Botticelli 1485-86

**ማሳሰቢያ**
**ቅንፍ የያዛቸውን የማይነበቡ ናቸው...ሀሳቡ ሲታሰብ ጥልቅ ያሉ ባዕድ ሀሳቦች እንደማለት**

# ውበት ምንድነው?!

**የ "ውበት ምንድነው?" ጥያቄ ለብዙ ዘመናት የፈላስፎች የማሰቢያና የመነታረኪያ ጉዳይ ከሆነ ይኸው እልፍ ዘመኑ። የፍልስፍና እእማደ ምስጢራት ከሚባሉ ውስጥም ይህ የውበት ጥያቄ**(aesthetics) **ከነ'**metaphysics**፣ ከነ'**ethics**፣ ከነ'**logic**፣ ከነ'**epistemology **ጋር የሚጠቀስ ነው። በፍልስፍና ውስጥ ነገረ ውበት በሶስት የዘመን ቅርፅ ተከፍሎ ሊተነተን ይችላል።**

## ፩. Classical theory of beauty

**ይህ ዘርፍ ውበትን** objective quality **ያለ፣ ሁሉንም የሚያስማማ ባህሪ እንዳለው የሚቀበል ሲሆን የውበት መገለጥም ከተጨባጭ መርህ የሚመነጭ ነው ብሎ ይሰብካል። በዚህ ዘርፍ የሚጠቀሱት የጥንታዊት ግሪክ ፈላስፎች የሆኑት ዝነኞቹ ፕሌቶና አርቶትል ናቸው።**

**ለፕሌቶ ውብት ማለት እውነት እና መልካምነት ነው። መልካም የሆነ ሁሉ ውብ ነው እንደማለት** (Beauty is a splendor of truth, the idea of beauty is the idea of good) **። ፕሌቶ ውበትን አርያም ወስዶ ይሰቅለዋል። ምድር ላይ የምናያቸው ነገሮች ሁሉ ጎዶሎ** (imperfect) **የሆኑ እና የትክክለኛው እውነት ነፀብራቅ ናቸው ብሎ ያምናል። ፕሌቶ ይህን ፍፁማዊ ውበትና እውነት፣ በልዕልና እና እውቀትን በመፈለግ የሚገለጥ ነው ይላል።**

**ሌላው የፕሌቶ ዘመን ተጋሪና ተማሪው የነበረው አርስቶትል መምህሩ ሰቅሎት የነበረውን የውበት ግንዛቤ ወደ ምድር ለማውረድ ይለፋል። ለአርስቶትል ውበት ማለት ስርዓት፣ ህብረት እና ምጣኔ ነው። ለአርስቶትል አንድ ነገር ውብ ነው የሚባለው የተስተካከል ቅርፅ እና የተሟላ ትርጉም የሰጠ እንደሆነ ነው።**

**አርትቶል እና ፕሌቶ አንዲት ኮረዳ ቢያዩ ጋሽ ፕሌቶ መልካምነቷንና ስነምግባሯን ሲመዝን፣ ልጅ አርስቶትል ደግሞ የአይኗን አቀማመጥ፣ የአፍንጫዋን አሰዳደር፣ የከንፈሯን ቅርፅ... ገለመሌ እያለ ሳይቆላው ይቀራል?! ሁለቱን ፈላስፎች በዚህ የውበት አረዳድ ስር እንዲካተቱ ያደረጋቸው ሁለቱም ውበት ቋሚ የሆነና ለአንዱ ውብ የሆነ ለሁሉም ውብ ይሆናል በሚለው አቋማቸው ነው** (objective beauty) **።**

## ፪. Romantic theory of beauty

ይህ ነገር መነሻውን ያደረገው 18ተኛ ክፍለዘመን መባቻ እና 19ኛ ክፍለዘመን መነሻ አከባቢ ነው። በጥንታዊው የውበት ብያኔ ላይ ማመፅ ተብሎ ሊቆጠር የሚችል እንቅስቃሴ ነው። ይህ የአስተሳሰብ ዘርፍ በዋናነት የሚገለፀው ውበትን subjective and individual experience በማድረግ ነው። በዚህ ጊዜ ውበትን objectively የሚተነትነውን ጥንታዊውን አረዳድ በመናድ subjective ወደ ሆነ የውበት ግንዛቤ ላይ ተደርሷል። በአጭሩ ለ romanticist ውበት እንደ ተመልካቹ ነው።

## ፫. Modern theory of beauty

ሰዎች የነገሮችን ውበትነት የሚገልፁበት ስልት ከማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖ የሚነሳ ነው ይለናል ይሄው ዘርፍ። ሀመር ውስጥ ጉብሉን እርቃነ-ስጋውን በከብት ጀርባ ላይ ያስሮጠ ውበት ወደ ሰሜን ቢኬድ ኡኡ የሚያስቡል ነውር ሆኖ ይገኛል። ይሄ የሚያሳየው የውበት ብያኔ ማህብረሰብ ነገሮችን ከሚረዳበት፤ አካባቢውን ከሚገነዘብበት፤ ለክስተቶች ትርጉም ከሚሰጥበት ጥቅል አስተሳሰብ የሚነሳ በመሆኑ ነው። ውበት እንደ ተመልካቹ(እንደ ግለሰብ) ሳይሆን ውበት እንደ ባህሉ ነው ብለን ዘመናዊን የስነውበት እሳቤ ልንገልፀው እችላለን። ው


## ክፍለ ውበታት

ውበት ሲባል የዜማውም ውበት፣ ስእሉም፣ የዛፉም፣ የእስሳቱም፣ የሴቱ፣ የወንዱ፣ የድንጋዩ(እማምላክን የሚያምር ድንጋይ አለ'ኮ ልክ ፊቴ እንደተቀመጠችው ሴት)፣ የወንበሩ፣ የክራንቹ የጨርቁ፣ የማብሪያ ማጥፊያው... ወዘተ የማረከን ቅራቅንቦ ሁሉ እንደ ሰነፍ ስልቻ የሚታጎርበት ቅጥ ያጣ ቃል ነው። ነገር ግን ውበት ሁለት አይነት ትርጉም ወይም የአረዳድ ከፍሎች ቢኖሩት ባይ ነን።

### ሀ) ጠቃሚ የውበት አይነት (beauty quite useful)

ተፈጥሮን ስንቃኝ አዋፋቱ፣ ተክሎቹ፣ አራዊቱና ሕይወት ያላቸው የተፈጥሮ አካላት ሁሉ ለውበት(ለቁንጅና) ያረገዱ ናቸው። ቁንጅናን የሚገነዘቡበት እና የሚቆነጃጁበት ስልት ቢለያይም ቅሉ ማማር አብዛኛው(ሁሉም ላለማለት) ሕይወት ያለው አካል የሚጋራው የወል ባህሪዩ ነው።

ወንድ ፒኮክ ልቡ የከጀላትን ሴት ፒኮክ ቀልብ የሚገዛውና ለስሪያ የሚጋብዛት በህብረ ቀለማት ባጌጠ ጭራ-ላባው ነው። የገነት ወፍ(bird of Paradise) የሚባለው ጉደኛ ወፍ ደግሞ ሴቲቱን በዳንስ ውበቱ ልቧን አጥፍቶ አንሶላ ሊጋፈፋት(?) ይሞክራል።



ወንዱ አጋዘን በተንዠረገገ ቀንዱ አማካኝነት የተመኛትን አጋዘኒት ለመማረክ ይለፋል። ቀንዱ የበለጠ በተዠረገገ እና ቅርፅ በያዘ መጠን የበለጠ የሴቷን ልብ የማሸፈት ነገሩ እየጨመረ ይመጣል። አበቦችም አይነ ገብ በሆኑ የቅጠሎቻቸው ቀለማት መስህብነት አርካቢዎችን (pollinators) በመጥራት ርቢያቸውን ያከናውናሉ። በተለያዩ የህይወት ዝርያዎች ውስጥ ውበት የጤና ፣ የጥንካሬ እና የ'genetic quality ማሳያ ቅጥ ተደርጎ ይወሰዳል።

በህይወት ያሉ አካላት በመሰረታዊነት ሁለት ፍላጎት አላቸው። በህይወት መቆየት እና ዘርን መተካት (survive and reproduce) ። በህይወት ለመቆየት እና አደጋን ለመቋቋም የተለያዩ ስልቶችን እና የአካል መዋቅራዊ ልውጠቶችን በዝግመተ ለውጥ ሂደት ያበጃሉ። ዘርን ለመተካትም እንዲሁ። ውበት በተፈጥሮ ውስጥ ካለ ከመራባት (reproduce) ደመነፍሳዊ ፍላጎት ጋር በእጅጉ የተሰናሰለ ነው። ቁንጅና በተቃራኒ ፆታ ላይ ፆር በማስነሳት የመራባት ድርጊያ እንዲፈፀም ያስችላል። ይሄም ውበት (ቁንጅና (ማማር)) ተፈጥራዊ ጠቀሜታን ያነገበ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በአጠቃላይ ቁንጅና(ውበት) በተፈጥሮ ውስጥ ህይወት በማስቀጠል ረገድ አቻ የማይገኝለት ሚናን ይጫወታል።

## ለ) ጥቅም አልባ የውበት አይነት (beauty is quite useless)

ሌላው የውበት ብያኔ ለሰውልጆች ብቻ ከተሰጠ(?) የልቦና ጠገግ የሚፈልቅ ነው። ይህን የውበት አረዳድ ጥበብ ብለን እንጠራዋለን። በመሰረቱ ጥበብ የሚለው የአማርኛ ቃል በውስጡ አምታች ሀሳቦችን የያዘ ነው። የእንግልጣርኛው wisdom እና art የተለያየ አንድምታ ያላቸው ቃሎች ሲሆኑ wisdom እውቀትን ከማግኘት፣ አዲስ አረዳድን ከማበልፀግ ጋር አቻ ሲሆን art ደግሞ ከተለምዷዊው እውነታ(fact) ውስጥ ውበት ቆስቁሶ የማውጣት ብልጠት እንደማለት ነው። ነገር ግን የኛው አማርኛ ሁለቱን ፅንፍ ሀሳቦች በወል ስም የመጥራት አባዜ ተጣብቶታል። በዚህ አረዳድ የ “art” ትክክለኛው ያማርኛ የቃል ግጣሙ ጥበብ ነው ጠቢብ ስንልም artist እያልን እንሆነ ልብ ይሏል።

ወደ ቀደመ ነገራችን ስንመለስ ጥበብ ከሰውልጅነት የሚገኝ በረከት(እዳ) ነው። ይህ ነገር ከሌላው የህይወት አካል በተለየ ንቁ(conscious) በመሆናችን የሚገኝ ነው። የሰውልጅ ባጋጣሚም ይሁን በስጦታ ባገኘው ንቃት የሚኖርበትን አካባቢ፣ የሚኖርበትን ሁኔታ፣ እዚህ ተፈጥሮ ውስጥ የተገኘበት ስልት፣ ያስገኘውን አካል፣ የተገኘበትን ምክንያት ለማግኘት እንደለፋ ነው። ነገር ግን ያለው መታገያ ምክንያታዊነት(logic) ብቻ ነው።

በምክንያታዊ አእምሮ ተጠቅሞ ዘናጭ ስልጣኔዎችን ፈጥሯል፣ ጨረቃ ላይ ተሰቅሏል፣ ምድር ጥልቀት ገብቷል። የደመነፍሱን ጥያቄዎች የሚመልስ አርኪ “ነገር” ማግኘት ተስኖታል። በዚህም ሳቢያ አሁንም ባዘናነት አልቀቀው። logical በሆነው የሰውልጅ አእምሮ እና illogical በሆነው ስርዓተ-ዓለሙ(universe) መካከል በሚኖር ግጭት ወለፈንዲነት ይፈጠራል ይሉናል ወለፈዳዊያን(absurdist)።

እኔያቹ ደግሞ ይህ አለመጣጣም የጥበብ መከሰቻ ስፍራ ነው እላለሁ። በተጠይቅ እውነትን ማወቅ ያቃተው የሰውልጅ በተስፋ ቢስነት እንዳይሞት በራሱ ምናብ የራሴ የሚለውን አለም እና እውነት ለመፍጠር የሚለፋበት ቅጥ ነው ጥበብ። ኒቼም መንፈስ መራውና እንዲህ ሲል ተነጋገረን “we have art not to die of the truth”።

ጥበብ የሰውልጅ አእምሮ የህልውና ጥያቄዎች አጣርቶ ባለመመለስ የሚፈጠርበትን አበሳ ሽል ብሎ ለማለፍ የፈጠረው የማርያም መንገድ ነው። እውናዊውን አለም ለመመሸሽ የሚያንፀው የእፎታ ቅፅር እንደማለት። ይህን ውበት ነው ጥቅም አልባ የምንለው። “All art is quite useless” እንዲል ኦስካር ዋይልድ ጥበብ ለሰው የሚሰጠው የሚታይ፣ የሚጨበጥ ፣ የሚዳሰስ ጥቅም የለም። ጥበባዊ ውበት ለተደራሲው የሚያቀብለው እፎይታን እና የስሜት ልህቀትን ብቻ ነው። ከጥበብ ስራ ውስጥ የሚጨበጥ ነገርን አገኘው የሚል ቢገኝ መልሳችን:- አርቲስቱ ጥበባዊ ውበትን ለመፍጠር ከተጠቀመው factual material (content) እንጂ ሊያቀነቅን ከፈለገው ውበት አንፃር አይደለም ማለት እችላለን። ይሄን ስል ምን ማለቴ ነው? !

በመሰረቱ የጥበብ ውጤቶች መሰረት የሆኑ ሁለት ነገር አሉ እነሱም ቅርፅ (form) እና ይዘት(content) ናቸው። ይዘት (content) ማለት አርቲስቱ ከእውነታው አለም የሚወስደው ሀሳብ እንደማለት ነው። ለምሳሌ ፍቅር መሰረት ያደረጉ ስንት ዘፈኖች፣ ስንትና ስንት ደርሰቶች እና እልፍ አእላፍ ፊልሞች ተሰሩ? ስለ ሀገር ፣ ስለ ጦርነት፣ ስለ ጓደኝነት፣ ስለ ክፋት፣ ስለ መልካም ምግባር… ወዘተ ብዙ ኪነ ጥበባዊ ሥራዎች ተሠርተዋል።

ይዘት ተደጋጋሚ የሆነ አዲስ ያልሆነ ከእውነኛው አለም የሚገኝ ሀሳብ ነው። ይዘት የሚፈጠር ነገር ሳይሆን ያለ የነበረ ወደፊትም የሚቀጥል ነው። “Content is neither created nor destroyed” ሳይባል ይቀራል ብላቹ ነው? ወደ ቅርፅ (form) ስንመጣ አንድ ሀሳብ (ይዘት) በምን አገላለፅ ቢገለፅ የሰመረ ይሆናል? ብሎ መጠበብ እንደማለት ነው። የአርቲስቱ ተግባር ይሄን ቅርፅ የማበጀት ነው። ጥበብ ማለትም ተራ ተርታ ለሆነው ሀሳብ፣ ይዘት(content) አዲስ የቅርፅ ማንነት ሰጥቶ መኳል ማለት ነው። ይሄ መኳኳል ውስጥ የምታገኘው ፍሬ ነገር የለም። Artist እንደፈጣሪ ነው ፈጣሪ ስጋ የሚባል አዲስ ቅርፅ ውስጥ ዘላለም አብሮት የነበረን እስትንፋስ እፍፍፍ ሲለበትም አይደል ሰው ህያው የሆነ። ልክ እንደዛው ጠቢብም አዲስ ቅርፅ ፈጥሮ የነበረን የሀሳብ(ይዘት) እስትንፋስ እፍፍፍ ቢልበት’ዜ እንሆ ጥበብ።

## Art for art’s sake (እኔ እና ቤቴ ግን ጥበባዊ ውበትን እናመልካለን)


ጥበብ ለጥበብነቱ የሚለው እንቅስቃሴ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አከባቢ በሰፊው ሲቀነቀን የነበረ ሃሳብ ነው። የሀሳቡ ዋና ማጠንጠኛ ጥበብ ከራሷ የጥበባዊ ፋይዳ ውጪ የትኛውንም ሀሳብም ሆነ ዘርፍ ማገልገል የለባትም የሚል ነው። ጥበብ ለማህበራዊ ፋይዳ፣ ፖለቲካዊ ርዕዮት ለማንፀባረቂያ፣ የሀይማኖት ስብከት ማጠጫ ፣ ሳይንሳዊ እወነት ማስተላለፊያ የሆነች እንደሆነ ጥበባዊ ውበቷ ይረክሳል ሲል በፅኑ ይከራከራል። ይህ ጥበባዊ አስተሳሰብ በዋናነት በሶስት መሰረታዊ መባያዎች ሊተነተን ይችላል።

1. በጥበብ ውስጥ የሌሎች ዘፎችን ጣልቃ ገብነት መቃወም። ጥበብ ራሷን የቻለች ዘርፍ እንጂ ሌሎች ዘረፎች አቋማቸውን ለማስተላለፍ የሚጠቀሙባት የዘር ፈረስ ያለመሆኗ ነገር።

2. በጥበባዊ ቁመና ውስጥ ለቅርፅ የሚሰጠው ትኩረት። በጥበብ ለጥበብነቱ አስተሳሰብ ውስጥ አርቲስቱ ከይዘት ይልቅ ለቅርፅ ተጨናቂ ነው። ማለትም ይዘት አርቲስቱ ጥበባዊ ለዛን ለመቀመር ሲል የሚጠቀመው ጥሬ የሀሳብ ፍንካች ሲሆን ይህ ሀሳብ የነበረ፣ ያለ፣ ወደፊትም የሚኖር አዲስነት የሌለው ነገር ነው። በጥበብ ለጥበብነቱ አስተሳሰብ አይን አንድ የጥበብ ስራ የሚመዘነው በይዘቱ ሳይሆን ይዘቱን በምን አይነት አዲስ ቅርፅ ቀረበ በሚል ነው።

3. የውበት ጥቅም አልባነት። Art for art's sake የሚለውን ጥበባዊ ንቅናቄ በጊዜው ወደ ላቀ ደረጃ ካሳደጉት መካከል የሚጠቀሰው Theophile Gautier እንዲህ ሲል ተደምጧል "whenever something becomes useful it ceases to be beautiful" እንደ ጥበብ ለጥበብነቱ አራማጆች ዲስኩር ከሆነ ጥበባዊ ውበት ለተደራሲው ከሚያቀብለው የስሜት ፍስሃ ውጪ የሚሰጠው ተጨባጭ ጥቅም የለም። ከላይ ጥቅም አልባ ውበት ብለን ካነሳነው የውበት አይነትን ይሄ ጥበባዊ አረዳድ በፅኑ የሚያምንበት ነው። አንድ ነገር መጥቀም ሲጀምር ውብ መሆኑ ያበቃለታል።

## የሰለሞን ደሬሳ ነገር



ማእበል ጠሪ የተባለለ የዴሬሳ ልጅ ሰለሞን በኢትዮጵያ ኪነጥበብ ውስጥ ከሚታወቅባቸው ነገሮች አንዱ ባለው የጥበብ ለጥበብነቱ አቋም ነው። ሰለሞን "እሸቅድምድም" ብሎ ርዕስ በሰጠው የልጅነት መፅሐፉ መግቢያ ላይ ጥበብ ለጥበብነቱን የሚለው አስተሳሰብ እንደሚያቀነቅን ሆኖ ለመቅረብ ሞክሯል። እንዲህ በማለት:-

"ልብወለድን፣ ግጥምን፣ ድራማን ለማንጠር ብእር የሚገፉ ሁሉ በእንቅልፍ ጊዜ ለምን ይህ ሁሉ ጣጣ? ከሚል ጥያቄ ጋር መተናነቅ አይቀርለትም። ለሀገር ብልፅግና፣ ለቋንቋ መዳበር እና የመሳሰሉ መልሶች አንድም ለማስመሰል ወይንም በየዋህነት የሚሰጡ መልሶች ናቸው።"

"...የግጥም(የጥበብ) መልክት እግጥሙ ውስጥ የተሸነቆረ ሳይሆን ግጥሙ ራሱ እንዲሆን ስለሚሻ። ግጥም የፍልስፍና ማስተላለፊያ፣ መስበኪያ ወይም የምስጢር ጎተራ አይደለም። እንደአጋጣሚ ሁሉንም ሊታከክ ይችላል።"

እነዚህ እና ሌሎች ያልተጠቀሱ ሀሳቦች የሰውዬውን አቋም በግልፅ የሚያንፀባርቁ ናቸው። ነገር ግን የግጥም ስራዎቹ ከዚህ አቋሙ የተገኙ ናቸው ብሎ መደምደም አስቸጋሪ ነው።




ሰለሞን የጥበብ ለጥበብነቱን አስተሳሰብ ተረድቶ ወደ ወደ ጥበባዊ ስራ የተረጎመበት አግባብ የተሳሳተ ነው። በመቅድሙ ውስጥ ያስፈረው ሀሳቡ የግጥሞቹን ጥበባዊ ማንነት አይገልፅም።

ከሌላ ወስልታ የወደለችውን ዲቃላ ለባሏ ልጅህ ነው ብላ እንደምታስታቅፍ መአተኛ ሴት ሰለሞንም የወለዳቸውን ዲቃላ ግጥሞች እንደ አቋም ለሚቀበለው አስተሳሰብ ልጅህ ናቸው ብሎ ያስተቅፋል። በነዚህ ዲቃላ ግጥሞች "መባለግ" አባት ነህ የተባለው "art for art's sake" ይሰደባል። ታዲያ የነዚህ ዲቃላ ግጥሞች እውነተኛ አባት ማነው? አትሉም?

ሰለሞን በመርህ ደረጃ በመቅድሙ እንዳስቀመጠው art for art's sake ን ይቀበላል ነገር ግን በግጥሞቹ መልክ ውስጥ የሚይንፀባረቀው Dadaism ነው።

# Dadaism




እ.አ.አ በ 1916 በመጀመሪያው የአለም ጦርነት ወቅት የተመሰረተ ጥበባዊ አረዳድ ነው። ጦርነቱ የፈጠረው ቀውስና ውድመት ይዞት የመጣ አስተሳሰብ ሲሆን ነገረዬው በ Zurich Switzerland ውስጥ cabaret voltaire በሚባል ካፊ ውስጥ በሚሰበሰቡ ሰዓሊያን እና ገጣሚያን የተፈበረከ ነው። ካፌው የ dadaism መስራች ከሚባሉት አንዱ በሆነው hugo ball አማካኝነት በ 1916 ተከፈተ። dadaism በሶስት መሰረታዊ ሀሳቦች የሚፀና ነው።

1.Anti art-ተለምዷዊ የሚባለው የጥበብ አከያየን መንገድን መካድ እንደማለት።

2.Nonsensical and absurd-የ”ጥበብ” ስራቸው ወለፈንዲነትን እና ኢ-ምክንያታዊነት የተፀናወተው ሲሆን ይህም የሕይወትን ትርጉም አልባነት አፅእኖት ለመስጠት ከመሻት የመጣ ነው። ሌላው ደግሞ ከ’conventional meaning ይልቅ ለምናባዊነት (imagination) ላቅ ያለ ስፍራ የመስጠት ዝንባሌ ነው። እንዲሁም የጥበብ ስራቸው ለተደራሲው ግራ አጋቢ የሆኑና ተደራሲው በስራው ላይ የራሱን አረዳድ እና ትርጉም እንዲሰጥ የሚገፋፉም ናቸው።

**3.Randomness- የጥበብ ስራቸው ዘፈቀዳዊነትን ተገን ያደረገ። ይህም ተምዷዊ በሚባለው የክየና ስልትን በእጅጉ የሚፈታተን ነው። ለዳዳው ድንገት እንደ ሽንት ወጥሮት ወረቀት ላይ የሞነጫጨረው የቃላት ጋጋታ ሁሉ ግጥም ነው። ሲደነቃፈፍ የደፋው ቀለም የሚፈጥረው ነገር ሁሉ ስዕል ነው።**

**እንግዲህ ሰለሞን ደሬሳ በግጥሞቹ ውስጥ በእጅጉ የሚያንፀባርቀው ይሄንኑ አስተሳሰብ ነው። የሰለሞንን Dadaistነት የምታጎላ ግጥም ልጅነት ከሚለው ስራው ጠቅሰን እናሳይ "ጉማላሎ" ትሰኛለች ግጥሚቱ።**

*"ብታቅማማ፣ ባታቅማማ*
*አትል ግጥም አይደል*
*ዱዳ ካልሆንህ የማትሰማ*
*ልጓም ካለ ለፍትወቱ*
*ሀሳብ ካለ ቸርነቱ*
*ብትሰማ*
*ባትሰማ*
*ብፈነዳ*
*ባልፈነዳ*
*ብቀኝ*
*ባልቀኝ*
*ባደምጥህ ትዝብትሁና*
*ቃላት ሳልቋጥር*
*ስንኝ ሳላዛውር*
*ግጥም ነው ቋንቋ ነኝ*
*ምን ታረጉኝ"*

**ሰለሞን በዚህ ግጥም ተምዷዊውን የአገጣጠም እና ያከያየን መንገድን ክዷል።**
**"ቃላት ሳልቋጥር"**
**ስንኝ ሳላዛውር ግጥም ነኝ ብሎ ችክ እንደማለት ይሄም የ Dadaism መሰረታዊያን ብለን ከላይ ከጠቀስናቸው ሀሳቦች ውስጥ anti art የመሆኑ ማሳያ ነው።**

**ሌላው በሰለሞን ግጥሞች ላይ የሚታየው የ**dada **ባህሪ** nonsensical **የሚለው ሲሆን ይሄም አጠቃላይ በግጥሞቹ ውስጥ የተንፀባረቀ ነው። ለምሳሌ እንዲሆነን "በሃምለት አገር" የሚለውን እንጥቀስ።**

*"ከተራራ ላይ ቅርብ ባህር ሲያዩ*
*የተሰነጠቀ መስሎ ለሁለት ሰማዩ*
*በስንጥቁ መሬት ሲገባ*
*ጥቁር ቅጠላዊ የህልም ገለባ*
*ደረቅ አረንጓዴ አንጀት የሚያባባ*
*ስወርድ ቁልቁለቱን*
*ስሄድ? ስንከባለል?*
*ባልጋ ልወረወር*
*ልስመጥ ልንሳፈፍ ፣ ወይንስ ልሳፈር*
*ወደ ሌላ በሌላ በር"*

**ልክ እንደዚህ ሁሉ አብዛኞቹ (ሁሉም ላለማለት) ስሜት የማይሰጡ ስለምን እያወራ እንደሆነ ተደራሲ ይረዳው ዘንድ የሚቸግሩ ናቸው። ግጥሞቹን የሚያነብ ሁሉ የየራሱን ግለሰባዊ አረዳድ ይኖረው ዘንድ እንጂ ሁሉም ባይሆን አብዛኛውን አንባቢ የሚያስማማ ነው። ገጣሚው ይሄን ሊለን ፈልጎ ነው የምንለው ነገር የሰለሞን ስራ ውስጥ ማግኘት ይቸግረናል። ይሄም ሰለሞን** Dadaist **ነው ያስባለን ማስረገጫ ነው።**

**ሌላው የሰለሞን ደሬሳን** Dadaist **መሆን የሚያረጋግጥልን ነገር "እሽቅድምድም" ብሎ በጠራው መግቢያው ላይ በዘወርዋራው የተናገራት ቃል ነች። እንዲህ ስትል ትነበባለች "...እነዚህ አርባ ተኩል ግጥሞች የተፃፉት መፃፍ ስለነበረባቸው ነው። አልፎ አልፎ ልፈትለክ ሲሉ ተለቅቀዋል። ጥቂቶቹ ወንዝ ዳር እንደሚገኝ በጊዜና በውሃ የለዘበ ድንጋይ ተዋጥተዋል። "**

**ሽንት ወጥሮን ፋታ ሲነሳን መገላገያውን እንደምንናፍቅ ሁሉ ሰለሞንም ቃላት ወጥረውት ልፈትለክ ሲሉ በግጥም መሰል ቅርፅ ለመገላገል ሸናቸው። ይሄ ከላይ የ** Dadaism elements **ብለን ከጠቀስናቸው ሀሳቦች** randomness **ያልነውን የሚያሳይ ነው። መፃፍ ስላለባቸው የተፃፉ ገጠመኛዊ የቃላት ድርድሮች።**

ስለ ሰለሞን ደሬሳ ግጥሞች ይሄን ካነሳን በ dadaism እና በ art for art's sake መካከል ያለውን መሰረታዊ ልዩነት እንይ። Dadaism አጠቃላይ ተለምዷዊ በሚባል ጥበብ ውስጥ ያለን ውበትን የማምለክ  ዝንባሌ ላይ መናፍቃዊነትን ያራምዳል።

መስራቾቹ በጊዜያቸው ከነበሩበት ጦርነት፣ ውድመትና መአት አንፃር ጥበብ የምታቀነቅነው ውበት ከእውነታዉ የራቀና ትርጉም የለሽ መሆኑን ጥበባዊ ውበት ላይ በመዘባበት ለማሳየት ሞክረዋል። በአንፃሩ ጥበብ ለጥበብነቱ የሚለው እንቅስቃሴ ከዚህ የምንፍቅና ሀሳብ በተቃራኒ ለጥበባዊ ውበት የተለየ አምልኮና መሰጠትን የሚያቀነቅን ነው። ጥበብ የትኛውንም ዘርፍ የምታገለግል ገረድ ሳትሆን ውብ እመቤት ናት ብሎ የሚሞግት ነው።

ሌላው Dadaism መአትን (chaos) ፣ ወለፈንዲነትን እና የአለምን አስቀያሚነት ጥበብን በማርከስ ስልት ለማሳየት ሲጋጋጥ በአንፃሩ art for art's sake የተሟላ ውበትን እና ውህደትን መሰረቱ ያደርጋል። ጥበብ ለጥበብነቱ የእውነታውን አለም ማስቀየም በጥበባዊ የውበት ማደንዘዣነት ለማለፍ ሲለፉ ዳዳ ደግሞ እውነታውን አለም በማስቀየም የጥበብን አደንዛዥ ውበት በመገዳደር ሊያሳየን ይሞክራል። Art is the opium of the people ሳይል ይቀራል ብላቹ ነው።

# የዓለም-አየሁ ነገር



ዓለማየሁ ገላጋይ ፀሃፌ ትእዛዙ በሆነው ቴዎድሮስ አጥላው በኩል "ጥበብ ለጥበብነቱን" አምርሮ መጥላቱን እንዲህ ሲል ይናገራል "ደራሲ የማኅበረሰብ ዕዳ አለበት በሚል አክራሪ አቋሙ የተነሣ፣ 'ጥበብ ለጥበብነቱ' የሚባልን ሐሳብ ጭምር አምርሮ የሚተቸው ዓሌክስ ለራሱ የሕዝብን ሕይወት የመተርጎም፣ የማኅበረሰብን ኑሮ የማስተማሰል (አስተማስሎ) ወይም የማንጸባረቅ፤ የእኔ የሚለውን ትውልድና ዘመን መንፈሱን የመግለጥ፤ ሀገርን እና ሕዝብን ራሱን እንዲመረምር የማንቃት፤ በመጥፋት ላይ ያሉ ትዝታዎችን የመጠበቅ፤ ዘመናችንን፣ ፍቅራችንን፣ ዕውነታችንን፣ ዕምነታችንን እንፈትሽ የማለትን ዕዳ ራሱ ላይ ጭኖ ይኽንኑ በወጉ የተወጣ ታላቅ ደራሲያችን ነው።"

ገላግሎቪች Art for art's sake'ን መተቸቱ ወይም አምርሮ መፀየፉ ባላስከፋ ነበር። ነገር ግን ነገርዬውን የሚተችበት መንገድ ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ ብናገኘው'ዜ ይችን ንጭንጭ የመሰለች ፅሁፍ ለመፃፍ ተጎባበዝን።

ከቴዎድሮስ አጥላው ፅሁፍ እንደምንረዳውና ጋሼም በቅርቡ ባወጣው "ማዕበል ጠሪ ወፍ" በሚለው ስራው ደጋግሞ እንዳሳየን ጥበብ ለማህበራዊ ግልጋሎች የመዋል ግዴታ አለበት ባይ ነው። በኔ እምነት ገላግሎቪች ጥበብ ለጥበብነቱን በቅጡ የተረዳ ራሱ አልመሰለኝም። ለሳቸው ማለቴ ለጋሽ አሌክስ art for art's sake ማለት የሰለሞን ደሬሳ ዲቃላ ግጥሞች ማለት ነው። ጥበብ ለጥበብነቱ ዋና ግብ ጥበብ የተለያዩ ዲሲፕሊዎችን ለማስተላለፍ እንደሚጠቅም መሳሪያነት ከማየት ወጥተን ጥበብ ራሱን የተቻለ ዘርፍ መሆኑን ማመላከት ነው።

ሳይንስና ሀይማኖት የተለያዩ ዘርፎች ናቸው። ፖለቲካና ፍልስፍና የተለያዩ ዘርፎች ናቸው። የሚጋሯቸው የሚያስተባብሯቸው(interdisciplinary) ነገር ቢኖርም አንዱ ያንዱ አገልጋይና ሎሌ ሳይሆኑ ራሳቸውን ችለው የቆሙ ጎበዛዝት ናቸው። ወደ ጥበብ ስንመጣ ግን ጥበብን እንደ አንድ ራሱን የቻለ ዘርፍ ከማየት ይልቅ ነገሮችን ለማስተላለፍ እንደሚያገለግል መሳሪያ የማየት ተለምዷዊ ዝንባሌ አለ።

ገላግሎቪች ይህን ጥበብን እንደ አገልጋይ ገረድ ከሚያዩት እንደ አንዱ ነኝ ይላል። ጋሼ እርጅና ሳይጫነው አልቀረም መሰለ ነገር መደጋገም አብዝቷል። ትችቱን የመሰረተው ቃላት እየቀያየረ በሚጠቀማት የማክሲም ጴካምፕ quote ነው እንዲህ የምትነበብ ነች *"form is beautiful, true when a thought beneath it! What is the use of beautiful forehead, if there is no brain behind it?"*

**ባጭሩ የሚያምር ግንባር ብቻውን ምን ፋይዳ አለው ከጀርባው አእምሮ ከሌለው እንደማለት ነው።**

ጋሼም የቃሏ ፀሃፊም ያልተረዱት ነገር የውበትን (ጥበብን) ስረ መሰረትን ነው። ሰዎች ጥበባዊ ስራን የሚታደሙት የሆነ አይነት ውበትን፣ የሆነ አይነት መስህብን፣ የሆነ አይነት መራቀቅን በመሻት ነው። ይህ ማለት የጥበብ ግቡ ውበት ይሆናል ማለት ነው። የጥበብ ግቡ ውብ ነገሮችን ፈጥሮ በሱ የእርካታ የእረፍት ስሜትን የማቀበል ጉዳይ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ጥበብ ግድ የሚለው ከበተስጀርባ ስላለው brain ሳይሆን ፊት ስላለው beautiful forehead ነው እንደማለት ነው። ጥበብ ብለህ ስትመጣ "brain" ከተባለው እውነት ተንፈስ ለማለት እና የሆነ አይነት ድማሜ ውስጥ ለመዘፈቅ መፍቀድህን የሚያሳይን ነው።

ጋሽ ዓለም-አየሁ እና ተጠቃሹ ሰው ይህንን የሸሸነውን "brain" የሚሉትን "ሰይጣን" የእፎይታ ቅፅራችን ውስጥ አስገብተው ይቀድስ ይሉናል። ይሄ እልም ያለ ምንፍቅና ነው። ውጉዝ ከመ አርዮስ የሚያስብል።

ለዓለም-ዓየሁ ለማህበረሰቡ እሴት ያልቆመ የተኛውንም ትውልድ ያላነቃ ጥበብ አይደለም። ይሄንን ነገር Oscar Wilde አጉል ልምድ (mannerism) ይለዋል። አርቲስት መጠበብ ያለበት እንዴት ውበትን ልቀምም ብሎ እንጂ እንዴት ለማህበራዊ እሴት ልቁም ብሎ አይደለም። Oscar Wilde "the picture of dorian gray" በሚለው ዝነኛ መፅሐፉ መግቢያ ላይ በቆንጆ ሁኔታ ሀሳባችንን የሚተባበር ነገር ይለናል።

"No artists desire to prove anything. Even things that are true can be proved. No artist has ethical sympathies. An ethical sympathy in artists is an unpardonable mannerism of style."



# ጥበቃ… (Expectation)

(ደምስ ሠይፉ)

*“Blessed is he who expects nothing, for he shall never be disappointed.”*
*Alexander Pope*

መጠበቅን መሰላል እንደመውጣት ነው የማስበው። በጣም ትጠብቃለህ ማለት በመሰላሉ ከፍተኛ እርካብ ላይ አለህ ማለት ሲሆን ጥበቃህ ዝቅተኛ ወይም መካከለኛ ነው ማለት ደግሞ የመሰላሉን ተመሳሳይ ቦታ ይዘሃል ማለት ነው። መሰላል የወጣ ሰው ዕጣፈንታ ሁለት ነው። ወይ እንዳወጣጡ ይወርዳል፤ አልያም ከደረሰበት ነጥብ እርካብ ከድቶት ይወድቃል።

የመጠበቅ ዕጣ ፈንታ የሚወሰነው መሰላሉ ላይ በሰቀለህ እውነታ ነው። ብዙውን ጊዜ ግን ጥበቃህ ከእጅ ካለው የታወቀ ሁኔታ ይልቅ ባልተጨበጠ ተስፋ ላይ የሚመሰረት ይሆንና ውጤቱ መውደቅ ይሆናል። በመስተጋብራችንም ሆነ በግል ልምምዳችን ውስጥ እጅግ አደገኛው ስሜት መጠበቅ ሲሆን አስከፊ ውጤቱ ደግሞ የጠበቁት ሳይሆን ሲቀር የሚፈጠረው ስብራት ነው። ይህ ጥበቃ የታክሲ ሰልፍ ወይም የቦኖ ወረፋ አይደለም። ጊዜ ሲደርስ የምትደርስበት ወይም የመሆን ዋስትና የጨበጠ አይደለም። የስሜት ዕዳ ነው። የቅጽበት ክስተት። ቀጣዩ ምን እንደሆነ የማይታወቅባት ዓለም ዕዳ።

እኛ ሰዎች ብዙ ጊዜ ከሕይወት ጋር በጻጥታ የምንገባው ውል አለን። ኮሽታ ሳናሰማ በተስፋ፣ በህልም፣ በምኞት በመፃኢ ላይ የተመሰረተ ስምምነት እንፈጽማለን። በአዕምሮአችን ውስጥ ጥንቅቅ ብለው የተሰደሩ በርካታ ውብ ስዕሎች አሉን። ጠንክረን ስለሰራን፣ አጥብቀን ስላፈቀርንና ተግተን ስለጠበቅን ሕይወትም በዚያው መሰረት ምላሽ እንደምትሰጠን እናስባለን። እናምናለንም። ግና ምኞትና እውነታ ሁሌ አይሰምሩም። ያንጊዜ ደግሞ የመንፈስ ስብራት ይገጥመናል።

ስብራት ያልሰመረ ጥበቃ ውጤት ነው። ብዙ የለፉለት ግንኙነት ምላሽ ሲያጣ፣ ለረጅም ጊዜ የጠበቁት ዕድል ቅዠት ሲሆን፣ እንደ ጣልንባቸው ተስፋና እንደ ሰጠናቸው ቦታ ሰዎች ሳይከውኑ ሲቀሩ ህመም ይገጥመናል። ህመሙ ግን ስለ እጦታችን ብቻ አይደለም። ከእጃችን በሌለ ነገር ላይ የገነባነው ተስፋ ከፊታችን ብን የማለቱ ሃቅ ብሎም ለርሱ ብለን ያጠፋነው ጊዜ የሚፈጥረው ቁጭትም ጭምር እንጂ።

"Disappointment is a sort of bankruptcy—the bankruptcy of a soul that expends too much in hope and expectation."

Eric Hoffer

## ነገሩን በምሳሌ እናፍታታው

ያፈቀርካት ልጅ ከልብህ የቀለስክላትን ጎጆ አክላ እንድትከሰትልህ ትጠብቃለህ። በእርሷ ልብ ውስጥ ዳስ የተጣለለት ተፈቃሪ ሊኖር መቻሉን ግን ትዘነጋለህ። እናም - "አይሆንም" አለችኝ በሚል ሰበብ ልብህ እንክት ትላለች።

ሃሳብህን ሰው ሁሉ እንዲረዳልህ ትጠብቃለህ - ግና ሁሉም ሰው በየራሱ ንሸጣ፣ በየራሱ መንገድ (በዚህ ምክንያት ድብርት ትከናነባለህ...)

ሰዎች ሁሌም በበጎ ቃልና በፈካ ፊት እንዲቀበሉህ ትጠብቃለህ - ሆኖም ሰዎች በብዙ ዓይነት የስሜት መዋዠቅ ውስጥ እንደሚያልፉ፣ ያም ቀናነታቸውን እንደሚያደበዝዘው ትዘነጋለህ። (በዚህ ምክንያት ቀንህን አስረክበህ ትውላለህ። አንዳንዴም ቂም ቋጥረህ ግንኙነትህን ታበላሻለህ።)

ሎተሪ እንዲደርስህ ትጠብቃለህ - ሆኖም ከብዙ ሚሊዮኖች ጋር የሚደረግ ውድድር መሆኑን ትዘነጋለህ። (በዚህ ሰበብ ዩኒቨርሱን በአድሎ ፈፃሚነት ትከሳለህ።)

በድካምህ ልክ ሹመት፣ በጥረትህ ልክ ሽልማት ትጠብቃለህ - የሰዎች ሚዛን ያለው ራሳቸው ጋ መሆኑን ግን ትዘነጋለህ።(እናም ይህን ሰበብ አርገህ የስራ ሞራልህን ትገድላለህ።)

ብዙ ድካምና ሃብት ያፈሰስክበት ቢዝነስ ፈጥኖ ውጤታማ እንዲሆን ትጠብቃለህ - የጊዜና የሁኔታዎችን ምቹነት የማጤን አስፈላጊነትን ግን ትዘነጋለህ። (በዚህ ምክንያት የሚያድግ ወረትህን ትቀብራለህ፣ ሌላ የመጀመር ድፍረትህንም ትሰዋለህ።)

በችግራቸው ጊዜ አለሁ ያልካቸው ሁሉ ኑሮ ሲፈትንህና ምርግ ሆኖ ሲጫንህ እንዲደርሱልህ ትጠብቃለህ - ከጓዳቸው ያደፈጠ፣ ከገመናቸው የተሻጠ ምስቅልቅል ሊኖር እንደሚችል ግን ትዘነጋለህ። (አዎን - በዚህ ተቀይመህ ሰው ትርቃለህ፣ የልብህንም ሰዎች ታጣለህ።)

ወዳጆችህ በሃዘንህ ጊዜ ጎንህ ተገኝተው እንባህን እንዲጠርጉ፣ በክፉ ጊዜህ ገመናህን እንዲሸሽጉ፣ በደስታህ ጊዜ ድግስህን እንዲያደምቁ ትጠብቃለህ - ከእነርሱ ታዛ ሰው የማይደርስበት ለቅሶና ምሬት፣ በሳቅ የሚከልሉት ችግርና ብሶት ሊኖር እንደሚችል ግን ትዘነጋለህ። (እናም በዚህ ሰበብ ሰው የምታይበት ዓይን፣ የምታቀርብበት ወሰን፣ የምታርቅበትም ሚዛን ይዥጎረጎራል።)

"We are all prisoners of our expectations."
Georges Bernanos

**ታዲያስ?**

እንግዲህ ጥበቃ የአዕምሮ ቅኝት ነውና ይቆጣጠሩታል እንጂ አያስቀሩትም። ይመጥኑታል እንጂ አልቦ አያደርሱትም። ማግስቱን ለድብርት፣ ከርሞ ለስብራት ምክንያት እንዳይሆን ግን ብዙ ነገር ማድረግ ይቻላል።

## ሦስት መላዎች ይታዩኛል

### ፩. *Flexibility*

"ይህን ካላገኘሁ ሞቼ እገኛለሁ" ከማለት ይልቅ "ይህ ባይሆን ያንን አሳካለሁ" ብሎ ማሰብ። ችክ አለማለት። አማራጮችን ማየት። አንዳንድ ጊዜ ያጣነው በመሰለን አንድ ነገር ፈንታ ያልጠበቅነው እልፍ ስጦታ ሊደርሰን ይችላል። የጠበቅነው የሚጎዳን፣ የሚሰጠን የሚያስደስት ሊሆንም ይችላል።

### ፪.

እንዲሆን የሚፈልጉት ነገር ላይ what if መቀላቀል። ባይሆንስ ብሎ ማሰብ። ቢቻል የጉዳዩን ተጨባጭነት ማጤን፣ አልያም ጥበቃን ማመጣጠን። (በመሰላሉ ግርጌ ላይ መቆየት። ነገሩን የሚያመጣው ወይም የሚያስቀረው ጥበቃው ሳይሆን የጉዳዩ ተጋጋዥ ሁኔታዎች ሕብር ነው። ሊመጣ ያለን ባለመጠበቅ አታጣም፣ የማይመጣንም በመጠባበቅ አትወልድም።)

### ፫. መቀበል

የሆነውን እንደመሆኑ ማስተናገድ። ስለ ጉዳዩ ከመብሰልሰል ይልቅ ክስተቱን እንደሁኔታው ተቀብሎ ወደፊት መጓዝ። ባለፈው ጎርበጥባጣ የባከነ ጉልበትህን ሳይሆን ቀሪው አቅምህ የሚያስወጣህን አቀበት ማስተዋል። let it go!

"We must accept finite disappointment, but never lose infinite hope."
Martin Luther King Jr.

**መልካም አሁን!!**
@bridgethoughts

# ባይራታ

እነሆ ባይራታ!

ታላላቆቹ ማለት ነው። በራሳቸው ትልቅ ሆነው ያስከበሩንን፣ ትልቅ ነገር ሰርተው ያኮሩንን እየመረጥን ህያው ስማቸውን የምናነሳበት አምድ ነው።

በየእትማችን የታላላቆቻችንን ህያው ስም ስናነሳ ልጅነትና ሰው መሆን ግድ ስለሚለን ነው። ከፍ ሲልም የቆምነው በእነሱው ትክሻ ላይ መሆኑን እንዳንስተው ነው።

# ተራማጁ መድረክ

(በሩት ሀብተማርያም)



*"A director must be a leader, a teacher, a psychiatrist, and sometimes a policeman."*
*Peter Brook*



ልባችንን በአንድ አድርገን የምንስማማበት አንድ እውነት ለተውኔት፣ የተውኔት አዘጋጁ የማይታይ ግን ደግሞ የልብ ትርታ መሆኑን ነው። ይህ ሰው ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ትንፋሾች፣ እንቅስቃሴዎች፣ ድምጾች፣ ምልክቶች፣ ፊደሎች፣ መስማማት መጣላቶች እና ማፍረስ መስራቶችን ወደ አንድ ህይወትና እስትንፋስ በማዋሃድ በመድረክ ላይ እንዲከወን ያደርጋል። በጥልቅ ያዳምጣል። የተውኔቱን ጽሁፍ ቃላት ብቻ ግን አይደለም። ይልቁንም የተዋናዮቹን ያልተነገሩ ህልሞች ጭምር እንጂ።

የቡድናቸው የልብን እና የነፍስ ቁርኝት እንዲሁም ተሻግረው የተመልካቾችን የልብ ምት ያስተውላሉ። ሌሎችን የሚመሩት በጉልበት ሳይሆን በትዕግስት እና በዓላማ፣ በመተሳሰብ፣ በማስተዋል እና በመተማመን ነው። አንድ ታላቅ አዘጋጅ የሚያዘጋጀው ተጽፎ የቀረበለት ጽሁፍ ብቻ አይደለም። በዝግጅታቸው ውስጥ እውነት የሚገለጥበት፣ የተደበቁ እና ያልተነገሩ ስሜቶች ድምፃቸውን የሚያገኙበት እና ሊስተዋል ያልቻለ ግን ውድ ነፍስ የሚታይበት ቦታ በተውኔቱ ውስጥ ያዘጋጃል። የአዘጋጅ እውነተኛ ድንቅ ስራው ትርኢቱ ብቻ ሳይሆን ከመጋረጃው ጀርባ የሚያዘጋጅበት መንገድ እና ያም የሚፈጥረው ውበት ነው።

ጋሽ አባተ መኩሪያ ለኢትዮጵያ ትያትር ታሪክ ልብ ነው ተብሎ ይነሳል። ብዙዎችም የመራሔ ተውኔት አባት እያሉ ይጠሩታል። አብረውት ኖረው፣ በእሱ ሰልጥነው፣ አብረውት ሰርተው የሚያውቁ ስለእርሱ የሚናገሩትን ምስክርነት ለሰማ ምነው ባገኘሁት፣ ባወራሁት ያስብላል። በፎቶዎቹ ላይ የምናየው ፊቱ ሙሉ ለሙሉ የተኖረ ህይወት ብቻ የሚኖረውን ጸጥ ያለ ፀጋን ለተመልካች ያጋባል።

ለዓመታት በሙዚቃ ለስላሳ ጣቶች ሲዳበስ፣ በመድረክ ትሁት ከንፈር ሲሳም፣ አንዳንዴም በሳንሱር እና ቢሮክራሲ ሲነከስ የዘለቀበት ሰፊ መንገድን ተጉዞ ለመድረሱ በፊቱ ላይ የሚታዩ ትንንስ እጥፋቶች ምስክር ናቸው። ጊዜ እና ዘመን አይኖቹ ተከድነው ፊቱ ላይ የሚደምቀውን ፈገግታውን ጠርዝ ለስላሳ አድርጎታል፣ ግን ሙቀቱ አልቀነሰም። ፊቱ ላይ የሚታየው እያንዳንዱ እጥፋት በጊዜ የተፃፈ ጥቅስ ይመስላል። ልብን ያሞቃል። ሰው ሁሉ "ጋሼ" ን አስቀድሞ ይጠራዋል። የወል የክብር መገለጫው ነውና እኛም "ጋሼ አባተ" እያልን እንዘልቃለን። በተጨማሪም ከድፍረት ሳይሆን ከመውደድ ጋሼ መኩሪያን አንተ እያልኩ እንድቀጥል አንባቢዎቼ ትፈቅዱልኝ ዘንድ እማጸናችኋለሁ።

ጋሼ አባተ መኩሪያ የተወለደው በመዲናችን አዲስአበባ አዋሬ ተብሎ በሚታወቀው ሰፈር ሕዳር 10 ቀን፣ 1932 ዓ.ም ነው። አንደኛ እና ሁለተኛ ትምህርቱን ቀድሞ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዴይ ስኩል ይባል በነበረው በአሁኑ ኮከበ ፅባህ ትምህርት ቤት ተከታተለ። በአንድ ወቅት ከጋዜጠኛ መዓዛ ብሩ የቅዳሜ ጨዋታ ፕሮግራም ላይ ባደረገው ቃለመጠይቅ ላይ ሲናገር የትያትር ፍቅሩ የጀመረው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዴይ ስኩል ሲማር ጀምሮ እንደነበር ይናገራል።

"The painter tries to master color, the dancer movement, the poet words, but a born artist master's emotion and turns life itself into art." እንዲል አንድ ማንነቱ የማይታወቅ አሳቢ ጋሽ መኩሪያ በወጣትነቱ የጀመረው የኪነት ፍቅር ይዞት የተወለደው ነው እንድንል ያስገድደናል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ ወደ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ የስነጽሁፍ ትምህርቱን ቀጠለ። ትምህርት መሃል ላይ እያለ ዶ/ር ፊሊፕ በሚባለ የውጭ ዜጋ አማካኝነት “ኪነጥበብ ወ ቲያትር” የሚባል ክፍል ተቋቋመ እና የክፍሉ አባል ሆነ።

ከመዓዛ ጋር ባደረጉት ቃለመጠይቅ “ኪነጥበብ ወ ቲያትር” ልዩ የትምህርት እድል ቢያገኝም የስነጽሁፍ እና ቋንቋ ትምህርቱንም ሳያቆም ሁለቱም ቦታ እየተማረ እንደነበር ይገልጣል። “ኪነጥበብ ወ ቲያትር” እንደተመሰረተ ጋሽ አባተን ጨምሮ በተለያዩ የኪነ-ጥበብ ዘርፎች የፈጠራ ችሎታ የነበራቸው ከያንያን ንቁ ተሣትፎ ማድረግ ጀመሩ።

ጉልህ እንቅስቃሴ ከነበራቸው መካከል አሁን ያንን ዘመን ስናስብ አንድ ሁለት ብለን ልንጠቅሳቸው የምንችላቸው *ተስፋዬ ገሠሠ፣ አፈወርቅ ተክሌ፣ ገብረክርስቶስ ደስታ፣ መንግሥቱ ለማ፣ ዮሐንስ አድማሱ፣ ፀጋዬ ገ/መድህን፣ ዳኛቸው ወርቁ እና ሌሎችም* ነበሩበት። ወርቃማ ዘመን! ስለ ወርቃማ ዘመን ጋሽ አባተ መኩሪያ የተለየ አስተያየት አለው። ብዙዎቻችን ጥሩ የኪነጥበብም ሆነ ሌላ ጥሩ ስራ የተሰራበትን ዘመን ስናስብ የምንለው “ያ ዘመን ወርቃማ ነው ፤ እነ እከሌ ያሉበት ዘመን ወርቃማ ነው” ነው። እሱ ደግሞ “ያንን ዘመን ወርቃማ የሚያደርጉት ሰዎቹ እና ጥረታቸው እንጂ ዘመኑ በእሳት ላይ እንደመራመድ ነው።” ይላል። የሚያስማማ አስተያየት ነው።

“ኪነጥበብ ወ ቲያትር” በዶ/ር ፊሊፕ መሪነት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደርግ ነበር። የተውኔት ዝግጅቶችን፣ ግጥሞችን፣ የስዕል አውደ-ርዕዮችን እና ሌሎችንም ዝግጅቶች በማቅረብ ታዳሚውን ያዝናናና ያስተምርም ነበር። ለ “ኪነጥበብ ወ ቲያትር” ክፍልም፣ ለዶ/ር ፊሊፕም ሆነ ለተሳታፊ ተማሪዎች ደጃዝማች ካሣ ወልደማርያም 1954 ዓ.ም የዩኒቨርስቲው ፕሬዘዳንት ሆነው ተሹመው እስኪመጡ ወቅቱ ጥሩ ይመስላል።

ታዲያን ደጃዝማች ካሣ ወልደማርያም ተሹመው ሲመጡ “ሹመት ያዳብር” ለማለት ተዘጋጅቶ በነበረው የግጥም ምሽት ዮሐንስ አድማሱ “ላም እሣት ወለደች በሬ ቀንድ አወጣ በስልጣን ሊቅ መሆን ይኸም አለ ለካ” የሚል ግጥም አቀረቡ። ግጥሙ ባለድግሱን አዲሱን ፕሬዘዳንት ለመንካት ነበር። የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዘዳንት በሴኔቱ ለመንካት ነበር። የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት በሴኔቱ መሾም ሲገባው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በቀጥታ ደጃዝማች ካሣን እንዲሾሙ በመደረጉ በተማሪውና በማህበረሰቡ ዘንድ ቅሬታ ነበር።

ዮሐንስ አድማሱ ይህን ቅሬታ የሚያባብስ ግጥም በመግጠማቸው “ኪነጥበብ ወ ቲያትር” በሣምንቱ በደጅአዝማች ትዕዛዝ እንዲዘጋ ተደረገ። የክፍሉ ኃላፊ ዶ/ር ፊሊፕ ካፕላንም ኮንትራታቸው ተቋረጠ። በዚህ ጊዜ አባተ መኩሪያ እና ጓደኞቹ ከ “ኪነ ጥበብ ወ ቲያትር” ተባረሩ።

ደጃዝማች ካሳ በሹመታቸው ወቅት የዩኒቨርሲቲውን የአካዳሚክ እና የአስተዳደር መዋቅር በመቅረጽ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ከአካዳሚክ አስተዋፅዖ ባሻገር በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ጥልቅ ተሳትፎ እንደነበራቸው ይገለጻል። አሳዛኙ ነገር ግን የደርግ መንግስት ስልጣን ላይ በነበረበት ወቅት ከታሰሩት እና በኋላም ከተገደሉት 60 ባለስልጣናት መካከል አንዱ ነበሩ።

ጋሽ አባተ ከዩንቨርሲቲው "ኪነጥበብ ወ ቲያትር" ከተባረረ በኋላ አዲስ በመቋቋም ላይ በነበረው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በአዘጋጅነት ተቀጠረ። ቴሌቪዥን ሥራውን በጀመረ ጊዜ የሚያስተዳድሩት እንግሊዞች ስለነበሩ ጋሽ አባተ ለአራት ወራት እንዳገለገለ ግላስኮት ቴሌቪዥን ኮሌጅ ውስጥ ገብቶ እንዲማር ወደ እንግሊዝ አገር የመሄድ እድል አገኘ።

የትምህርት እድሉ ቢገኝም መሄዱ ቀደም ሲል ከመንግስት ጋር በነበር ሰጣገባ ቀላል አልነበረም። ግን በልበ ቅን ሰዎች እርዳታ ለመሄድ እና ትምህርቱን ለመከታተል ችሏል። በእንግሊዝ አገር ቆይታው ሚዲያ ኮሚዩኒኬሽን አጥንቶ እና በቢቢሲም እንዲሁ እየሰራ የሥራ ልምድ አግኝቶ ወደ አገሩ ተመለሰ። ከዚያ እንደተመለሰ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እና በሀገርፍቅር ቲያትር ቤት አዘጋጅና እንዲሁም አሰልጣኝ በመሆን ቀጠለ። በመሃሉ የሲኒማቶግራፊ ትምህርት ለመማር እድል አግኝቶ ወደጀርመን ሄደ።

ጀርመን ውስጥ ኮሎኝ በሚገኘው ቪዲ ኤፍ ስቱዲዮ ስልጠና ወስዶ ተመለሰ። ከጀርመን እንደተመለሰ በሀገርፍቅር ቲያትር ቤት በአዘጋጅነት ተቀጥሮ ለመጀመሪያ ጊዜ "አ! ዘመቻ" በሌላ ስሙ "መልክአ ምድር" በሚል የሚታወቀውን የኢዩኤል ዮሐንስን ተውኔት አዘጋጅቶ አቀረበ። ተውኔቱ ማህበራዊ ህይወትን የሚዳስስ፤ የዝቅተኛ መደብ አባላትን ህይወትን የሚያሣይ ነበር።

ቀደም ሲል  አንድ ታላቅ አዘጋጅ የሚያዘጋጀው ተጽፎ የቀረበለት ጽሁፍ ብቻ አይደለም። በዝግጅታቸው ውስጥ እውነት የሚገለጥበት፣ የተደበቁ እና ያልተነገሩ ስሜቶች ድምፃቸውን የሚያገኙበት እና ሊስተዋል ያልቻለ ግን ውድ ነፍስ የሚታይበት ቦታ በተውኔቱ ውስጥ ያዘጋጃል እንዳልነው ጋሽ አባተም ይሔንኑ አደረገ። ሆኖም ግን አራት መድረኮችን በአርብ የምሽት ፕሮግራሞች እንዳቀረበ በቅድመ ምርመራ (ሳንሱር) መሥሪያ ቤት ተጠርቶ ተውኔቱን ማሣየት እንዲያቆም መወሰኑ ተነገረው። የወርቃማ ዘመን አልነበረም የነበሩት ወርቃማ ሰዎች ናቸው።

ከዚህ ተውኔት ጋር በተያያዘ ከሀገር ፍቅር ቤትም ከቴሌቪዥንም እንዳይሰራ በአንድነት ታገደ። ከሥራ ታግዶ ሁለት ሳምንታትን እንዳስቆጠረ ታሪኩን ይከታተሉ የነበሩ የብሪትሽ ካውንስል ሃላፊዎች እንግሊዝ አገር ለንደን ከተማ ውስጥ የኦፔራ ሴንተር በአዘጋጅነት የስኮላርሽፕ እድል እንደተሰጠው ተነገረው።

ወደ እንግሊዝ አገር ለሁለተኛ ጊዜ ከመሄዱ በፊት ስኮላርሽፕ በሰጡት እና ጉዳዩ በሚመለከታቸው የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት መካከል ስምምነት ነበር። ጨርሶ ሲመለስ እንደ ገና ከሥራ የመገለል ችግር እንዳይገጥመው በማሰብ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቲያትር አርቲስቲክ ዳይሬክተር ሆኖ እንዲሰራ ስምምነት ተደርሶ ወደ ውጭ ሄደ። አቶ አባተ በእንግሊዝ የነበረውን የትምህርት ቆይታ አጠናቆ ወደኢትዮጵያ እንደተመለሰ አብዛኛውን የሥራ ዘመኑን ያሣለፈው በብሄራዊ ቲያትር እና በአዲስ አበባ ማዘጋጃ የቲያትር ና ባህል አዳራሽ ነው።

ጋሽ አባተ መኩሪያ ከቲያትር አዘጋጅ በላይ የነፍስ ታሪክ አዘጋጅ፣ የኢትዮጵያ የባህል ድምጽ ጠባቂ እና ያለፈውን እና የአሁኑን ድልድይ ነበር። በእሱ ዝግጅት የተዳሰሰ ተውኔት ሁሉ የተውኔትን ጽሑፍ በቃል ከማነብነብ ይሻገራል። ማህበረሰቡን፣ ታሪክን፣ ዘመንን፣ ትውልድን በአንድ የዋጀ ነበር። በትህትና እና አላማ የህዝቡን የተስፋ፣ የትግል እና ህልም ክብደት ተሸክሞ ያልተነገረውን ለመናገር የሚያስፈራውን እና ሀይለኛውን ባለጊዜ በኪነጥበብ ለመሞገት ደፍሯል።



በጋሽ አባተ የዝግጅት መስኮት በኩል ካለፉት ተውኔቶች ከበርካቶቹ መካከል እነዚህ ይገኙበታል።

1. ሀሁ በስድስት ወር (1966)
2. አቡጊዳ ቀይሶ (1971)
3. መልዕክተ ወዛደር (1971)
4. የመንታ እናት (1971)
5. መቅድም (1972)
6. ጋሞ (1973)
7. ኦቴሎ (1973)
8. ቴዎድሮስ (1973)
9. ሐሙስ (1978)
10. አሉላ አባነጋ (1979)
11. ያላቻ ጋብቻ (1980)
12. ታርቲዮፍ (1980)
13. ኤዲፐስ ንጉሥ (1988) ይገኙባቸዋል ።

**የእሁድ ሰበዞች የሚባል ፕሮግራም ስለጋሽ አባተ ባዘጋጀው ዝግጅት ላይ ከተጋበዙት ወዳጆቹ መካከል ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ ባዬ ጋሽ አባተ ደጋግሞ ያነሳት ነበር ያላትን ግጥም በጽሑፌ ለማካተት እወዳለሁ። ግጥሟ ካሊዳሳ ናት። "salutation to the Dawn" ይላል ርዕሷ። ካሊዳሳ ከጥንታዊ ህንድ ታላላቅ ገጣሚዎች እና ፀሃፊዎች አንዱ ነው።**

## እንሆ ግጥሟ

"Salutation to the Dawn
Look to this day!
For it is life, the very life of life.
In its brief course lie all the verities and realities of your existence:
The bliss of growth,
The glory of action,
The splendor of beauty.
For yesterday is but a dream,
And tomorrow is only a vision;
But today well lived makes every yesterday a dream of happiness,
And every tomorrow a vision of hope.
Look well therefore to this day!
Such is the salutation to the dawn."

**ከነገሩ ሁሉ መጨረሻ ስለ ጋሽ አባተ መኩሪያ ስራዎች እና አበርክቶዎች ሰምተን፣ አንብበን ስንጨርስ ልንል ምንችለው ጋሼ ዛሬውን በደንብ ኖሮ እኛም የነገዎቹ ልብ ውስጥ ታትሟል ነው። እንሆ መጨረሻው እጥፋት ጋር ደረሰ እና ሐምሌ 14፣ 2008 የኢትዮጵያ የትያትር ልብ አንጋፋው መራሄ-ተውኔት አባተ መኩሪያ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።**

**ምንጭ ፡- ሰዋሰው.com**
**ታሪካዊ መዝገበ ሰብ**

# ስሜትን ፍለጋ-አንድ

*ወ/ሚካኤል አዳሙ(ዕዝራ-ዘዓብ)*



አዎ! ይህም አንድ አለም ነዉ። ልክ እንደዛኛዉ አለም እዚህም ትላንት ለነገ ብለን ያስረከብናት ሌሊት አዳራዋን ተቀብላ ህይወትን ለዛሬ ታደርሳለች። ህይወትም "መኖር" በሚባል ሰረገላ ተጭና እንደ ልማዷ ዛሬንም ትሰናበታለች- ወደ ሌላ ነገ። ነገር ግን አሁንም የተጥበረበረ፣ የተዘበረቀረቀ የስቃይ ወይንም የፍስሃ ይሁን የማናዉቀዉ ጠባሳ ከኋላዋ ይከተላል- ታሪክ!

ሞት ያነቃዉ ዝምታ! ደግሞ ፍቅር የበላዉ ማንነት! ሰዋዊነት ያሸነፈዉ ሀይል! ዉሸት የዋጠዉ እኔነት!!

ዛሬም ሞትን ጥልቅ በመሰለ ዝምታ፣ ዝብርቅርቅ ባለ እስትንፋስ፣ ማስመሰል የሚባል ቃል ባሸነፈዉ ስጋ ህይወት "መኖር" በሚባል ምናባዊ ዉሸት ወደ ፊት ትቀጥላለች። ነገር ግን አሁንም ፍቀርና ማንነት በዉሸትና በማስመሰል እየተሸነፉ ይኖራሉ።

ይህ ከእለታት አንድ ቀን ብሎ የሚጀምር ታሪክ አይደለም። ምክንያቱም ለዚህ ታሪክ ባለቤት "አንድ ቀን" ማለት ተስፋ እንጂ በሆነ ሰዓት የተኖረ አልያም የሚኖርም ትዝታ ሆነ ታሪክ አይደለምና። ቢሆንም ግን አሁንም ሞት ያነቃዉ ዝምታ፣ ፍቅርም የበላዉ ማንነት፣ ሰዋዊነት ያሸነፈዉ ሀይል፣ ዉሸት የዋጠዉ እኔነት እዚህ አለ!!

ይቺህ ሀገር ኢትዮጲያ ትባላለች። እዚህችም ሀገር "አለዉ አለዉ" ማለት ደግሞ መዉደም፣ መሰልጠንና መጥፋት፣ መኖርና መሞት፣ መነሳትና መዉደቅ እንዲሁ አለ። ታሪክ ይፈጠራል ደግሞ ይሞታል። እዚህም እንዲሁ ይደረጋል። አለም ዉስጥ አለም፣ ሀገርም ዉስጥ ሀገር፣ ኢትዮጲያም ወስጥ ኢትዮጲያ አለ!! ታዲያ ይቺህ ሀገር እንደዛ ናት። ትላንት በዛሬ ያልተሸነፈባት፣ ዘመነዊነት ድሮን ያላጠፋባት፣ እንዲሁ ሁሉም በጥንድነት የፀናባት።

እና? በድሮ ለታ በእንባና በሀዘን ታጅበን ስናደምጥ የነበረዉ ነገር ግን "ህይወት ከኖረ ታሪክ ይቀጥላል!" ብለን ፍፃሜዉን ሳንደርስነት ያቆምነዉ ያ አሳዝዛኝ ታሪክ ከምን ደረሰ? ዛሬም "ህይወት" በተባለች ቁማርተኛ በመታለል "የሰዉ ልጅ" የተባለዉ ባለ ታሪክ (ዋና ተዋናይ) ያንን አሳዛኝ ታሪክ እንደተጫወተ አለ? ወይስ እኔና እናንተ እንዳሰብነዉ ቁማሯን በማሸነፍ የራሱን ታሪክ በደስታና በፍስሃ የሚተረክ ለማድረግ በቃ? እኔም የምነግራችሁ ይህንንኑ ነዉና።

በፍቅር ስም ታሪኩ ፍቅርን በማስቀደም ይጀምራል። በዚህ ታሪክ ዉስጥ ፍቅር ደግሞ እንደዛ ያደርጋል - ፍፁም ባዶ! እንግዲህ ተፈጣሪ ሆይ እያስተዋልክ ነዉ? አሁን ያቺ ቁማርተኛ ህይወት ጉዱ ፈላ ማለት ነዉ። ለምን? ምክንያቱም የጨዋታዉ መሪ ተዋናይ የሰዉ ልጅ አሁን ጨዋታዉን ለማሸነፍ ምንም ፍላጎት የለዉም። ምክንያቱም “ፍቅር እራሱን አጧል!”።

ታድያስ! ፍቅር ለሰዉ ልጅ እራስን ማጣት አይደለም? እና አሁን ያቺ ቁማርተኛ ምን ታድርግ? መችስ ስሜት አልባ የሆነን ተጫዋች ማሸነፍ ለአሸናፊዉም ስሜት አይሰጥም አደል? ቢሆንም ግን እሷ ምርጥ ቁማርተኛ ናትና ጨዋታዉን ማዞር አያቅታትም።

እራሱ ፍቅርንም የጨዋታዉ አንድ አካል ታደርገዋለች። አዎ! ካርታዉ ወደ ፍቅር ይዞራል። ይህ ከሆነ ደግሞ “ፍቅር ከሌለበት ገነት፣ ፍቅር ያለበት ሲኦል ይሻላል!” ብሎ አምላኩን እንኳን ሳይቀር አሻፈረኝ ያለ አፍቃሪ (የሰዉ ልጅ) እራሱንም ቢሆን አስይዞ ከመቋመር ወደ ኋላ አይልም።

አሁን ጨዋታዉ “ፍቅርን የማሸነፍ” ጨዋታ ይሆናል። የሰዉ ልጅ ካሸነፈ አፍቃሪ በመሆን እራሱን በመተዉ ወደ ባዶነት ይቀየራል። ድሉ ለዛች ቁማርተኛ ህይወት ከሆነ ግን ፍቅር ከማሸነፍ ባሻገር በሰዉ ልጅ ላይ የምታደርገዉ ትልቁ በቀልና ምታገኘዉ እርካታም ይሆናል።

አንድ ቀን አዳም አይኑን ወደ ላይ አነሳ። ምን አየ? ልዩ ፍጥረት- ሄዋን!! በዚህች ቅጽበት ጊዜ መዘዉሯን ጥላ ቆመች።

በፍቅር ጊዜ በራሱ መለኪያዉ ምንድነዉ? እልፍ አእላፍ አመታት በፍቅር ዘንድ ስንት ናቸዉ? ምንም ናቸዉ። ለምን? አንድም ፍቅር ከመሆን ወደ አለመሆን ደግሞ ከአለመሆን ወደ መሆን የሚያደርስ ጉዞ ነዉና። ሁለቱም መድረሻቸዉ ያዉ “ባዶነት” ነው።

አዳም እራሱን የመርሳት ጉዞ በዚህች ቅጽበት ጀመረ። ሄዋን እፊቱ ቁጣ እላይዋ ላይ ከተንዠረገገዉ ትልቅ ዕጽ ፍሬ ልትቀርጥ ትታገላለች። “አምላክ ስለ ምን ቁመትሽን ይህንን ታክል ብቻ አደረገዉ?” ያለ ይመስላል አዳም በዉስጡ። ፍሬዉን ልትይዝ ከታች ወደ ላይ በእግር ጣቶቿ ስትነሳ አዳም በተቀመጠበት አብሯት ወደ ሰሚ ይፈናጠጣል። እንደ እድል ሁኖ ሳይሳካላት ቀረ። ተናደደ አዳም።

መሞቻዉ መሆኑን ባወቀ!! ከተደጋጋሚ ሙከራና ዉድቀት በኋላ ተስፋ በመቁረጥ እዛዉ ዕጹ ስር ከፍቷት ተቀመጠች። አልቻለም አዳም!! ቁመቱን ሊያበድራት ፈለገ። ቁመትን ማዋስ ይቻላልን? በፍቅር ምን የማይቻል ነገር አለ?

ሂዶ ሊያባብላት ፈለገ። ግን ፍራቻ ዉስጡን ወረረዉ። “ንዴቷን ብትወጣብኝስ?” ሲል አሰበ። በእዉነቱ ብትወጣበትና ባለፈላት በወደደ። ግን የመጨረሻዉን ጥፊ “ሁለተኛ እንዳላይህ!” ከሚል ማስጠንቀቂያ ጋር ብታከናንበዉ ምንም እንደሚዉጠዉ ምን ሊዉጠዉ ነዉ? ስለዚህ ፈራ። ግን ተስፋ አልቆረጠም። ምናልባት ጥሩ የማጽናኛ ቃል ከያዘ ልታዝንለት እንደምትችል አሰበ። አእምሮዉ ዉስጥ ቃላትን ፍለጋ ገባ። ለምን አይሆንም? ቃል ስጋ ሁኖ የለ?

በመጀመሪያ የመጡለትን ቃላት አገጣጥሞ "እመቴ ዉዴ ሆ! አምላክ ምንም ያህል አጭር ቁመት ቢሰጥሽ እንዳትከፊ ምክንያቱም እኔ ረጅም ባሪያሽ አለሁና! ይህ ዕጽ ምንድነዉ? አንቺ ካልሽ ጨረቃንም በመጀንጀን ከክዋክብቶቹ እንዷን ከሰማይ ላይ አወርድልሻለሁ።" ይህንን ሊላት ፈለገ።

(አባታችን አዳምም ያኔ ያቺን ቆጅንጅየ እናታችንን እንዲሁ ይላት ነበር አሉ።) ሆኖም ግን ይህ ቃል እንደሚያጽናናት ምንም እርግጠኛ ሊሆን አልቻለም። ስለዚህ ተጨማሪ ፍለጋ ተነሳ። ድጋሚ አጣመረ "ዉቤ ሆይ አትከፊ ስትከፊ አልወድም፤ እሞታለሁኝ!!" የሚል።

"ኡህ የተሻለ ይሁን?" አሰበና እየደጋገመ አጠናዉ። ይህንንኑም እያደረገ እራሱን መርሳት ጀመረ። ተጠግቶም ቃላቶቹን አፈስሰላት። ሄዋንም ቀለጠች። የተጠቀመዉ ቃል ግን ቅድም ያሰበዉን አልነበረም። እሷ እንባዋ ይፈስ ጀመር። አላስቻለዉም። እቅፍ አደረጋት። ተጣበቀችበት። እንባዋን አበሰላት። ዉብ ከንፈሮቿን ሳመላት። አንድ ላይ ደግሞ አለምን ጥለዉ ኮበለሉ። ልክ እንደመጀመሪያዎቹ። በቃ ሄዱ።

ከቆይታ በኋላ ሄዋን በድንገት ተስፈንጥራ ተነሳች። አዳም ደነገጠ። ፊቷ ያገኘችዉን ረጅም እንጨት (ለመጥ) አነሳች። እላይዋ ያለዉን የዕጽ ንዴት በሚመስል መልኩ ስትለዉ እንዷ ተፈናጥራ ወደ አዳም አይን ስትሮጥ ሌሎቹ እዛዉ ምድር ላይ ረገፉ። አዳምም አሁን ገና ነበር በድንጋጤ አይኖቹን ይዞ ይህንን ሁሉ ያደረገዉም በምናቡ መሆኑን ያረጋገጠዉ። ቢሆንም ግን የፍቅርን አምላክ ሳያመሰግን አልቀረም። ለቅጽነታትም ቢሆን ፍቅርን ሊያይ ተችሎታልና!!

ሄዋን በጥበብ ያወረደችዉን ፍሬ ወሰደችና ቀደም የተከፋችዉን ያህል በተዓምራዊ ፈገግታ ትገምጠዉ ገባች። አሁንም እሱ ለየለት በቃ! አብሯት እየገመጠ ያለ መሰለዉ። እየደጋገመች ገምጣ ጨረሰችዉ። ድጋሚ አንዱን ፍሬ ከምድር አነሳች። አዳም ወደ ከንፈሮቿ የምታስጠጋ መስሎት አብሮ ሊወስድ የስራኛዉ መንጋጋ ጥርሱን ከላይኛዉ አጋጨ። ሆኖም መኖ ቀረ። ምንም እንደነካት ባይታወቅም ፍሬዉን ወደ ከንፈሮቿ አድርሳዉ መለሰች። ያቺን ፍሬ እንደያዘች እየፈነደቀች ሰማይ ምድሩ እንደጠበዉ እንበሳ እየቦረቀች ከአይኑ ተሰወረች። እሱም በዐይኖቹ ሸኛት።

አሁን ያቺ ቁማርተኛ ህይወት በመሃል ገብታ መሆን አለበት። ተነስቶ ለመራመድ ሲሞክር ሰዉነቱ በመላ ደንዝዟል። በሚጎረብጥ ድንጋይ ላይሳይታወቀዉ ይህንን ያህል መቀመጡን አሁን ገና ለማሰብ እየሞከረ ነዉ። ተንስቶ ሰዉነቱን እንደምንም አፍታታ። ሄዋን በጥበቧ ወደ ምድር የጣለቻቸዉን ፍሬዎች ተመለከታቸዉ።

አንዱን ወስዶ ነሳ። በቅጽበት ደግሞ አንድ ድምጽ በአንጎሉ ተቀረቀረ። ድምጹን መልሶ ለመስማት ሞከረ። “ከዚህ ፍሬ የበላህ ቀን የሞት ሞትን ትሞታለህ!” የሚል ነበር። እራስ ቅሉን ወደ ምድር ደፍቶ ያነሳዉን ፍሬ እጁ ላይ አፈጠጠበት። “አንዴ አብሬያት በልቼ የለ እንዴ?”ሲል መልስ ሰጠ።

አዎ እሱ የሚያምነዉ ያንን አንድ የዕጽ ፍሬ በፍቅር አምላክ ስም አብሯት እንደተጋመጠ ነዉ። ያልገባዉስ ይልቅ “ሁለተኛዉን ፍሬ ለምን ወደ ከንፈሯ አድርሳ ሳትገምጠዉ መለሰችዉ?” የሚለዉ ነዉ። “ሌላ አብራዉ የምትበላዉ አዳም ይኖራት ይሆን?” ሲል አሰበ። “ወትሮስ ከአምላኳ ይልቅ የእባብን ድምጽ የሰማች ሄዋን. . . “ ያሰበዉን ሳይጨርስ አቆመዉ።

ለምን? ምክንያቱም ሄዋን ምንም ብታመነዝር አዳም እሷንከማመን ወደ ኋላ አይልምና ነዉ። አሁንም ለምን? ምክንያቱም አዳም ምንም ጌታዋ ቢሆን ሄዋን ደግሞ ብልጥና ጠቢብ ናትና ነዉ። አዳም ምንም ያህል ቢያምናትም “ይሆን?” የሚል የጥርጣሬ ቃል አጦ አያዉቅምና ነዉ።

የጨበጣትን አንዲት ፍሬ ይዞ ወደ ቤቱ ገባ። በደህና ቦታም አኖራት። ከሄዋን ወደ እርሱ ዘንድ የመጣች የመጀመሪያዋ የትዝታቸዉ አካል ናትና። ከአልጋዉ በጀርባዉ ተንጋለለ። ሀሳቡን ደግሞ መልሶ ወደ እሷ ዘንድ ላከዉ። መልዕክተኛዉ ሀሳብ ግን ከትዝታዉ ጓዳ ብቻ ያለፈዉን ደጋግሞ እያመጣ ያሳየዋል እንጂ ምንም አዲስ ነገር ጆባ ሊለዉ አልፈቀደም። እሱም ቢሆን ይህንን ክስተት በራሱ አልጠገበዉምና አልከፋዉም።

እራሱን ከእሷ ጋር እያነጻጸረ ብዙ አለ። የሚያስበዉ ነገር ግን ፍጻሜዉ ሁለት ብቻ ነዉ። “ፍቅርና በደል” ስለእሷ ሲያስብ ሁሉም ነገር ተዓምር ነዉ። ወደ ቀረዉ አለም ሲመለስ ግን ከእሷ አንጻር ምንም ነዉ። የተበደለ። አሁን አንድ ነገር አሰበ።

“ተፈጥሮ እንደምታዳላ” ቀጠለ። “ለሷ እሷ የፈለገችዉን ብታደርግ ሙሉ አካላቷ ይተባበሩዋታል። ረጅም ጥቁር ፀጉሯ ለሷ ባሪያዋ ነዉ። ተባዕቱን አደለም እንስቱንም ጭምር ያስገዛላታል። አይኖቿ ለ’ሷ አስማተኞች ናችዉ። አትኩሮ የተመለከታቸዉ እሱ በቃ አበቃለት።

የአስማት ስራ እንዴት ነዉ? አዎ!! አፍንጫስ ከመተንፈስ ሌላ ጉዳዩ ምንድነዉ? የ’ሷ ግን አምላክ የፊት ቅርጿን ተጠቦ እየሰራ ለሌላ ተጨማሪ ዉበት ብቻ የሰራላት ነዉ ሚመስለዉ። አምላክም በራሱ ስራ ፈት መሰለዉ። “እንዴት አንዲትን እንስት ለመስራት ሲል ጊዜዉን ያጠፋል?” ሲል። ታዲያስ እንዲሁ የተቆሰቆሰ አእምሮ ምንንስ ከማሰብ ወደ ኋላ ይላል?

አልበቃዉም ቀጠለ። ከንፈሮቿ ለ'ሷ ለመሳም አይደለም የተፈጠሩት። ለዉበት ብቻ ነዉ። ምክንያቱም የሚያልቁ ስለሚመስሉ ነዉ። ጥፍጥና ከአእምሮ በላይ ሁኖ ያዉቃል? ከሆነ ይህንን ጥፍጥና ማን መጨረስ ይሻል? ዘለዓለም የአይን ምግብ እንዲሆኑ ብቻ መተዉ እንጂ! የሚያስበዉን ለአፍታ ሲገታ አንድ የሀሳብ ሞገዱን የጣሰ ሀሳብ ሲመጣ በአፉ ተናገረዉ። "እኔማ ሞትኩኝ!" በማለት።

አምላክ ለሷ ያጠፋዉን ጊዜ እያሰበ ወደ እሷ ደግሞ ተሻገረ። "እሷም ምን አለበት ብታርፍ? ረጅም ፀጉር አለኝ ብሎ የዕጽ ፍሬ በማዉረድ ሰበብ ወንድ ፊት ንፋስ ላይ ማዋል፤ አስማታዊ አይን አለኝ ብሎ እየተከፉ መደሰት፤ ተዓምራዊ ከንፈር አለኝ ብሎ ወንድ ፊት ፍሬ መግመጥ።

ይህ ሁሉ ምን አለ ቢቀር?" እሷ ግን መልስ ልትሰጠዉ አልፈቀደችም። ተገረመ በቃ! ምነዉ ብሎ ሲያስብ ይህንን ሁሉ ተከትሎ የሚመጣ ነገር አለ- ፍቅር!!

የሰዉ ልጅ ፍቅር የሚይዘዉ ከተፈቃሪዉ ወይስ ከተፈቃሪዉ ዉበት? አፍቃሪስ? የሚያፈቅረዉ አካሉን የወረሰዉን የማይለየዉ መንፈስ ወይስ እራሱ ሰዉነቱ ገላዉን? የልብስ ጉዳይ እዚህ ጋር ምንድነዉ? እሱማ የሂደቱ ስራ አስፈጻሚ ነዉ። ፍቅሩ ያበቃለት ግን የመጀመሪያም የመጨረሻም ተጠቂ የሚሆነዉ እሱ ራሱ ነዉ። እስከዛ ድረስ ሌላዉ በሙሉ ዜሮ ሁኖ ቁጭ ይላል።

አዳም ሳምንቱን በሙሉ በዚህ ሀሳብ የሚሆነዉን እያጣ አሳለፈ። በሳምንቱ ድጋሚ ሊያገኛት ወሰነ። በባለፈዉ ሳምንት በዛቹ እለት በዛቹ ሰዓት ተገናኛት። ከወዲያኛዉ ማዶ የኮሪደር ጥግ ቀጥ ብላ ስትመጣበት። የቀሚስ ሞደሊስት መስላ ታየችዉ። "የቀሚስ ሞደሊስት ደግሞ ምን ማለት ነዉ?" ብሎ በዛዉ ተሻገረ። "ንፋስም ያንቺ አሽከር ነዉ?" ሲል ተናገር ለራሱ። ያ ፀጉሯም ቀሚሷም አየር ላይ በመዋላቸዉ።

እራሱ ጋር በሃሳብ ሲሟገት አጠገቡ ደርሳ ልታልፈዉ ስትል ግድግዳዉን ተደግፎ ዘጋባት። እነዛ አስማተኛ አይኖች ከመቸዉ ወደ ስራቸዉ እንደገቡ ሳያዉቀዉ ጦራቸዉን ቀሰሩበት። ለጥቂት ጊዜ እሱም በራሱ አይኖች ተማፀናቸዉ። "አሻፈረኝ!" አሉ።

የደጋናቸዉን ቀስት ቢወረዉሩ መድረሻቸዉ ልቡ ላይ ሆነ። የሚቀጥለዉ ስራ የከንፈሮቿዋ ነዉ። ዉስጧ ከሚመላለሰዉ ሀሳብ አንዱን ይዛ ልታቀብለዉ ብትሞክር ግራ በመጋባቷ አልቻለችም። ይልቅስ እራሳቸዉ ከንፈሮችዋ ይረጥቡ ጀምር። አዳምም ይህ የሚረጥብ ከንፈር ቢጎርስ ለሚደማ ልቡ መልካም እንደሆነ አሰበ።

የሚችለዉን ያህል በአእምሮዉ ከወዲያኛዉ ጥግ የሚመጣዉን ሀሳብ ለማስቆም እየታገለ ከንፈሮቹን ወደ ከንፈሮችዋ አስጠጋ።

ሁለቱም ከጓላቸዉ ሽፋን የሚሰጣቸዉ ተዓምር ቢፈጠር እያሉ ሲያስቡ ተፈጥሮ ተባበረቻቸዉ። በንፋስ መልክ የሞዛርት ዜማ በጆሮዋቸዉ በኩል ይፈሳል። የዚህን አለም ማህበራዊ ህግ ወደ ኋላ ትተዉ አንድ ሁነዉ ሊዋሄዱ ፈለጉ። ማነዉ በዚህ አለም ህግ ፍራቻ ያሰበዉን ሳያደርግ የቀረ? አዳምና ሄዋን ግን ይህንን አደረጉ።

በሞዛርት ሙዚቃ እየታጀቡ፣ በሽክስፒር ተዓምራዊ ቃላት እየተማረኩ፣ በዳቬንቺ ቀለማት እራሳቸዉን በምናብ እየሳሉ፣ በሶቅራጠስ ሀሳብ እራሳቸዉን እያናናሩ፣ ደግሞ በክርስቶስ ፍፁም ፍቅር እኔነታቸዉን እየረሱ ወደ ፍፁም ባዶነት ተቀየሩ። አዎ! ፍቅር ቅጽበታትን ወደ ዘለዓለማዊነት ይቀየራል።

ድንገት ግን ሞዛርት ያንን ሙዚቃ አቁሞት ይሁን በማይታወቅ ሁኔታ ስሜታቸዉ ሂዶ ከተከረቸመበት ቦታ ሲደርስ ቀጥ አለ። ሄዋን እነዛን አስማተኛ አይኖች ድጋሚ አነጣጠረችበት። አዳም ምንም ያህል ቢፈራም በዛ ዉብ ስሜት ዉስጥ ለመቆየት ሞከረ።

ከንፈሮቿንም ድጋሚ ልትጠቀምባቸዉ ሞከረች። ግን አልተቻላትም። ፍቅር ባዶ ያደርጋል። ይህም የፍፁምነት ትክክለኛ ትርጓሜ ነዉ። እራስን በማጣት ጀምሮ ሌላን ወደ መሆን ያደርሳል። አዳም ግን ተባበራት። ልታወጣ ያልቻለችዉን ቃላት ታወጣ ዘንድ አገዛት። ሆኖም ግን በመናገር ሳይሆን በዝምታ። በቃላት ሳይሆን በምናብ መናገር እንደሚቻል አስተማራት። ራስ ቅሉን አስተካክሎ ከግድግዳዉ ካሳረፈ በኋላ “እሽሽሽ” በማለት በጣቶቹ ከንፈሯን ዘጋቸዉ። እሷም ፀጥ አለች። በመሃከላቸዉም ዘለዓለማዊ የሚመስል ዝምታ ተፈጠረ።

አዳም ዝምታዉን ሰብሮ “በዝምታ ብቻ እንዳፈቅርሽ ፍቃድሽ ይሁንልኝ?” ሲል ተናገረ። እሱ ዝምታን አስተማራት እሷም ተማረች። በአርምሞ ያወሩም ጀመር።

በፍቅር እራስን ማጣት ማለት እራስን በመተዉ ያፈቀርነዉን እሱን መሆን ማለት ነዉና። የልባቸዉን ለራሳቸዉ ልብ መልሶ እንደማዉራት ሁሉ በዝምታ በአንድነት በመዋሄድ አወሩ። ድጋሚ ጊዜ መዘዉሯን ጥላ ቆመች።

እኔነት አበቃ! የአልም ህግ ተፈፀመ! አይን አያይም፤ ጆሮም አንዲት ኮሽታ አይሰማ፤ አእምሮም ሀያልነቱን አጣ። ሁሉም በቅጽበታት ባዶ ሁኖ ቁጭ አለ። አዳም በፊት ያልተሳካለትን ከንፈር ያለ አንዳች ስሜት ከከንፈሯ ጋር አገናኘዉ። ዉበትንም ፈጠረ!! አሜን!!!

ይቀጥላል . . .

# ባይራ ውይይት

ይህ አምድ የባይራ ዲጂታል መጽሔትና የአንባቢዎች የሃሳብ ማንሸራሸሪያ ነው። በየጊዜው ከመጽሔቷ አዘጋጆች ወይም ከአንባቢዎች የመወያያ ጥያቄዎች በባይራ የፌስቡክ ገጽ ይለቀቃሉ።

ሃሳቡን ማጋራት የፈለገ ሁሉ ግሩፑ ላይ ይጽፋል። ከተሰጡት ሃሳቦች ወይም ምልከታዎች ውስጥ ከመጽሔቱ ቢካተት መልካም ነው ብለን ያሰብነውን ወደ እናንተ እናጋራለን።

ይሔም መጽሔቱን ከማንበብ ባሻገር በመካከላችን ያለውን የሐሳብ ምልልስ ያጎለብታል። ለአንባቢዎቻችንም መድረክ ለመፍጠር ያስችላል። በውይይት ወቅት ሁላችሁም ሃሳባችሁን ታካፍሉን ዘንድ እንጋብዛለን። እንድንወያይበት የምትሹት ሃሳብ ሲኖርም ብትልኩልን በደስታ እንቀበላለን።

# ኑኒ ባይራክ!

# መንገደኛው

አንድ መንገደኛ ነበር። በመንገዱ ላይ ሳለ ድንገት ሳያውቀው አውሬዎች በሚኖሩበት የጫካው ክልል ይገባል። ወዲያውኑ አንድ አውሬ ይመለከታል። ከአውሬውም ለመዳን ሩጦ ከገደል ስር ይደበቃል። ቁልቁል ሲመለከት ከገደሉ ስር ዘንዶ አፉን ከፍቶ ሊውጠው ይጠባበቃል። በዚህ የተደናበረው መንገደኛ ከገደሉ እንዳይወጣ አውሬውን ፈራ። ወደታች እንዳይወርድ ዘንዶውን ፈራ።

ምንም አማራጭ ስለሌለው ከገደሉ መሐል ላይ ሆኖ የዛፍ ስር በእጆቹ ይዞ ይንጠላጠል ጀመር። ድንገት እጆቹ እየዛሉ ሄዱ። ይባስ ብሎ አንድ ጥቁርና አንድ ነጭ አይጠ መጎጦች በሌላው ጫፍ ያለውን የዛፍ ስር በጥርሳቸው ለመቁረጥ ይታገላሉ። በሂደት የዛፉ ስር መቆረጡ እንደማይቀር ማሰብ ጀመረ። ስሩ ከተበጠሰ ከታች አፉን ከፍቶ በሚጠብቀው ዘንዶ መሰልቀጡ እሙን ነው። ይሄም እጅግ ያስጨንቀው ጀመር።

በዚህ ሁሉ ሽብር መካከል እያለ ከዛፉ ቅጠሎች ላይ የተንጠባጠቡ የማር ወለላዎች ከዚህ ተስፉ ቢስ መንገደኛ ከንፈር ላይ አረፉ። እሱም የማሩን ጣዕም እያጣጣመ ለአፍታም ቢሆን የተደቀኑበትን የሞት መንገዶች ረሳ።

*ይሄ ታሪክ ታላቁ የሩሲያ ደራሲ ሊዮ ቶልስቶይ (Leo Tolstoy) A Confession and Other Religious Writings በሚል መጽሐፉ ላይ ያካተተው ነው።*

**ይሄ ታሪክ ለማስተላለፍ የፈለገው ፊትለ ነገር ምን ይመስላችኋል?**
**ከዚህስ ምን መረዳት እንችላለን?**
**ሃሳባችሁን በነጻነትና በመሰላችሁ ሰፋ አድርጋችሁ ብትሰጡን እንወዳለን።**

# ከተወያይ የተሰጠ መልስ

*በዚህ ፅሁፍ ላይ ሁለት እይታዎችን በየተራ ለማስቀመጥ እሞክራለው።*

*በዚህ ተረት ውስጥ ተንዥ የሰውን ሁኔታ ይወክላል። ይህ ደግሞ እንደ ሰውኛ የህይወት አደጋን መጋፈጥን ያሳየናል። በመንገዱ ላይ ያጋጠሙት ጨካኝ አውሬዎች በሕይወታችን ውስጥ ሊያጋጥሙን የሚችሉትን ውጫዊ አደጋዎች እና ችግሮች የሚያመለክት ይሆናል። በቀጣይ ከጉድጓዱ በታች ያለው ዘንዶ ደግሞ ሊኖረን የሚችለውን ውስጣዊ ፍራቻ እና ጭንቀቶችን ይወክላል።*

*ስለዚህ ይህ መንገደኛ ሰው የተንጠለጠለበትን የዛፉ ቅርንጫፍ በሕይወታችን ውስጥ የምናገኛቸውን ጊዜያዊ ተስፋ እና ጊዜያዊ እፎይታዎችን የሚወክሉ ይመስለኛል። ሁለቱ አይጦች፣ አንድ ጥቁር እና አንድ ነጭ፣ ቀንና ሌትን የሚወክሉ ሲሆኑ በጥርሳቸው የሚገዘግዙት ቅርንጫፍ የሞትን አይቀሬነት እና የጊዜ መሻገሪያን ያመለክታሉ ብዬ አስባለው።*

*በጫካው ቅጠሎች ላይ ያሉት የማር ጠብታዎች በህይወት ውስጥ ልናገኛቸው የምንችላቸውን ትንንሽ ደስታዎች ናቸው። በጣም የሚገርመው እነዚህን የማር ጠብታዎች አንዳንድ ምሁራን ሞትንም እንደሚወክል ይናገራሉ። እንዴት ሲባሉ? “ከጭንቀት በሞት መገላገል በራሱ ይጣፍጣል” በማለት። እኔ ይሄንን ሀሳብ አልስማማበትም ነገር ግን እንደ ሀሳብ አስቀምጬው አልፋለው።*


*በጠቅላላው ተረቱ እንደሚያመለክተው የማይታለፉ የሚመስሉ ችግሮች እና መከራዎች ብሎም ሞት በየመንገዳችን ሊያጋጥሙን ቢችሉም አሁንም በህይወት የምናገኛቸውን ትንንሽ ተድላዎች እና ደስታን በመያዝ መታለል እንደሌለብንና ሂወትን በአጋጣሚና ድንገት ልንፋታት ስለምንችል በሂወት እስካለን መልካም እየሰራን በዙሪያችን ያለውን ልንከባከብ እና ልንደሰት ይገባል የሚል እሳቤን ይዟል።*

*ሁለተኛው እይታ ደግሞ አብዛኛው ምሁራን የራሱን ሂወት ነው የተረከው የሚለው ይሆናል። በሌላ እይታ አንዳንድ ምሁራን ይሄን ታሪክ በጉዞው ላይ ያለው ተጓዥ እራሱ ቶልስቶይ ሲሆን በህይወት ጉዞ ላይ መሆኑን ለማሳየት የሞከረበት ነው ይላሉ።*

*አስፈሪው አውሬ ና ተጓዡን ሊውጠው የሚጠብቀው ዘንዶ የማይቀር ሞትን እንደሚያመለክት ቶልስቶይ እየጠቆመን ነው። ሌላው ጥቁሩ እና ነጭ አይጥ ቅርንጫፍን እየገዘገዙ የሚቆርጡት ቀንና ሌትን የሚወክሉና እና የማያባራውን የጊዜ ጉዞ ለመወከል የገለፀባቸው ናቸው። የማር ጠብታዎቹ እና የተጣበቀባቸው ቅርንጫፎች ሁለቱን በሂወቱ በጣም የሚወዳቸውን ነገሮች የገለፀበት ነው።የመጀመሪያው ሚስቱ ስትሆን፣ ሁለተኛው ጽሁፉ ነበር።*

*ቶልስቶይ ይህን ታሪክ የሚናገረው በኋለኛው የህይወት ዘመኑ ያጋጠመውን አጣብቂኝ ስለሚወክል ነው። ምንም እንኳን በሂወቱ ውስጥ የተሳካ የፅሁፍ ስራ እና አስራ አራት ልጆች ቢወልድም, የሞት አይቀሬነትን፣ የህይወትን ከንቱነትን መስሎበታል። ስለዚህ ሕይወት ይቋረጣል እና እንዴት መኖር እንዳለበት እና ምን ማድረግ እንዳለበት ያየበት ፅሁፍ ነው። ሌላው በሁለት አውሬዎች መካከል በተሰበረው ቅርንጫፍ ላይ እንደተሰቀለው መንገደኛ እራሱ ቶልስቶይ በህይወቱ ሙሉ ቆሞ የነበረውና መልስ ያጣለት ነገር ከእግሩ በታች ወድቆ ምንም እንዳልቀረ የተረዳበት ነበር።*
#ኸታቢው_ዐይኔ

- በ Sabit Abdu



# “ተዓምሩ” ጫሌ፤ የወረ-ባቦው ንጋት


(ነቢል አዱኛ)

የእርስዎን ቃል ስንዋስ “ብድግ አርጎ ሲያበቃ!” ኸድር ታጁ ከዘገበልዎ ህይዎትዎ ጨልፈን ልናነሳሳ ነው። ጸሐፊ መዋዕልዎ እንዳለው “እነኾ!

ትውልድ እራሱን ዘንግቶ የሌሎች ጥላ እንዳይኾን፣ በኩረጃና በቅጂ ከመታመም እንዲድን፣ በእራሱ ኮከብ እንዲደምቅ - መጽሐፈ ‘ሼህ ሠይድ ኢብራሂም’ ከነ-ህፀፁ የአደባባይ ሻማ ኾኖ ቀርቧል። ጸሐይ ሞቋል።”

እርስዎ ማለት ገጣሚው እንዳለዎት ነው፡- “ሼህ ጫሌ ሐበሻ ተወልደው ባልነበር የሐበሻ ሰው ምንደር እያለ ያወጋ ነበር?” ከወረባቦ ፈልቀው ሀገር ምድሩን “ጉድ” ያሰኙ “ተዓምር” ነዎት። ያየዎት እና ያወቆት ብዙ ብሏል። “ሰው ኾኜ ተምፈጠር የሸኾቹን ዘለላ ጠጉር ብኾን እመርጣለኹ!” ተብለዋል።

መሬት ሰማዩን ነቅንቀው ሲያልፉ፣ ያጣዎት “ለካ ሰው ነዎት! መለክ(መልዓክ) ይመስሉኝ ነበር” አለ። ኾኖም አልተዘከሩም፤ አልታወሱም። ታሪክዎን ለራሱ የሰረቀ፣ ታሪክዎን በተቃራኒ የወሰደ ትውልድ መጥቷል። ይህን ትውልድ ቢያገኙት “ብድግ አርጎ ሲያበቃ!” ማንበብ እና መጻፍ ከዒልም እንጂ ከጀህል እንዳልኾነ ያሳውቁት ነበር።




## እናትና አባትዎ

በወላጆችዎ፣ በአራቱም አያቶችዎ

በኩል ከላይ ጀምሮ ዕውቀት የታጠቀ፣ በአምልኮ የበለፀገ ሥረ-ግንድ አለዎ። ከታላላቅ ሊቃውንት ቢጠራ ከተቀዳሚዎቹ ቤተሰቦችዎ ናቸው።

አባትዎ ሼህ ኢብራሂም ያሲን ሥም እና ግብራቸው የገነነ ልሂቅ ነበሩ። ዕውቀት የታጠቁ፣ ምንፍሥናን የተመረቁ፣ ነብዩ ሙሐመድን በማፍቀር የታወቁ፣ ለሌሎች በመኖር የደከሙ፣ ጽሑፋዊ አሻራዎችን ያተሙ ሊቀ-ሊቅ ነበሩ። ከእርስዎ እንደሚበልጡም ይዘከራል።

“ኑንያ”(ኑን/ ں በተባለው የዓረበኛ ፊደል ቤት የሚደፉ 81 ስንኞች ያሉት)፣ “ሚምያ”( ሚም/ م በተባለ ዓረበኛ ፊደል ቤት የሚደፉ 34 ስንኞች ያሉት)፣ “ዳልያ”(ዳል د በተባለ ዓረበኛ ፊደል የሚያልቁ 130 ስንኞች ያሉት) መድብሎቻቸው ይበልጥ ይታዎቃሉ። ሼህ ሠይድ ዑመር(አረባል) እንደሚሉት፦

*“ያዚነተና ያጧሃ ያሲን(ጌጣችን ነብዩ ሙሐመድ ሆይ!)*
*ጉዱን ወልዶታል*
*ኢብራሂም ያሲን።”*

እናትዎ እመት ዘቡራ ሙሐመድ መልክን ከዕውቀት የታደለች፣ ቁንጅናዋ ሳር ቅጠልን ሳይቀር ያዋለለ፣ በዕውቀትም ምሥጉን ነበረች። በወጣትነቷ ቁርዓንን ከነ-ሥርዓታዊ አነባበቡ፣ “ኢህያዕ-ዑለሙዲን” የተባለውን የታላቁን ፈላስፋ ኢማም አልገዛሊ(Al Ghazel) ኪታብ በቃሏ ያጠነጠነች ነበረች።

*“መገን ዘቡራ ወለደች ጉዱን*
*ያንን ሙሂቡን*
*ያን ሙጃሒዱን”*

እመት ዘቡራ ማህፀኗ ለፍሬ ሳይረዘቅ ረዥም ጊዜ ቆየች። ኋላም ከባሏ ጋር መከሩና ሊቃውንት ቤታቸው ጠሩ። “ልጅ ይቸረን ዘንድ ፀልዩ” አሉ። ዱዓው ቀጠለ። ምርቃቱ ተቀጣጠለ። ‹”አሏህ ሰባት ልጅ ይሰጥሻል›” አሏት። “ሰባት ስወልድ ሳሳድግ ለአላህ(ለአምልኮ) የምሰጠውን ጊዜ ይሻማብኛል፤ የሰባቱን የያዘ አንድ ይበቃኛል!” አለች። ሸኾቹም “የሰባቱን የያዘ አንድ አሏህ ይሰጥሻል” አሏት። ከዓመት በኋላም በ1874 ሼህ ሠይድ ኢብራሂም(ሼህ ጫሊ) ተወለዱ። እናታቸው እንዳለችው፦

*“እንደ ሰው ለማግባት ባገሬም አላጣሁ*
*ሠይድን ለመውለድ ገንደ-ጎራ ወጣሁ።”*

# እድገትዎ

ልጅነትዎ እንደ ፊት መልክዎ ኹሉ የጠየመ ነው። አባትዎ በተወለዱ በዓመቱ በ1875 አለፉ። በልጅነት የአባት እጦት ታቀፉ። አራት ዓመት ሲኾንም እናትዎም ለጠቁ። ወላጅ አልባ ኾኑ። በየቲምነት ተፈተኑ። አያትዎንም ተደገሙ። ይህ ክስተት ከነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ህይወት ጋር ይገጥማል።

“የክፉ-ቀን” ተብሎ የሚታዎቀው ረሃብ እዚያው ተከሰተ። የእርሻ ቀን አለፈ፣ ከብት እና ህዝብ ተረፈረፈ። እርስዎም ተብቻዎ ቀሩ። ኾኖም በ1882 ኢ.ል ሰባት ዓመት ሲኾንዎ ልጅነትዎን ‘ሚያንደላቅቅ፣ ዕጣዎትን የሚያስቅ፣ ዕድገትዎን የሚያሞቅ ኹነት በክሱትነት ፈለቀ።

የአባትዎ የልብ ወዳጅ የነበሩት ራስ ወሌ ጉግሳ፣ የአጤ ዮሐንስ ፬ኛ የሙስሊም አግላይነት ፖሊሲ በርሳቸው(አጤ ዮሐንስ) ሞት በ1881 ቲያበቃ የወዳጃቸውን ልጅ ፍለጋ መጡ። እርስዎን ወደ ቤተ-መንግሥት አመጡ።

“ከጌታው ሼህ ኢብራሂም ያሲን ልጅ ጋር ማንም እኩል አይኾን!” ብለው አንደላቀቁዎት። ጥቅጥቅ በግ፣ ወተት፣ መረቅ በላይ-በላዩ አጋቱዎት። “የሊቅ-ልጅ” ብለው ከቅዱስ ቁርዓን ንባብ ጀምረው አስተማሩዎት።

የቢትወደድ ወሌ ዓይን ሳይነቀልብዎ የፊቅህ ትምህርቶንም ተማሩ። እየተዘዋወሩ ሸመቱ። ከአፍላነትዎ ጀምሮ የሚናገሩባቸው ቃላት፣ የሚያወሩባቸው መንገዶች ቢትወደድ ወሌን ያስደንቃቸው ነበር።

በአንድ ወቅት ችሎት በተሰየሙበት እርስዎ ሊዘይረዋቸው መጡ። ቢትወደድ ወሌም ብዙ ቦታ እየዞሩ መማርዎን ተቃወሙ። “ለምንድን አንድ ቦታ እረግተህ የማትማር? ውሃ እኮ አንድ ቦታ ላይ ሲቆፍሩት እንጂ እዚያም እዚህም ስለቆፈሩት አይገኝም!” አሉዎ። እርስዎም “መገን ወሌ! ተፈልጌ የምቆፈረው እኮ እኔ ነኝ! መቆፈሪያው ነው በእኔ ላይ የተቀያየረው!” ለአስር ዓመትም ቤተ-መንግሥት ኖሩ።

ቢትወደድ ወሌም “የወዳጄን ልጅ ወግ ማዕረግ ልይ” ብለው ሊድሩዎት አሰቡ። እርሳቸውን “እሺ” እንደማይሏቸው ስለተረዱም ለመምህርዎ አሳሰቡ። ሸይኾም “አሉታ እንዳይወጣዎ” አሉዎት። “እኔ የአላህን የምስጢራት ቤት ታሳውቁኛልሁ ብዬ ነው እርስዎን የተጠጋሁ። የወሌን-የወሌን ቤትማ እዚያው እቤቱ አይደል ያለኹት? ከዛሬ ጀምሮ የእኔ እና የእርስዎ ግንኙነት አብቅቷል” ብለው መልሰው ከቤተ-መንግሥቱም ከመድረሳውም ሸፈቱ።

ሀገር እና መምህር እየቀያየሩ ቀሰሙ ተዘዋውረው በዕውቀት ጎለሰሙ። ኋላም

*“ልኬታዋ ተሰኝቶ ራቀ፥ ማኩራቷ አብቦ ፈነደቀ*
*ምስጢሯ ከበረ ጠለቀ፥ ብርሃኗ ለምድር ፈነጠቀ*
*ልህቀቷ ጥንት ተጠመቀ፥ የማይነበብ ደረጃዋ*
*ረቀቀ”*

ብለው የተቀኙላት “የጠቢባን አምባ፣ ዘመን ሳይነጋ፣ ጥበብ ሳይዘረጋ ብዙ የተከተተበት ሥልቻ፣ ለሃይማኖት ስንቅ፣ ለትውልድ ትጥቅ አስሰናቂ ዳርቻ” ወደ ኾነው ከቀድሞው የወሎ ክፍለሀገር በየጁ ጠቅላይ ግዛት ሥር ወደሚገኘው “ዳና” ዩኒቨርሲቲ አቀኑ።

ከአጤ ዮሐንስ፬ የግፍ በትር በኋላ እስልምና በኢትዮጵያ ጎልው ኾኖ እንዲቆይ ተቀዳሚውን ሥርፋ የሚይዘው ዳና የዕውቀት ማዕከል ነው። እርስዎ ከዳንዩል አወል እስከ ዳንዩል ሳኒ ድረስ ተማሩ።

“ርቡ! ስቡ!” ተብለው ተመርቀው ወደ ሀገርዎ ጫሌ አመሩ። በፊት በቅድመ አያታቸው የተመሠረተውን “ጫሌ - የዕውቀት ማዕከል”ን እንዳዲስ ገነቡት፤ ዳግም መሠረቱት። “ጫሌ - የዕውቀት ማዕከል፣ የጥበብ ማዕድ፣ የሥልጣኔ አውድ ተዘርግቶ እንዲፈሰስበት ዘንድ ለዘመኑ ተበረከተ።” ወዲያውኑ የዳግም ምሥረታው ዜና ተሠራጨ። ሁሉም ከሁሉም ቦታ ፈሰሰ። 2000 የሚደርሱ ደረሳዎች ተሰበሰቡ።

የትምህርት ማዕከልዎ እና ተማሪዎችዎ

*“ወረባቦ ላይ ማን ነው ያጉራራው*
*የዘቡራ ልጅ የገንደ-ጎራው (ሼህ-ጫሌ)”*

የዕጅ ጽሑፍን የተለየ ትኩረት ሰጥተው ማስተማርዎ እንዳለ ኾኖ በተደምት የሐበሻ ሊቃውንት ይስሰጡ የነበሩትን 12 የትምህርት ዘርፎችን አስተምረዋል።

*Exegesis, Islamic Juriorudnce, Arabic Grammer and Syntax, Morphology, Theology, Rhetoric, Logic, Prosody, Eloqunce, The science of metaphorsor of good style, The pronciple of law, The study of traditions of the prophet*። ደረሳዎችዎን ለስኬት አብቅተው አምጥቀዋል። በዕውቀት አንፀው አስመርቀዋል።

የራሳቸውን ማዕከል(ዩኒቨርሲቲ) የከፈቱ መቶዎች አብቅተዋል። ለዒልም የመጡ ደረሳዎችዎን እንደ ወንድምዎ እንደ ልጅዎ አድርገው ማኖሩን ከቀደምት የሐበሻ ሊቃውንት የተማሩት ነው። ደረሳዎ እድሜው ለትዳር የደረሰ ሆኖ ሲያገኙት እንደ አባት ኾነው የዳሯቸው በርካቶች ናቸው። አሥር የእርሻ መሬትዎን ተማሪዎቾን ረሃብ እንዳይፈትን ለነርሱ ቀለብ አውለዋል።

ዱዓ የሻቱ ምርቃት የፈለጉ ደጅዎን ያንኳኳሉ። የስጦታ ገፀ-በረከት ያጎርፍልዎታል። ቢኾንም ግን እርስዎ እንደመምህርዎችዎ ኹሉ በሲዋክዎ(ጥርስ መፋቂያ) ገፉ ያደርጉታል። ለደረሳዎች ያበረክቱታል። እንደ ቀደምት ሊቃውንት ለተማሪዎችዎ እጅ ሰጥተዋል። የደረሳዎን ድርሳን አንብበው በለቅሶ ተንፈቅፍቀዋል። “ብድግ አርጎ ሲያበቃ! እኛም ጻፍን እንላለን!” ብለዋል። በሐበሾች ዘንድ “እንደ ታምር” ይቆጠር የነበረውን የሐጅ ሥነ-ሥርዓት ተማሪዎችዎን እየመሩ ይዘው ሄደዋል።

ቸርነትዎ ዝናብ ነው፤ ሜዳ ድንጋይ የማይመርጥ። በልግስናዎ ብዛት ቤተሰብዎ ዕዳ ገብቶ ነበር። “ተተቀባዩ ይልቅ እኔ ሠጪው እደሰታለሁ” እያሉ ነበር የሚቸሩት። ሃብት ሲካብት፣ መኸር ሲገባ ሃዘንዎ ይመጣል። “እንዴት አከማቸቼ!” ይላሉ። የእርስዎ ተወዳጅ(ነብዩ ሙሐመድ) ውልብ ይልብዎታል። “እርሳቸውን ወድጄ ለመጣው ኹሉ መቸር ነው እንጂ ማከማቸት ተመንገዳቸው ማፈንገጥ ነው” ይላሉ።

የለበሱትን መሥጂድ ውስጥ ላገኙት ሰው ሰጥተው፣ የሚለብሱትን አጥተው በጋቢ ተጠቅልለዋል። አጤ ኃይለሥላሴ የሰጡዎትን ስጦታ ተነጥቅለሉ ለደረሶቾ እዚያው ሰጥተዋል። ስለርስዎ ተሰው አልፎ እንስሳቶች፣ ተቀላቢ ውሾቹ እና ከብቶቹ ይመሰክራሉ። ቸርነትዎ ቅጥ አጥቶ መለመን የፈሩ እንዲሰርቁዎ ኹኔታዎችን አመቻምቸዋል። ኹሌ ጫማዎትን የሚሰርቅብዎ ሰው አዲሱን ጫማዎን ሳይሰርቅ ሲቀር “ብድግ አርጎ ሲያበቃ! ኸዳማችን የት ሄደ?” ብለዋል።

## ሀገር እና የዘመኑ ሹማንቶች ጋር

ሁሉም የሐበሻ ሊቃውንት “ሀገርን መውደድ ከዕምነት ነው” የሚለውን የነብዩ ሙሐመድን(ሰ.ዐ.ወ) ንግግር ከራሳቸው በማስረፅ ስለሀገር አንብረዋል፣ ደም ገብረዋል። የየዕለት ዱዓዎ፣ 16 መድብልዎ፣ ከ350 በላይ ስንኝዎ ሀገር የሚል ነበር። በጢጣ ጦርነት የኃብተጊዮርጊስን ጦር ለመፋለም ወገንዎን ወክለው ተፋልመዋል። ኾኖም ድል የእርስዎ አልነበረምና ተማረኩ። ወዳጆቾ እነ ሼህ ላፍቶ ሲገደሉ ቀደርዎ አልኾነምና በነጣ ተለቀቁ። ለዚህም 1909 ምስክር ነው።

በዘመንዎ የነበሩ ሹማምንት እና ነገሥታት ለ’ርስዎ ሲያረግዱ፣ “ምን እናርግ? ምን ጎደለ?” ሲሉ፣ “ዕድሜዬ(ሥልጣኔ) እንዲረዝም ዱዓ አርጉልኝ” ሲሉዎት እርስዎ ግን እንደ ሌላው ዑመት አላሸረገዱም። ግፍ ሲበዛ፣ ግፈኝነቱ ሲንሰራፋ “ሥርዓት!” ሊሉ ወደ ቤተ-መንግሥታቸው ይሄዳሉ።

አቤቱታ ሊያቀርቡ። “ሊቃውንትን በደልክ! የመሻይኾችን መሬት ቀማህ!” ለማለት ተደጋጋሚ ወደ ሹማምንት ቀርበዋል። ግን አንድም ቀን ለራስዎ ጥቅም፣ ስለራስዎ እርሻ በአንበጣ መውደም፣ ሃብትዎን እየጀቡ ባዶ እጅዎን መቅረትዎን ተናግረው አያውቁም። “ጠይቁ እንጂ ይሰጥዎ” ሲሎዎት ወዳጅዎችዎ “ተአላህ እንጂ ተፍጡር ሃጃ የለኝም” ብለዋል። ግፈኛው ግፉን አላቆም ሲል ዱዓዎትን ይጀምራሉ።

ራስ ከበደ መንገሻ ግፉን ሲያዘወትር ዱዓ አደረጉበት። “ከበደ ቢከፋ፣ ጣልነው ወደ ከፋ” አሉ። “ራስ ከበደ ወደ ደቡብ ግዛት ተሹሞ ተዛወረ። እንደሚባለው ብዙ ሳይቆይ ተጎሳቁሎ ሞተ።”(317) ይህን የሚያውቀው የኢጣሊያ ጦር “ዱዓዎትን ያቁሙ” እያለ ማስፈራሪያ ሲልክብዎ ከርሟል።

ፋሽስት ኢትዮጵያን ወርሮ፣ ያገኘውን ሲገድል፣ ሲሰቅል፣ ሲገርፍ እርስዎም በክፉ ዓይን ታይተው ሁለት ጊዜ የስቅላት ትዕዛዝ ተላልፏል። “እንዴት ይንቀናል? ተጎናብሶ እጅ መንሳት ሲገባው! ዱዓ እያደረገ እንድንወገድ ይለምናል?” ተብለው ታድነዋል። እርስዎም እንደ ልማድዎ “ሚምያ” ድርሳንዎን በ352 ስንኝ አጠናቅረው “ሀገሬን ፈርጃት! ንጉሣችንን እርዳው! ጥልያንን አጥፋው!” ብለው የመረረ ጥላቻዎን በፋሽስት ላይ ገልፀዋል።

እንዲህም ኾነና ደጃች ጉግሳ አልዩ የወረ-ባቦ ገዥ ኾኖ ሲገባ ከእርስዎ መሬቶች(እርሻዎች) ውስጥ አንደኛውን ቀማዎት። ሚአ የተባለውን። እርስዎም ተቆጡ። የቃል ምልልስ ጀመሩ። “ይህ መሬት የመንግሥት እንጂ አይኾንም የግለሰብ” አለ። “ወንድ ከኾንክ ንካው!” አሉት። ዱዓዎትን ወጥረው ያዙ። ኋላ እሱን አጤ ኃይለሥላሴ ወደ ውጭ ላከው።

ሲመለስ ወሬ አዋሳጆች “ጫሎች ‘ላክነው’ እያሉ ዱዓ ላይ ነበሩ” አሉት። ከት ብሎ ስቆ “ቆንጆ ሴትና መሬት በረዥም ምንሽር እንጂ ቁጭ ተብሎ ዱዓ ስለተደረገ አይገኝም” አለ። ንግግሩ እርስዎን አስከፋዎት። ዱዓዎትን ናቀ፣ መንፈሣዊ ልዕልናዎን አንኳሰሰ። ወደ ወዳጅዎ ሼህ አብዱልወሃብ ኦዳ አቀኑ። “የርስዎ ረዥም ምንሽር ዱዓ አይደለም እንዴ?” አለዎ። 79 ረዣዥም ስንኞች ያሏቸው “ላምያ” “ኸንጀር” የተባለ መድብል አዘጋጁ። ደጃች ጉግሳን የሚረግም የዱዓ መጽሐፍ።

ከወዳጆችዎ ጋር ኪታቡን ከረሩ። ዱዓዎን ወረወሩ። ወደ አሏህ በረሩ። ከሼህ ሷልህ ጋር አመሹ፣ አነጉ። “ጉግሳ ተሰብሮ አሳየን” አሉ። ተልብ አለቀሱ። ደጃች ጉግሳ ለበዓለ ሲመቱ ደሴ ላይ ከነ አጤ ኃይለሥላሴ ጋር ድግስ አሙቀዋል። በልተው ተደስተው መጠጥ ይዞ ሲንጎራደድ በድንገት ወድቆ ሞተ። በእርስዎ የመንፈስ ቅሩብነት ነገሩ ተገለፀልዎ።

በሌሊት ሼህ ሷልህ ጋ አቀኑ። “ብድግ አርጎ ሲያበቃ! ጉግሳ ራሱን ተይዞ ቢፈጠረቅ ለደሴ ሰው አንገቱ በቃው” አሉ።

ደጃች ከበደ ዓሊ ወሌ እርስዎን ቢያከብርዎ እና ቢያፍርዎ ልጅዎ ሙሐመድ-መኪን የሚያስተምሩበትን መሬት ግን ፈለጉ። እርስዎ ሳያውቁ ልጅዎን ሊያስደበድብ ሰው ላከ። ሼህ ሙሐመድ-መኪንም ወሬው ደርሷቸው አመለጡ። ወደ’ርሳቸውም ፈጠኑ። “ምንነው ልጅህ አይደለሁ ወይ?” ሲሉ ወቀሱ። ኋላም እርስዎ ቢሰሙ “ደጃች አብዱሰመድ ቀብሩ ይታዎቃል። ኣንተ ግን የምትሞትበትም የምትቀበርበትም አይታዎቅ” አሉ። ከዘመን በኋላ በደርግ ከተረሸኑ 60 ተገዳዮች አንዱ ኾነ።

*“የደርግ መኪና ሸራ የለበስሸው*
*ከበደ ዓሊ ወሌን ወዴት አደረስሸው?”*
ተባለ።

## ንባብ እና የድርሳን አበርክቶ

ተልጅነትዎ መጻፍ እንደጀመሩ ይነገራል። መደዱ ሲመጣ በብርዕዎ ማስታገሥ ነው። ቀን ማታ፣ ውስጥ እውጭ አይመርጡም። ደረሳዎ ሙሐመድ ሁሴን እንደተናገሩት “በሚያሳዝን መልኩ እበቅሎ ላይ ኾነው፣ በዝቅታ ተቆራምደው ይጽፉ ነበር” በአንድ ሌሊት ወይም ቀን፣ አንዳንድ ጊዜ በአንድ አፍታ መድብል ያዘጋጁ ነበር።

የመምህራቸውን ሼህ አህመደ-ዳንይ ግለ-ታሪክ የሚያትት “ያ ባህረል-መደድ” የተሰኘ ኪታብዎን በ “ዳልያ/ د” በረኽም እና አጭር 308 ስንኞች አዋቅረዋል። ስለእኚሁ መምህርዎ የተሰነደ ሌላ “ኑንያ/ ن”

የተባለ መድብል አለዎ። “ታእያ/ ت”፣ “ራእያ/ ر”፣ “ላምያ/ ل”፣ “ሚምያ/ م” … ወዘተ ከ120 ከላቁት ድርሳኖችዎ የሚጠቀሱ ናቸው። ግብፅ አዝሃር ዩኒቨርሲቲ ድረስ ተቀባይነት አግኝቶ ለማስተማሪያነት የበቃው “ሙህመል” የተባለ ድርሳንዎ የዘመኑን ዓለማቀፍ ሊቃውንት ያስደመመ ነው።

በዓረብኛውም በዓጀሙም(ዐማርኛ) እጅግ ተራቅቀውበታል። በረቂቅ ገለጻ፣ በጥጥር ቋንቋ፣ በጠሊቅ ድርደራ ያስደምማሉ። በሁለቱም ቋንቋ ቅኔ አመስጥረዋል። ግጥሞችዎ ከዓረብኛው ወደ ዐማርኛ የተተረጎመው እና እርስዎ በዐማርኛ(ዓጀም) የጻፉት ልዩነቱ ጉልህ ነው። የርስዎ ጥብቀቱ እስከ ልብ ነው። ዓረብኛዎም ረቂቅ ነው። ሼህ አህመድ ሙነወር እንዳሉት “ዓረበኛ ቋንቋ ዐውቃለሁ ብሎ የሼህ ጫሊን ኪታብ ያልተረዳ ዓረበኛ ያውቃል አልለውም።” በዓረበኛ ሲራቀቁ ለበርካቶች ቋንቋው ሲጠና እንዲህ ሲሉ ገጠሙ።

*“ባህሩን በሰፊና አሳውን በመረብ*
*ጃሂሉን በዓጀም ዓሊሙን በአረብ*
*በዓረብ ስንዘክረው ማዕናው ስንቱን አከረው፣*
*ባማርኛ እንሞክረው ቢገባው እጀሥራ።”*

መምህራቸው፣ ታላቁ ሼህ አህመደ-ዳንይ እንደመሰከሩት “ሠይድን ሳይጠቅስ፣ የሠይድን ጽሑፍ በቀላሉ የሚወስድ የለም” ይላሉ።

የንባብ ፍቅርዎ የመጠቀ ነበር። ለእስቲንጃ(ትጥበት) ሄድኩ ብለው፣ ተኝተው ያነብቡበት የነበረው ሜዳ ምስክርዎ ነው። መጽሐፍ ተውጭ ሀገር ተላከልዎ ሲባል በደረሰ፣ አልደረሰ ሲጨነቁ እንደነበር፣ የመጣ ቀን ደስታዎ እንደነበር፣ ለመጽሐፉ ቅበላ የታረዱት በሬዎች እና የተተኮሱት ጥይቶች ምስክርዎችዎ ናቸው። የተቀላቀለበዎት መዓልትና ሌሊቱ በንባብ እያልሉ ነበር። የኅልፈታችዎስ ቀን ተዕጅዎ መጽሐፍ አይደል የተገኘ?

# ኅልፈትዎ

በርካታ ሊቃውንት ኅልፈታቸው ሲቃረብ ይታወቃቸዋል። እርስዎም ቀደም ብለው አውቀውታል። በዟሂርም በምስጢርም ለቅርብዎችዎ አሳዎቁ። አደራዎትን አሳለፉ። አርብ፣ ሐምሌ 12፣ 1949 ከደረሳዎችዎ ጋር ተቀምጠው ኪታብ እያነበቡ በድንገት "አሏህ! አሏህ!" አሉ።

የመጨረሻ ቃልዎም ኾነ። ሀገር ምድሩ ተናጠ፣ ሰማይ ምድሩ ተናወጠ፣ ሳር ቅጠሉ ልቅሦ ተቀመጠ። "ሞቱ!" ተብሎ ወዲያው በየግዛቱ ተነገረ። ህዝብ ተምሞ ተገተረ። "እርሳቸውም እንደ-ሰው ይሞታሉ እንዴ?" አሉ ኅልፈትዎ ያልዘለቃቸው።

በነጋታው ተቀበሩ። ለቀብርዎ የመጣውን ህዝብ በአካል ያዩት፣ አኹን በህይወት ያልሉት ሼህ ዓብደላህ እድሪስ "ከህዝቡ ብዛት መተላለፊያ ጠፍቶ 300 ሜትር 4 ሰዓት ፈጀ!"። አንድም ሰው አልተገኘም - በእንባ የሚታጠብ ቢኾን እንጂ። ሼህ አህመደል ሃዲ ግጥማቸውን አወረዱ።

*"እንቅልፍም እንቢ አለኝ : በጎኔ መጋደም*
*መሄድም ተሳነኝ : መራመድ በቀደም*
*እንባዬ ፈሰሰ : ተቀላቅሎ በደም*
*የሊቆቹ ዋና ዛሬ ሲደመደም*
*ሞተ ወይ ሼህ ጫሌ ልክ እንደ በኒ- አደም?"*

ብለው በ "ሃያቱል ዓለም" ወጡት። ሰው እስ'በሱ ተደጋገፈ። እንባው ረገፈ። "ተዓምሩ" ጫሌ አለፈ። "ተርሳቸው ኅልፈት ኋላ እምድር ላይ የሚታይ አጣን" ተባለ።

# “የጎፋ ተረቶች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችና እንቆቅልሾች” መጽሐፍ ዳሰሳ



(በመ/ር ይርዳው ግፎ ዶምባ (በፎክሎር MA) )[1]




ዛሬ የምንመለከተው በ2016 ዓ.ም የታተመ አንድ የጎፋ ማኅበረሰብ ሥነቃል መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ በሁለትዮሽ (ጎፍኛ-አማርኛ) ቋንቋ ስነዳ መንገድ ተከትሎ የማኅበረሰቡ ቃላዊ ሃብቶችን ቀጥታ የመዘገበ ነው። በጎፍኛ ቋንቋ በ88ገጾች፣ በአማርኛ ደግሞ በ95ገጾች ተዘጋጅቶ ቀርቧል። ተመሳሳይ ይዘት ያለው በሁለት ቋንቋ የተዘጋጀ አንድ መጽሐፍ።

የመጽሐፉ አዘጋጅ አቶ ግርማ ቡኬ ጩዶ ሲሆን አርታኢዎች ደግሞ ደመቀ ግዛቸው፣ አረካ አደም እና አቶ ኡርጋሞ ዚዳ ናቸው። የሥነቃሉ ሰብሳቢዎች ደግሞ አረካ አደም እና ሙናኔ ሙካኖ ናቸው። ከጎፍኛ ወደ አማርኛ ተርጓሚው አቶ አረካ አደም ናቸው። አሳታሚው ደግሞ ደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ነው። የመጽሐፉ አዘጋጅ አቶ ግርማ ቦኩ በሥነ ቃል ጥናትና ስነዳ ዘርፍ ልምድ አላቸው። የበርካታ ማኅበረሰብ ባህላዊ ገጽታዎችን መዝግበው በማሳተም የረጅም ጊዜ ተሞክሮም አድብረዋል። ይሄንንም ከመጽሐፉ መግቢያ ላይ ካለው የግርጌ ማስታወሻ መረዳት ይቻላል።

## ክፍል አንድ

አስቀድመን “የጎፋ ተረቶች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችና እንቆቅልሾች” በሚል በአማርኛ ተሰይሞ የተዘጋጀውን የሥነ ቃል ጥራዝ ሙላት-ጉድለቱን እንይ። በመጽሐፉ መግቢያ ለመመልከት እንደሚቻለው፣ መጽሐፉ በሦስት ክፍል ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው።

---

1 መ/ር ይርዳው ግፎ፣ በአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ የሳውላ ካምፓስ ሚድያና ተግባቦት ት/ቤት የጎፍኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ት/ት ክፍል ሌክቸረር፣ በጎፍኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ BA ዲግሪ ከአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ፣ በፎክሎር-ባህል ጥናት ሁለተኛ ዲግሪ(MA) ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ አግኝቷል። መምህር ይርዳው የሁለተኛ ዲግሪ ጥናቱን “የቃልቻ ቀን እና የታላቅነት አሰጣጥ ክዋኔ ትውን ጥበባት ገጽታና ማህበረ-ስነ ልቦናዊ ፋይዳ በጎፋ ዞን ዛላ ወረዳና ሳውላ ከተማ ቃልቾች” በሚል ርእስ በማጥናት በነሐሴ 17 ቀን 2014 ዓ.ም አቅርቧል። ጥናቱ በዩኒቨርስቲው ድረገጽ: “http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/14689” ላይ ይገኛል። መምህር ይርዳው ስለ ጎፋ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ መረጃ የሚያጋራበት የቴሌግራም ገጽ: https://t.me/go1Culture2history94 ይገኛል። መምህር ይርዳውን ማግኘት ይችላሉ።

ለበለጠ መረጃ:
Phone: +251992205594
Email Address: gifoyirdaw9@gmail.com
On Telegram: @yirdawofgifo

በመጀመሪያው ክፍል 21 የቃል ትረካዎች (ተረቶች፣ አፈታሪኮች፣ ሐተታ ተፈጥሮዎች...)፣ በመቀጠልም 176 የጎፋ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና በሦስተኛውና የመጨረሻው ክፍል 82 የጎፋ እንቆቅልሾች ከነመልሶቻቸው ተካተውበታል።

የጥንቅሩ ዓላማዎች ሦስት ናቸው በቅድሚያ ቃላዊ ሃብቱን ሰንዶ ለማቆየትና ለማስተላለፍ፤ ሁለተኛ ደግሞ የጎፍኛ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ለመደገፍ ብሎም ቃላዊ ሀገር በቀል እውቀቱን ለሌሎች ለማስተዋወቅ፤ ሦስተኛ ለተመራማሪዎች ተጠቃሽ የመረጃ ምንጭ እንዲሆን።

በመጽሐፉ መግቢያ ላይ የተቀመጡ ሃሳቦች ምጥን ያሉ እና ሙያዊ የንድፈ ሃሳብና ጽንሰ ሃሳብ ይዘዋል። የሃሳብ አወራረዱም ያማረ ሆኖ አግኝቻለሁ። አዘጋጁ የሥነ ቃሉን አሰናነድ ግልጽ በሆነ መንገድ ለማቅረብ ያደረገው ጥረትም ይበል ያሰኛል።

ሌላው ማለፊያ! የሚያሰኘው፣ የየተረቶቹ እና የቃለ ትረካዎች የርእስ አሰጣጥ ነው። የሁሉም ባይሆን አብዛኛዎቹ ርእሶች አጭር፣ ግልጽና አይረሴነት ጠባይ ያላቸው ሆነው አግኝቻቸዋለሁ።

*በአጠቃላይ በአማርኛው ጥራዝ የታዩኝን ጉድለቶች እንደሚቀጥለው ማስቀመጥ ይቻላል።*

፩) የቃላዊ ፎክሎሩን አሰባሰብ ሂደት በመግቢያው በዝርዝር አለመገለጹ-አውድ ተኮር የአጠናን ዘዴ አለመከተሉን ያሳያል። አውድን መሠረት ያላደረገ የባህል ቅንጣት ስብስብ ደግሞ ትርጉሙ ከሙላቱ ይልቅ ጉድለቱ ይጎላል። ምክንያቱም አሁናዊ የፎክ-ቡድን ሃብት መሆን አለመሆኑን፣ ፎክሎሩ (ሥነ ቃሉ) ሕይወት ያለው መሆኑን የምንረዳው ከትክክለኛው አውድ ሲቀዱ ነውና ነው።

፪) የሥነ ቃሉ ሰብሳቢዎች እንዴት፣ ከማን፣ መች፣ በምን ያክል ዙር፣ ከየት (ከየትኛው ማኅበራዊ አጋጣሚ... ከሠርግ፣ ከለቅሶ...) የሥነ ቃሉን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ምን ምን ሂደቶችን አለፉ? የሚሉ ሃሳቦች መነሳት ይገባቸዋል።

፫) እንደ ጥናትም እንደ ጥንቅርም የተዘጋጀ መጽሐፍ በመሆኑ በጎፋ ማኅበረሰብ ሥነቃል ላይ የተሠሩ ቀደምት ሥራዎች ተከልሰው (Review background) በአጭሩም ቢሆን አለመቅረቡ የመጽሐፉ ክፍተት ነው። ምክንያቱም የማኅበረሰቡ ሥነ ቃል ሲሰነድ ይህ የመጀመሪያ ሥራ አለመሆኑን የሚጠቁሙ ቀደምት ሥራዎች መኖራቸው እሙን ስለሆነ።

በጎፋ ማኅበረሰብ ባህላዊ ገጽታ ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶች፣ የተጻፉ መጻሐፎችና መጽሔቶች ይኖራሉ፤ አሉም። ሌሎችን ትተን ለአብነት አንዱን ብቻ አንስተን እንይ።

ከአሁኑ መጽሐፍ ጋር ቀጥታ በሚመሳሰል ርእስ በ2000 ዓ.ም፤ በጊዜው በጋሞ ጎፋ ዞን የባህል ማስታወቂያ መምሪያ ተዘጋጅቶ የታተመ "የጋሞ ጎፋ ብሔረሰቦች ሥነ ቃል" የተሰኘ መጻፍ ታትሟል። በዚህ የሥነ ቃል መጽሐፍ በአጠቃላይ 266 የጎፋ ማኅበረሰብ ምሳሌያዊ ንግግሮች (Tosseta)፤ 48 እንቆቅልሾች (Qon77isheta) እና 30 የሚሆኑ እንካሰላንቲያዎች (Sedhemenkketa) ተካተውበት ቀርቧል።

ስለዚህ በአሁኑ መጽሐፍ ምን ምን ጉዳዮች እንደታከሉበት፤ ምን ጉዳዩች ደግሞ እንደተደገሙ ቢገለጽ የተሻለ ይሆን ነበር። እነዚህ ክፍተቶች በሌሎች አጥኚዎች ወይም በዚሁ መጽሐፍ ዳግም ሕትመት ይስተካከላሉ ብዬ በማመን በአማርኛው ጥራዝ ላይ የማነሳውን ሃሳቤን እገታለሁ። ከዚህ በመቀጠል የጎፍኛውን ጥራዝ እንመልከት።

# ክፍል ሁለት




"Goofatho Hayseta, Tossetanne Sedhemenkketa"

በዚህ ክፍል የጎፋ ማኅበረሰብ ቃላዊ ሃብቶች ስብስብ የጎፍኛ መጽሐፍ ከቅርጽ እስከ ይዘት፤ ከሥርዓተ ጽሕፈት እስከ መልክዓ ገጽ ያሉትን ጉዳዮች በቋንቋው (ጎፍኛ) መሠረት ላይ ቆመን እንፈትሻለን።

ለGoofatho ጥንቱ Goofa የተሰኘው ማኅበረሰብ ነው። "Goofa" የሚለው ቃል ማኅበረሰቡ ሰፍሮ የሚገኝባቸው ቦታዎች መጠሪያ፤ አንድም ቦታው ላይ ሰፍረው የሚገኘው ማኅበረሰብ መጠሪያ ነው። ቀዳሚው ጎፋ መሰኘቱ "ማደሪያ"፤ ተከታዩ ደግሞ ጎፋ መባሉ በ "አድጎሪው" ሲጠራ እንደ ማለት ነው።

ቋንቋው ጎፋሦ' ይባላል። ጎፋሦ' በጎፋና በሌሎች አጎራባች ዞኖች መግባቢያ ሆኖ የሚያገለግል ሰሜን ኦሞአዊ የቋንቋ ግንድ ያለው ነው። በቋንቋው ከዛሬ 30 ዓመታት በፊት ሰሜን ኦሞአዊ የፊደል ገበታ በሚል በ'ላቲን' የድምጸ ልሳን ውክልና(አጻጻፍ) ሥርዓት በመከተል 21 ነጠላ ተነባቢ ፊደሎች፤ 9 ድርብ እና 5 አናባቢ ፊደላት፤ በድምሩ 35 ፊደላት ተቀርጸውለት ወደ ጽሑፍ ቋንቋነት የሚያደርገውን ጉዞ ጀመረ።

በዚህ ሁኔታ የጀመረው የጎፍኛ የጽሑፍ ቋንቋነት ታሪክ እስከ 1990ዎቹ አጋማሽ ድረስ ከሌሎች ሰሜን ኦሞ ቋንቋዎች ጋር በመሆን እየተሠራበት ቆይቶ፤ ራሱን ችሎ፤ በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ እና ማስተማሪያ መጽሐፍት በጎፍኛ ቋንቋ እየተዘጋጁ እስከ አሁን ትምህርት እየተሰጠበት ይገኛል።

ለመማር ማስተማር ሥራ በጎፍኛ ቋንቋ መጽሐፍት የተዘጋጁበትን ጊዜና የክፍል ደረጃዎች በአጭሩ እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል።

◊ 1998 ዓ.ም ከ5-8ኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ለመስጠት መጽሐፍ ትታትመው አገልግሎት ላይ ውለዋል።
◊ በ2000 ዓ.ም የ1-4ኛ ክፍል ሁሉም የትምህርት ዓይነቶች በጎፍኛ ቋንቋ ተዘጋጅተው ታትመዋል። በዚሁ ዓመት ጎፍኛ ከ5ኛ እስከ 12ኛ ክፍል እንደ አንድ ትምህርት ዓይነት ተዘጋጅቶ ሲሠራበት ቆይቷል።
◊ 2003 ዓ.ም፣ ጎፍኛ ከ9ኛ እስከ 10ኛ ክፍል እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ለትምህርት ሥራ ጥቅም ላይ ውሏል።
◊ በ2007 ዓ.ም ለ11ኛ እና 12ኛ የክፍል ደረጃዎች እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ተዘጋጅቶ ትምህርት እንዲሰጥ ተደርጓል።
◊ 2014 ዓ.ም ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል ድረስ ሁሉም የትምህርት ዓይነት በጎፍኛ ተዘጋጅተው በመታተም ሥራ ላይ ውለዋል።
◊ በዚሁ የህትመት ዘመን፣ (2014 ዓ.ም) ከ7ኛ-10ኛ ክፍል ጎፍኛ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ተዘጋጅቶ መማር ማስተማር አገልግሎት እየተሰጠበት ይገኛል።

በሌላ መልኩ ደግሞ፣ ጎፍኛ ቋንቋ በሰርተፍኬት (ከ1991 እስከ 1997 ዓ.ም) ፣ ከ2001ዓ.ም ጀምሮ በዲፕሎማ በአርባምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ፣ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በመጀመሪያ ዲግሪ በአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ በመደበኛ ፕሮግራም፣ እንዲሁም ከ2009 ዓ.ም በክረምት መርሃግብር እንደ አንድ ትምህርት ክፍል ተደራጅቶ በቋንቋው ተማሪዎች እየተማሩ እና እተመረቁ ወደ ሥራ እየተሰማሩ ይገኛሉ።

በዚህም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመሰልጠን በጎፍኛ ቋንቋ ማኅበረሰብን የሚያገለግሉ የተለያዩ ባለሞያዎች ማለትም፣ የህዝብ ግንኙነት ኦፊሰሮች፣ ጋዜጠኞች፣ መምህራን እና መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆችን ማፍራት ተችሏል። ከትምህርት መርጃ መሣሪያነት አልፎ፣ በተለያዩ ጊዜያት መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ጎፍኛ ቋንቋ በመተርጎም ለሃይማኖት ተቋማት የስብከት አገልግሎት እየተሰጠበት ይገኛል። ለአብነትም:-

• በ1927/28 ዓ.ም የማርቆስ ወንጌል ብቻ በጎፍኛ ቋንቋ ተተርጉሞ (በሳባ ፊደል) ለስብከት አገልግሎት ውሏል።
• 2011 ዓ.ም ደግሞ አዲስ ኪዳን ብቻ ወደ ጎፍኛ ቋንቋ ተመልሶ በቋንቋው ተናጋሪዎች ጥቅም ላይ ውለዋል።
• 2016(?) ዓ.ም(ተመርቆ የተሰራጨበት) ብሉይ እና አዲስ ኪዳን መጽሐፍ በጎፍኛ ቋንቋ ተተርጉሟል።

ጎፍኛ ቋንቋ የራሱ የሆነ የሰዋስው፣ አጻጻፍ እና መሠረታዊ ድንጋጌዎች ያሉት ቋንቋ ነው። በመሆኑም እስከ ዛሬ ድረስ የተሠሩት የጽሕፈት ሥራዎች የቋንቋውን ሥርዓት ጽሕፈት ተከትሎ፣ አንድም የቋንቋውን የአጻጻፍ መንገድ እያዳበረ ለዚህ በቅቷል። ስለዚህ ልብ የምንለው ጉዳይ:-
1. የቃላት መጥበቅና መላላት (Minnidinne leppidi nabbab tethi) በተነባቢ ነጠላነትና ድግመ ጽሕፈት፤
2. የቃላት ረዝመውና አጥረው መነበብ *(aduqqidinne qaammidi nabbabetethi)* በአናባቢ ነጠላ ሆኖ መጻፍና መደገም፤
3. የትንሽና ትልቅ ፊደላት አጠቃቀም (Guuthanne wogga pidaleta go7etetha wogaa)
4. አንዳንድ ልዩ ባህርይ ያላቸው ፊደላት (በተፈጥሮ ጠንካራ የሆኑ እና ሲጻፉ ማጥበቅን ለመግለጽ ተደግመው የማይጻፉ) እና በቃል መነሻ ላይ የማይጻፉ ፊደላት... ወዘተ። በጎፍኛ ቋንቋ ሥራዓተ ጽሕፈት መኖራቸውን ማወቅ ያሻል።

በ88 ገጾች የተቀነበበውና በጎፍኛ ቋንቋ የተዘጋጀው ይህ "የጎፋ ማኅበረሰብ ሥነ ቃል" መጽሐፍ ፣ ርእሱ እንዲህ ይነበባል።

*"Goofatho Haysseta, Tossetane Sedhemnketa"*
*"Dugeha Tophiya Kilille Kawotetha Wogganne Turizime Biiro"*
ውድ አንባቢዎቼን መጠቆም የምፈልገው፣ የጽሑፉ መመልከቻዬ የጎፍኛ ቋንቋ ሥርዓተ ጽሕፈት ሲሆን፣ የማንጸሪያዬ አቅጣጫ ደግሞ የመጽሐፉ ቅርጽና ይዘት ብቻ ነው። ለዚህም የመጽሐፉን መልካም ጎን በማውሳት አድናቆት፣ ስህተቶችንም በመንቀስ በጎውን መንገድ ማሳየት የትኩረት ነጥቦቼ መሆናቸውን ከወዲሁ እገልፃለሁ።

በጎፍኛው ጥራዝ የታዩ መልካም ነገሮችን ላስቀድም። በጎፍኛ ጥራዙ በሁሉም ምዕራፍ መግቢያ ላይ የቀረቡ የየሥነ ቃሎች ምንነት፣ ዓይነት፣ ጥቅምና የሥነ ቃሎቹ አቀራረብ መንገድ የሚመለከቱ ማብራሪያዎች ወሳኝ፣ አስፈላጊ እና ገላጭ መሆናቸውን ተገንዝቤያለሁ። በየማኅበረሰቡ የሚነገሩ፣ የሚተረኩ ቃለ ታሪኮች አንዳንዶች የራሳቸው አቀራረብ ቅደም ተከተል ያላቸው መሆኑን በሚጠቁም መልኩ፣ በጎፋዎች ባህል ተረት ዝም ተብሎ መነገር አይጀመርም። የራሱ የተረት አቀራረብ ቅደም ተከተል ይኖራል።

ለምሳሌ በጎፍኛ
ሀ. ተረት ተራች:- Haysey hanees. ለ. አድማጭ (ጮች): Harey qooxees.
ይልና ተረቱን መናገር ይቀጥላል። በመጨረሻም ተረቱን ተናግሮ ስጨርስ "... Haysey hayse gakko." በማለት ይዘጋል። እነዚህ የተረት አቀራረብ መንገዶች ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ የሚለያዩ ሲሆን፣ ተረታቸው ሲጠና እና ሲሰነድ አቀራረብ መንገዶችም በትኩረት መጠናት አለባቸው። በ"ጎፋ ተረቶች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችና እንቆቅልሾች" አማርኛው ላይ ግን ጎፍኛ ተረቶች አቀራረብ መንገድ ሳይገለጽ መታለፉ እንደከፍተት ቢታይም በጎፍኛው ጥራዝ ማብራሪያው መካተቱ መልካም ነው።

"Goofatho Haysseta, Tossetanne Sedhemnketa"፣ መጽሐፍ ከቀዳሚዎች ገጾች ማለትም ከምስጋና እና ከመግቢያ ገጾች በስተቀር፣ ምዕራፍ አንድ እስከ ሦስት የቀረቡ ሃሳቦች በሙሉ፣ በይዘት በኩል የጎፍኛን ሥርዓተ ጽሕፈት ማለትም በቃላት ቅንጅት፣ በፊደል አጻጻፍም ሆነ በሥርዓተ ነጥብ በኩል ጥንቅቅ ያለ፣ ሲያነቡት የማይጎረብጥ መሆኑን አለመመስከር አይቻልም።

ሌላው ጥራዙ ውስጥ የተመለከትነው በጎ ነገር፣ የየተረቶች ጭብጥ በሥዕል ለመግለጽ የተደረገው ጥረት ነው። በተለይ ቃላዊ ተረኮች በጥሩ ቃለ ታሪክ አቅራቢዎች ሲነገሩ፣ ምስል ከሳችና ድራማዊ ቅርጽ ያላቸው ይሆናሉ። ታሪኩ (ተረቱ) በቃል ቢገለጽም በውስጡ የተቀረጹ ገጸ ባህርያት የሚፈጽሙትን ድርጊት በዓይናችን እንድናይ ያደርጋል። ተረቶችን በሥዕል ማስደገፉ በተለይም ለታችኛቹ የክፍል ደረጃዎች ለመማር ማስተማር ሥራ ለማዋል እና ታሪኩን ፈጥነው እንዲረዱት ያግዛቸዋል።

በጎፍኛው ጥራዝ በዋናነት ሁለት ችግሮች ተስተውለዋል። እነዚህም ርእስ፣ ምስጋና እና መግቢያ ላይ በተቀመጡ ጽሑፎች ላይ የታዩ የአጻጻፍ እና የፊደል አጠቃቀም ችግሮች ናቸው። ወደ ጎፍኛ ቋንቋ ሥርዓተ ጽሕፈት ስንሄድ፣ ቀዳሚው ጉዳይ አናባቢዎች ልዩ ባህርያት ማለትም በአናባቢ ፊደላት አነባብ፣ "ማጠር" -ነጠላ ተደርጎ መጻፍ፣ እንዲሁም "መርዘም" - ሁለት ጊዜ መጻፍ እና ያንን ተከትሎ፣ በቃላት እርባታ ወቅት የሚታዩ የትርጉም ለውጦች ቀዳሚ ጉዳዮች ሲሆኑ፣ ሌላው ደግሞ የጎፍኛ ተነባቢዎችን ሞያ ልብ ይሏል።

ይሄውም ተነባቢዎች በቃል ውስጥ ነጠላ ተደርጎ መጻፍ የቃሉን መላላት ለመግለጽ፣ እና ሁለቴ (ሁለት ጊዜ) መጻፍ መጥበቅን ለመግለጽ እንደሆነ፣ ያን ተከትሎም የሚታይ የቃላት ትርጉም ለውጥ በትኩረት መመልከት ተከታይ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም በጎፍኛ ቋንቋ በጽሑፍ ተግባቦት፣ የአጻጻፍ ችግር የሚከሰተው የቋንቋውን ሥርዓተ ጽሕፈት ጠንቅቆ ካለማወቅ የሚመነጭ ችግር ነው እንላለን።

## በመጽሐፉ ርእስ እና ፊት ገጽ ላይ የታዩ የፊደል አጠቃቀም ግድፈቶች

"Goofatho Haysseta, Tossetane Sedhemnketa" ይላል የመጽሐፉ ርእስ። በዚህ ላይ ሁለት ችግሮች ታይተዋል። እነዚህም፣ ነጠላ ፊደል መጻፍ ያለበት ቃል ተደግሞ፣ ሁለቴ መጻፍ የነበረበት ነጠላ መሆን። ይህን ሃሳብ ግልጽ ለማድረግ ርእሱ ላይ… Hayssета … በሚለው ቃል ላይ፣ በጎፍኛ ቋንቋ 'hayse' ማለት ተረት ነው። ሲጻፍ ደግሞ ፊደል "s" ነጠላ ሆኖ ይጻፋል። በቃሉ የሚጠብቅ ድምጽ የለውም። ስለዚህ Hayseta እንጂ Haysseta ተብሎ አይጻፍም። ስህተት ነው።

በመጽሐፉ ርእስ ላይ ሁለተኛው ችግር ተደግሞ መጻፍ የነበረበት ፊደል ነጠላ ተደርጎ የመጻፍ ችግር ነው። ቃሉ “Tossetane” ሲሆን፣ በቃሉ ውስጥ ‘n’ ፊደል ሁለቴ ተጽፎ ጠብቆ መነበብ ይገባዋል። “Tossetane” የሚለው ቃል፣ “… Tossetanne…” ተብሎ መጻፍ አለበት።

ሌላው በመጽሐፉ ፊት ገጽ ላይ የተፈጠረው የፊደል አጻጻፍ ግድፈት፣ የመጽሐፉ አሳታሚ ተቋም ስም ላይ የተመለከተው ነው። “Dugeha Tophiya Kilille Kawotetha Wogganne Turizime Biiro” በሚለው ውስጥ፣ በቋንቋው ሥርዓተ ጽሕፈት፣ Tophiya የሚለው ቃል Tophphiya መባል፣ Wogga የሚለው ቃል ደግሞ Woga ተብሎ ፊደል “g” ሳይደገም (ሳይጠብቅ) መጻፍ አለበት። ምክንያቱም በቋንቋው Wogga ማለት ትልቅ፣ ሲሆን Woga ማለት ባህል ማለት ነው። ስለሆነም ባህልና ቱሪዝም ለማለት፣ Woganne Turizime መባል አለበት። በሦስተኛውና በአዘጋጆቹ መግለጫ ገጽ ላይ የታዩ የፊደል አጻጻፍ ችግሮችን በገረፍታ ስንጠቁም፡-

» “Geeshi Xeelidayssati” የሚለው ሐረግ Geeshshi Xeellidayssati መባል አለበት።
» “Gido Eesho” የተባለው Giddo Eesho አድርጎ መጻፍ ያስፈልጋል።

ሌላኛው የዚህ ጥራዝ ችግር “Galata-ምስጋና” ጽሑፍ ላይ የታየ የፊደል አጠቃቀም ችግር ነው። በተለይም በዚህ ርእስ ሥር የመጀመሪያውን አንቀጽ ብቻ ወስደን ለአብነት የጽሕፈት ግድፈቶችን አሳይተን እንለፍ። Wogga Pidaleta Go7etetha Maaraa- በቋንቋው የትልቅ ፊደል አጠቃቀም፣ ችግር በአንዱ አንቀጽ ብቻ ከሰባት በላይ ስህተቶች ተገኝተዋል። ስንዘረዝራቸው፡-

- 2015 m.l በሚለው ምህፃረ ቃል ውስጥ፣ Maarota Laytha ለሚለው በጎፍኛ M.L ተደርጎ በትልቅ ፊደል መጻፍ አለበት።

- Dugeha tophiya ተብሎ መጻፉ ስህተት ሲሆን መጻፍ ያለበት፣ Dugeha Tophphiya ተደርጎ ነው። ምክንያቱም በቋንቋው የሀገር፣ የአቅጣጫ እና አካባቢ ወዘተ.ስሞች ሲጻፉ፣ በ “Wogga Pidale-በትልቅ ፊደል” ይጻፋሉ። ይህም ሁለት ጊዜ tophiya የተባለው Tophphiya ተብሎ በተመሳሳይ መልኩ መስተካከል አለበት እንላለን።

- የሰዎች ስም በ “guutha pidale- በተንሽ ፊደል” አይጻፍም። ለምሳሌ የተፈጠረው ስህተት firehiwot dubale ተብሎ መጻፉ ግድፈት ሲሆን፣ Firehiwot Dubale ተብሎ መስተካከል ይገባል። በተጨማሪም “milkiyaas kalsa-Milkiyaas Kalsa” መባል አለበት።

በመጽሐፉ ምስጋና ጽሑፍ ላይ የተፈጠረው ሌላው ችግር በአጻጻፍ ላይ ቃላት መጥበቅ (ፊደላት ሁለቴ መጻፍ) ሲገባ ነጠላ አድርጎ መጻፍ ችግር ነው። በዚህ ጉዳይ በመጀመሪያው አንቀጽ ላይ ብቻ ከ81 ቃላት፣ በትንሹ በአሥራ ሁለት ቃላት ውስጥ ስህተት ተገኝቶበታል። ሁሉም የምስጋና ገጾች በእንደዚህ ዓይነት ስህተቶች የተሞላ መሆኑን ገልጸን እዚህ መዘርዘሩን በመከተት ወደ Gelo-መግቢያ ገጽ እንሻገር።

Gello (Gelo) እንግዲህ መግቢያ ለማለት የተሰጠ ርእስ መሆኑ ነው። ይህ አጻጻፍ ስህተት ነው። Gelo መግቢያ ማለት ሲሆን በቃሉ ውስጥ ተደግሞ የሚጻፍም ሆነ የሚጠብቅ ድምጽ የለውም። በመሆኑም ገና ርእሱ ላይ የተፈጠረው የአጻጻፍ ችግር የመግቢያው ሃሳብ እስኪጠናቀቅ ድረስ ይዘልቃል።

... ይቀጥላል ስህተቱ። Billa oddati... ጸሐፊው "Bila odati..." ለማለት የፈለገ ይመስላል። ሥነ ቃሎች ማለት ነው። እንደ ሚታወቀው፣ ከቃላት መጥበቅና መላላት የተነሳ የፍቺ-ትርጉም ለውጥ ወይም ትርጉም ማጣት ይከሰታል።

"Bila" ማለት "ሥነ" ሲሆን ጥብቆ Billa ተደርጎ ሲጻፍ "ፍታ" የሚል ትእዛዛዊ ቃል ይሆናል። Oda ማለት ነገር፣ ዜና ወይም ቃል የሚል ትርጉም ሲሰጥ፣ Odda ቆሻሻ የሚል ትርጉም አለው። ስለዚህ ከአውዱ የምንረዳው "Bila oda" ተብሎ መጻፍ እንዳለበት ነው። ሌላውን አንዱን አንቀጽ ቀጥታ ጽፈን አጻጻፍ ግድፈቶችን በመጠቆም ጽሑፋችንን እናበቃለን።

××××× ×××××× ×××××××

Gello [Gelo]

Billa[bila] oddati[odati] odetethan haysen woyko[woy] yethan eretida [erettida] deretan ayso cincatethanine [cinccatethininne] ikonome gahetethan, dere issipetethan, mino qofan, cincatethan [cinccatethan], tumatethan, maara h.h.m shiishi oyqida medho qaala. Billa [Bila] odati Beni asa na7a taariken beetidaba [beettidabaa] shiiqidaba iyapeka woga kaalethiyabane [kaalethiyabaanne] dichiya guuge [guugge/kaha] qofa murruta [muruuta]. Bila oddi [odi] issi derey banatethane [banatethaanne] bawoga [ba wogaa] hara deriyas de7iya qofane [qofaanne] xeeluwa qonciso, baqofa [ba qofaa] amanuwa [ammanwaa], medhetetha beetuwa ... h.h.m de7iya erathetatha [eratethata] qoncisanaw ha7isine [ha7isinne] Yana [yaanaa] yeletas athanaw [aathanaw] dandda7isiya [dandda7osona?].

××××××× ×××××× ×××××××

በመጽሐፉ መግቢያ ጽሑፍ በቀዳሚው አንቀጽ ላይ የታዩ የአጻጻፍ ችግር ከላይ የተቀመጠውን ይመስላል። [_]ወስጥ አስምረን ያመለከትነው በትክክለኛው የጎፍኛ ሥርዓተ ጽሕፈት ተከትሎ ሲጻፍ ያለውን መልክ ለማሳየት ነው።

እንደ መውጫ፣ በጎፍኛው ጥራዝ በዋናው ጽሑፍ ላይ የጎላ ችግር አልተስተዋለም። ይሁን እንጂ በመጽሐፉ ፊት ገጽ ማለትም ርእስ፣ ምስጋና እና መግቢያ ጽሑፎች የመጻሐፉን ጥራት የሚያወርድ፣ በር ላይ እንደተቀመጠ እንከን እና ክርፋት ሆኖ ታይቷል። በጽሑፉ ላይ የተፈጠረው ችግር ከጸሐፊው፣ ለቋንቋው እንግዳ ከመሆን የመነጨ፣ አሊያም በማን አለብኝነት የተጻፈ የድፍረት ውጤት ነው። ስለዚህ ሥራው ፍጹም ምስጉን እንዲሆን የመጽሐፉ በጎፍኛው ጥራዝ ምስጋና እና መግቢያ ጽሑፎች በትክክለኛ ጎፍኛ አጻጻፍ መንገድ ዳግም መጻፍ አለባቸው። ይህን የምንለው የሚጽፉ እጆችን ብእር ጥለው፣ ታጥፈው እንዲቀመጡ ሳይሆን ጽሑፋቸውን ይበልጥ እንዲያበለጽጉ ከማበረታታት ጋር ነው።

አመሰግናለሁ!

(ጥር 2017፣ አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ሣውላ ካምፓስ ሣውላ ኢትዮጵያ)

# አዲስ ልብስ ወዳለሁ!

(በሳምራዊት ንጉሤ)



ልጅ እያለሁ ለበዓል ልብስ ይገዛልኝ ነበር። የሚያምር ቬሎ ቀሚስ አበባ ካለባት የምታምር ቋቋ ጫማ ጋር ወይም ደግሞ ሱሪ ጎኑ እና ጎኑ ጋር ከሚበራ ሽፍን ጫማ ጋር። ልብስ ሲለሚገዛልኝ ዓመት በአል ሲመጣ ደስ ይለኛል። ብዙ ጊዜ ለአዲስ አመት እና ለፋሲካ አዲስ ልብስ ይኖረኛል። ታድያ የምጓጓው አዲስ ልብስ ለመልበስ ብቻ አይደለም። ከአመት በዓል ቀጥሎ ያለው ቀን ወደ ትምህርት ቤት ስሄድ ዮኒፎርም ሳላደርግ የተገዛልኝን አዲሱን ልብሴን ለብሼ ነው የምሄደው።

በፊት ላይ ጓደኞቼ እንዲሆኑ የምፈልጋቸው ልጆች ግን ፊቴ ላይ ወቶ አልጠፉም ባለኝ ኪንታሮት ይስቁብኛል። እህቴ “የልጆች ጊዜ” ቴሌቪዥን ዝግጅት ላይ አንድ ምታምር ልጅ ተሰርታ ያየችውን ዝክዛክ የፀጉር ሹርባ ስትሰራኝ “እባብ ስራ ተሰርታ መጣች” እያሉ እያሯሯጡ ያስለቅሱኝም ነበር። አሁን እነዛ ልጆች አዲስ ልብስ ለብሼ ስሄድ ከአጠገቤ አይርቁም። እጄን ለመያዝ ይሽቀዳደማሉ። እኔ ነኝ አጠገቧ የምቀመጠው እያሉ ይገፈታተራሉ። ያቺ የተገዛችልኝ ቀሚሴ የዛን ቀን እንደ ልዕልት አስከብባኝ ትውላለች። ለዛ ነው አዲስ ልብስ ምወደው።

አሁን አድጌ ሰዎች አምሮብሻል ካሉኝ የሚያምር ልብስ ለብሻለሁ ማለት ነው። በፊት እጁን የሚዘረጋልኝ ወንድ አሁን ካቀፈኝ አምሮብኛል ማለት ነው። ግን ያን ልብስ ነገ ብደግመው ያ ሁሉ ፍቅር እንደማይኖር አውቃለው። ልክ በልጅነቴ ጊዜ እንደነበረው።

በሰው ለመከበብ፣ አምሮብሻል ለመባል፣ ትንሹም ትልቁም አጠገቤ እንዲሆን፣ ሁሉም እንዲወደኝ ምታምር ልጅ ለመባል፣ ያቺ ዘናጪ፣ ለመባል ደሞዝ እንደተቀበልኩ ወደ ልብስ ገበያ ሮጣለው። “ሰው ምን ለበሽ እንጂ ምን በላሽ አይልም” ይላል የሀገሬ ሰው። ለዛ ነው መሰለኝ ሁሉም መከፋቱን፣ ማጣቱን፣... በልብስ ሸፍኖት የሚሄደው። “ይሄ ልጅ ግን ደህና ነው” ብለው ሲያወሩ “አላየሽውም እንዴ አምሮበት? የሌለ ዘናጭ ሆኗል እኮ” ይባልለታል። እኔም “ደህና ናት አምሮባታል” እንዲሉኝ፣ የራቁኝ እንዲቀርቡኝ፣ የሆኑ ሰዎችን ለማናደድ...

አዲስ ልብስ ወዳለሁ!

የወር ሰው ይበለን

# ምርትና አግልግሎትዎን ያስተዋውቁ!




bayradigital@gmail.com

ባይራ

ባይራ ዲጂታል መጽሔት

ሃሳብ አስተያየታችሁን በኢሜል አድራሻችን bayradigital@gmail.com

አልያም በማህበራዊ ትስስር ገጾቻችን

ባይራ ዲጂታል መጽሔት

Bayradigital

@Bayradigital

www.bayradigital.com